መጠጥ ቤት ውስጥ በተፈጠረ ጊዜያዊ ፀብ ያስከፈለው ዋጋ

ገጽ 10

ልብ ውልቅ - በመንገድ ላይ...

ገጽ 11

ጠንካራ መሠረት የጣለው የንግድ ሥራ- ከኢትዮጵያ እስከ ቻይና

ገጽ 13





# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

83ኛ ዓመት ቁጥር 103 ታኅሣሥ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የፕሮጀክቱን አፈጻጸም ገምግመዋል

# የኮይሻ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ 62 በመቶ ደረሰ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኮይሻ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት በተለወጠ የፕሮጀክት አስተዳደርና ክትትል ሥርዓት የአጠቃላይ የግንባታ አፈጻጸሙ 62 በመቶ መድረሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የኮይሻ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ያለበትን ደረጃ ትናንትና ገምግመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትናንት በማህበራዊ ገጻቸው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ "ከ2013 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ለ12ኛ ጊዜ ባካሄድኩት የኮይሻ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግምገማ በለወጥነው የፕሮጀክት አስተዳደር እና ክትትል ሥርዓት የተነሳ የአጠቃላይ ግንባታው ሂደት 62 በመቶ መድረሱን በመመልከቴ ደስታ ተሰምቶኛል" ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአፍሪካ ደረጃ በግዙፍነታቸው አንደኛ እና ሶስተኛ የሆኑት የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ እና የኮይሻ ግድቦች ባለቤት በመሆናችን የንፁህ የኃይል

የኮይሻ የሃይል ማመንጫ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ፎቶ፡ አዩብ ተሬረ

## "ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት የምታደርገው ጥረት ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ ነው"

\- ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት የምታደርገው ጥረት ጦርነትን እንደ አማራጭ ያልያዘ ፍጹም ሰላማዊ እና ሕጋዊ ነው ሲሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውሃ ሳይንስ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ ገለጹ፡፡

ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ስለኢትዮጵያ ታሪክ የተነገሩትና የተጻፉት ሁሉ የሚያስረዱት ኢትዮጵያ የተጻፈም ይሁን ያልተጻፈ ፖሊሲዋ ሰላም መሆኑን ነው፡፡

"ኢትዮጵያ ስሪቷ ሌላ ሀገር ወርራ ጦር የመመዘችበት አጋጣሚ የለም" ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ድንበር ገፍተው ሲመጡባት ግን ራሷን ለመከላከል

"ኢትዮጵያ የባሕር በር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ፋብሪካው

በግብዓት እጥረትና በማሽነሪዎች አቅም መድከም በሚፈለገው ልክ ማምረት አልቻለም

ገጽ 4

## ኮሚሽኑ የተሳታፊ ልየታ በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች አጀንዳ የመሰብሰብ ሥራ ሊጀምር ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ ተጠናቆ አጀንዳ የሚሰጡ ተወካዮች በተመረጡባቸው አካባቢዎች በቅርቡ አጀንዳ መሰብሰብ እንደሚጀምር አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ኮሚሽኑ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚያደርገውን የተሳታፊ ልየታ አጠናክሮ

ኮሚሽኑ የተሳታፊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ጥበቡ ታደሰ









አቶ ባንኬ ሱሜ

# በደቡብ ኦሞ ዞን በጎርፍ ምክንያት ከ79 ሺህ በላይ ዜጎች ተፈናቅለዋል

**- ማኅበረሰቡን በዘላቂነት ከጎርፍ ጥቃት ለመከላከል እየተሠራ ነው**

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ኦሞ ዞን በጎርፍ ምክንያት እስካሁን ከ79ሺህ በላይ ዜጎች ተፈናቅለው በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች እንደሚገኙ ተገለጸ፡፡ ማህበረሰቡን በዘላቂነት ከጎርፍ ጥቃት ለመከላል የሚያስችል መፍትሄ ተቀምጦ እየተሠራ እንዳለም ተጠቁሟል፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ባንኬ ሱሜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በድርቁ ተጎድቶ የነበረው የደቡብ ኦሞ ዞን አካባቢ የተሻላ የእንስሳት ርባታና የሰብል ምርት እየታየበት ቢሆንም በቅርቡ በተከተሰው ጎርፍ ምክንያት የግብርና ሥራዎች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ እስካሁንም 79ሺህ 828 የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተፈናቅለው በተለያዩ ማእከላት ውስጥ ይገኛሉ፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በዞኑ ስድስት የአርብቶ አደር ወረዳና አንድ ከተማ አስተዳደር ያሉ ሲሆን፤ ሥፍራው በቆላማ አካባቢዎች ሕይወታቸውን የሚመሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩበት ነው፡፡

አካባቢው በተደጋጋሚ የጎርፍ አደጋ ሲያጋጥመው ቆይቷል ያሉት ኃላፊው፤ በዞኑ ቀደም ሲልም ድርቅ ተከስቶ ማህበረሰቡን መጉዳቱንም ጠቁመዋል፡፡

ከድርቁ ጎን ለጎን በተለይም በማዕከላዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚዘንበው ዝናብ ከፍተኛ መጠን ያለው በመሆኑ፤ የኦሞ ወንዝ ከታችኛው ቱርካና ሀይቅ ጋር ሲገናኝ ወደ ኋላ የመመለስ ሁኔታ በማሳየቱ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ጎርፍ ተከስቷል ብለዋል፡፡

ጎርፉ ላለፉት አምስት ዓመታት ማህበረሰቡ ላይ ጉዳት ሲያደርስ መቆየቱን የገለጹት ኃላፊው፤ በዚህ ሳቢያ በሰብል ልማትና በእንስሳት ርባታ የግብርና ሥራዎች ላይ ትልቅ ተግዳሮትን እንደፈጠረ ገልጸዋል፡፡ ከግብርና ሥራው መስተጓጎል ባሻገር በርካቶችን ተፈናቃይ አድርጓል ነው ያሉት፡፡

ተፈናቅለው በተለያዩ ማዕከላት ውስጥ ያሉ ዜጎችም በመንግሥትና ረጂ ድርጅቶች አማካኝነት ሠብዓዊ ድጋፍ እየቀረበላቸው እንደሚገኝ ገልጸው፤ አሁን ላይ በጊዜያዊነት በድጋፍ መልክ ውሃ፣ ምግብ፣ የጤና ግብዓቶችና መጠለያ እየቀረበላቸው እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ሕዝቡ ከዓሳ ርባታ ጀምሮ አብዛኛውን የግብርና ሥራ የሚያከናውነው የኦሞ ወንዝን መሠረት አድርጎ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከአንድ ወር በፊት የተከሰተው የዘንድሮው ጎርፍ እስካሁን እንደቀጠለ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በዚህም የመስኖ፣ የትምህርት ቤት፣ የጤናና፣ የግብርና ተቋማት በጎርፉ ምክንያት ጉዳት እንደደረሰባቸውም ተናግረዋል፡፡

ጎርፍ በተደጋጋሚ የሚያጠቃውን የደቡብ ኦሞ አካባቢ ማህበረሰብ በዘላቂነት ከጎርፍ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል መፍትሄ ተቀምጦ እየተሠራ መሆኑንም አንስተው፤ ዳግም በማይፈናቀሉበት ሁኔታ ለእንስሳት ርባታና ሰብል ምርት ምቹ የሆነ ሁኔታን ለመፍጠር ከወረዳ እስከ ፌዴራል ድረስ በተዋቀረ አደረጃጀት እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ እንደተገባ አመላክተዋል፡፡

በእቅዱ መሠረት ውሃው የማይደርስባቸው አካባቢዎች ላይ ሕዝቡን የማስፈርና በቂ መሠረተ ልማት የማሟላት ሥራዎች እንደሚከናወኑም ኃላፊው አስታውቀዋል፡፡

የተያዘው እቅድ ተስፋ ሰጪና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ዘላቂ መፍትሄ የሚያመጣ መሆኑን ጠቅሰው፤ በእቅዱ ጎርፍ በማይደርስባቸው አካባቢዎች ላይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ጨምሮ መሠረተ ልማቶችን የማሟላት ሥራዎች እንደሚሠሩና ሀብት ተገኝቶ ወደ ተግባር ሲቀየር ማህበረሰቡ ችግር ውስጥ የማይገባበትን እድል እንደሚያገኝ ገልጸዋል፡፡

# “ኢትዮጵያ እየጠየቀች ያለችው በውሃ ሥርዓት እና በኃይል ምርቷ ላይ የተመሠረተ የሉዓላዊነት መብት ነው”

ፕሮፌሰር ላውረንስ ፍሪማን

የአፍሪካ ቀንድ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ተንታኝ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በዓባይ ጉዳይ እየጠየቀች ያለችው በውሃ ሥርዓት እና በኃይል ምርቷ ላይ የተመሠረተ የሉዓላዊነት መብት ነው ሲሉ በአፍሪካ ቀንድ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ተንታኝ ላውረንስ ፍሪማን ተናገሩ። ግብፃውያን የዓባይ ግድብን አንድምታ ከመረዳት ይልቅ ታሪካዊ መብት ላይ ያተኮረ ርዕዮተ ዓለም እንደሚከተሉም ተናግረዋል።

ላውረንስ ፍሪማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ ግድቡ በዓባይ ወንዝ ላይ የሚከናወን በመሆኑ ማንም ታሪካዊ መብት ሊኖረው አይችልም።


“እኔ እንደማስበው ግብጾች የሚፈልጉት ዋስትና ያለው የውሃ መጠን በሙሉ ወደ አስዋን ግድብ እንዲሄድ ነው፤ ነገር ግን በእኔ እይታ ኢትዮጵያውያንም ይህን ዋስትና ለግብጾች ሊሰጡ አይችሉም” ብለዋል።

ሁለቱ ሀገራት ወደ ትብብር መምጣት ይችላሉ ያሉት ፕሮፌሰር ላውረንስ ፍሪማን ሆኖም ግብጻውያን ለጊዜው ውድቅ እያደረጉት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

“የዓባይ ግድብ ለልማት የውሃ ሃይል የሚያመነጭ ግድብ ነው” ያሉት ፍሪማን ኤሌክትሪክ ኃይልንም ወደ ጅቡቲ፣ ኬንያ እና ሱዳን ለመላክ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

ይህ ግድብ የጨመረው አምስት ሺህ 150 ሜጋ ዋት ኃይል በዓባይ ወንዝ እና በነጭ አባይ ዙሪያ ያሉ ሀገራትን የማልማት አቅም እንዳለውም መታመን አለበት ሲሉ አክለዋል።

ፍሪማን ፤ ግብጾች ኢትዮጵያን እንደ አንድ ትልቅ የኢኮኖሚ ተፎካካሪ ማየት እንደማይፈልጉ ገልጸው፤ ይህም ሀገራት ለኢኮኖሚ ልማት አንድ ላይ ከመሆን ይልቅ ያለውን የአቅም ልዩነት የመመልከት የተሳሳተ መንገድ ነው ብለዋል።



“ኢትዮጵያ እየጠየቀች ያለችው በውሃ ሥርዓት እና በኃይል ምርቷ ላይ የሉዓላዊነት መብት ነው። አሁንም ከዚያ ብዙ የሚቀየር ነገር ያለ አይመስለኝም። ግብጾችም ያንን የሚቀይር የሚያደርጉት ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም። ግብጾች በየዓመቱ ይህን ያህል ውሃ ይገባል ብለው ጠብቀው ቆይተዋል፣ ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ማድረግ የማይቻል ነው” ሲሉ አብራርተዋል።

“በግድቡ የተጠራቀመው የዝናብ ውሃ መጠን 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ሲደርስ ውሃው ሙሉ ለሙሉ የሚለቀቅ ይሆናል፤ ይህ ደግሞ ለዓባይ ተፋሰስ ሀገሮች ልማት የሚውል የኤሌክትሪክ ኃይል ያመነጫል” ያሉት ፍሪማን የግብጻውያን እይታ ግን ከዚህ የተለየ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ፕሮፌሰር ላውረንስ እንዳሉት፤ የግብፅ የይገባኛል ጥያቄ አሳማኝ አይደለም፤ ምክንያቱም ግድቡ ተገንብቶ በመጠናቀቅ ላይ ነው።

ስምምነት ላይ ለመድረስ ግብፅ በየዓመቱ የምታነሳውን ለአስዋን ግድብ የተረጋገጠ የውሃ መጠን ማቅረብ የሚለውን ርዕሰ ጉዳይ መቀየር አለባት ያሉት ላውረንስ ፍሪማን፤ ይህ ሃሳብ የሞተ ጉዳይ ነው ብለዋል። ያንን ርዕሰ ጉዳይ ትቶም የግድቡን አቅም እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የሚሉ ሃሳቦች ላይ ማተኮር ይሻላል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

# ሀገራዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ ጠንካራ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትን ማቋቋም ያስፈልጋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የተማሪዎችን አቅም በማጎልበት ሀገራዊ ዕድገትን ለማረጋገጥ ጠንካራ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትን ማቋቋም እንደሚያስፈልግ የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አዘጋጅነት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ተቋማት ለሀገራዊ እድገት በሚኖራቸው ሚና ላይ ትናንት የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በመድረኩ የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ሃላፊ ቶላ በሪሶ (ዶ/ር)፤ ሀገራዊ እድገትን ለማረጋገጥ ጠንካራ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትን ማቋቋም የሚጠይቅበት ወቅት ላይ ነን ብለዋል፡፡

እንደ ሀገር ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊና ሳይንሳዊ እድገትን ለማስመዝገብ የሳይንሳዊ ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማት ሚና የጎላ ነው ያሉት ዶክተር ቶላ፤ ለተማሪዎች የሚሰጡ ትምህርቶችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር መደገፍ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በርካታ ተማሪዎችን በልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ላይ እያስተማረ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ለተማሪዎች የሳይንሳዊ ቴክኖሎጂ የምርምር ተቋማትን በማቋቋም ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

በልዩ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር በርካታ በመሆኑ የሳይንስ ተቋማትን በመክፈት ማስተማር ተገቢ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በተለይም ከውጭ ሀገራት ጋር የሚመጣጠኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትን በማቋቋም ማስተማር ውጤታማ እንደሚያደርግ አስረድተዋል።

ተማሪዎችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማት በማስተማር ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ ማድረግ



ቶላ በሪሶ (ዶ/ር)




ብርሃኑ ታፈሰ ቡልቻ (ዶ/ር)

እንደሚያስፈግ በመግለጽ፤ ለዚህም ጠንካራ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትን ማቋቋምና ውጤታማነታቸው ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል፡፡

የብራይት ጀነሬሽን የዳያስፖራ ፕሮግራም አስተባባሪ ብርሃኑ ታፈሰ ቡልቻ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የማህበረሰቡን ችግር የሚፈቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማትን በቅንጅት ማቋቋምና ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በዳያስፖራ ፕሮግራም በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች 35 የትምህርት ማዕከላትን በማቋቋም ተማሪዎች እየተማሩ እንደሚገኙ የገለጹት ዶክተር ብርሃኑ ፤ በቀጣይ የዳያስፖራ አባላትን በማሳተፍ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋም ለማቋቋም እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ ተማሪዎችን ተመራማሪና ችግር ፈቺ ሥራ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ እንዲሆኑ ለማስቻል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማት ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ በየተቋማቱ የፈጠራ ሥራዎችን በማውጣት ሀገራዊ ዕድገትን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

እንደሀገር በዕውቀትና ምርምር ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይገባል ያሉት ዶክተር ብርሃኑ፤ ጠንካራ የሳይንስ ተቋማትን በማቋቋም የቴክኖሎጂ ዕውቀቶችን ለትውልዱ ማሸጋገር ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

በውይይት መድረኩ ላይ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት ሃላፊ አብዱላዚዝ ዳውድ (ዶ/ር)፣ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሃላፊ ቶላ በሪሶ (ዶ/ር)፣ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶችና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚደረገው ሽግግር ፓርኮቹ ወሳኝ ድርሻ እየተወጡ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚደረገው ሽግግር ኢንዱስትሪ ፓርኮች ወሳኝ ድርሻ እየተወጡ መሆኑን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ። ኮርፖሬሽኑ የመጀመሪያውን የኢንቨስተሮችና የባለድርሻ አካላት የጋራ ፎረም ትናንትና አካሂዷል።

በወቅቱ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሽራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ እንደተናገሩት፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጥራት በጠበቀ መልኩ በማስፋፋት ኢትዮጵያ ከግብርና ዘፍር ወደ ኢንዱስትሪ የምታደርገውን ሽግግር ማፋጠን ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው፡፡

ለኢንቨስትመንትና ለኢንቨስተሮች የተመቸ ሁኔታ ለመፍጠርና ተግዳሮቶችን በመፍታት ትርፋማ እንዲሆኑ በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በቅርበት እየተሠራ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ በሌሎች ተቋማትም የሚሰጡ አገልግሎቶች በመኖራቸው እነዚህንም በአንድ ላይ በመገምገምና የሚታዩ ችግሮችን በየወቅቱ በመፍታት የኢንዱስትሪ ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ገንብቶ እያስተዳድራቸው በሚገኙ 13 ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ መገኘቱንም አስታውሰዋል።

በተጨማሪም ከ750 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመቱ ተኪ ምርቶች በሀገር ውስጥ ኢንዲመረቱ ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የውጭ ምንዛሬ ወጪ ጫናን ለመቀነስ ጥረት መደረጉን አስረድተዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፈጠሩን አስታውቀው፤ የሥራ ዕድል ፈጠራው በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቁመዋል።

ባለፈው አንድ ዓመት ኮርፖሬሽኑ የተለያዩ የአሠራር ማሻሻያዎች ያደረገ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ ባለሀብቶች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ከፍተኛ የውጪ መዋለ ነዋይ ፍሰት ያላቸውን ሀገራት በመለየት ቀድሞ በየሀገራቱ የማግባባት ሥራ መሥራት፣ ሠራተኛ ማትጊያ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን አመላክተዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ መንግሥት ሀገሪቱን ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ የተለያዩ የፖሊሲ ማሻሻያ አድርጓል። የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራትን ለመጠገን በፋይናንስ፣ በኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በቱሪዝምና በሌሎች ዘርፎች ላይ ጠንካራ ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከተመሠረተ ጀምሮ ይህንኑ ሀገራዊ እውነታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሀገራዊ ኢንዱስትሪ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል።

ኮርፖሬሽኑ የተሰጠውን ተልዕኮ ብቻውን ማሳካት የማይችል በመሆኑ ሀገራዊ የኢንዱስትሪ አቅምን በማዳበር የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እንዲሁም ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ባለድርሻ አካላት በጋራ እንዲሠሩ አቶ አክሊሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በመድረኩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ቦርድ ሰብሳቢና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ገብረመስቀል ጫላ፣ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ፣ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አሰግድ ጌታቸው እንዲሁም የተለያዩ ኢንቨስተሮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።



**አቶ አክሊሉ ታደሰ**



# በኦሮሚያ አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር የመኸር ምርት ተሰብስቧል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- 2015/16 የመኸር እርሻ ሥራ አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር የደረሰ የመኸር የሰብል ምርት መሰብሰቡን የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ የህብረተሰቡ ንቃተህሊና ላይ በበቂ ሁኔታ በመሠራቱ ምክንያት የዘንድሮው የመኸር ወቅት ምርት ስብሰባ ሂደት ከዚህ ቀደም ከነበረው በፈጠነ መልኩ መከናወኑም ተመላክቷል።

በቢሮው ሰብል ልማት ዳይሬክተር አቶ ሙስጠፋ ሁሴን ለኢትዮጲያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ 9 ነጥብ 48 ሚሊዮን ሄክታር ሰብል የተዘራ ሲሆን ከዚሁ ውስጥም 6 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሄክታር ሰብል ለምርት ስብሰባ ደርሶ አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር የመኸር ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

አቶ ሙስጠፋ እንዳመላከቱት፤ በክልሉ በተያዘው የመኸር ምርት ካሉት 21 ዞኖች በ16 ዞኖች ላይ የሰብል ስብሰባው የተከናወነ ሲሆን፤ ከ16ቱ ዞኖችም አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር የመኸር ምርት መሰብሰብ ተችሏል፡፡

እንደ አቶ ሙስጠፋ ገለጻ፤ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በሰብል ስብሰባው ላይ ችግር ጋርጦ የነበረ ሲሆን የከፋ አደጋ ሳይፈፀም ማሳለፍ ተችሏል፤ የደረሱትን እንዴት መሰብሰብ ይቻላል የሚለውን ከትምህርት ሚኒስቴርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተሠርቷል።

እንደ አቶ ሙስጠፋ ንግግር፤ ሕዝቡን በማስተባበር ሌሊትም ጭምር በአርሲና ምዕራብ አርሲ ላይ የደረሰውን ምርት የመሰብሰብ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡

ባለፉት ቀናትም በአርሲ ቆላና ወይናደጋ አካባቢዎች እየተሰበሰበ ወደ ማለቁ መሆኑን ያመላከቱት አቶ ሙስጠፋ፤ ደጋማ ክፍሎች ላይ እህሎች ያልደረሱ ሲሆን ሰብሎች ለመሰብሰብ በሚደርሱበት ወቅት የሚሰበሰቡ ይሆናል ብለዋል፡፡

የህብረተሰቡ ንቃተህሊና ላይ በበቂ ሁኔታ በመሠራቱ ምክንያት የዘንድሮው የመኸር ወቅት ምርት ስብሰባ ሂደት ከዚህ ቀደም ከነበረውና ከአምና ተመሳሳይ ወቅት አንፃር በፈጠነ መልኩ መከወኑን የጠቀሱት አቶ ሙስጠፋ፤ ሕዝቡን ማስተማርና በህብረት እንዲሠራ ማድረግ መቻሉ ስላለው መልካም ጎን አመላክተዋል።

አቶ ሙስጠፋ በሰጡት ማብራሪያ፤ አሁንም ቀሪ የሰብል ስብሰባ ሥራዎች ስለሚቀጥሉ ህብረተሰቡ እስካሁን ያሳየውን የትብብር መንፈስ በመቀጠል በንቃት ሊሳተፍ ይገባል፡፡

# በአፈር ማዳበሪያ

## የግዥ ሥርዓት ማሻሻያ በመደረጉ ከ20 ቢሊዮን ብር በላይ መቆጠብ ተችሏል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ እስካሁን ከተገዛው ማዳበሪያ በተደረገው የግዢ ሥርዓት ማሻሻያ 20 ቢሊዮን ብር ወጪ መቆጠብ እንደተቻለ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ የግብርና ሚኒስቴርን የ2016 በጀት ዓመት የአምስት ወራት አፈጻጸም አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ፣ እስካሁን ከተገዛው ማዳበሪያ በተደረገው የግዢ ሥርዓት ማሻሻያ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር 20 ነጥብ 01 ቢሊዮን ብር ወጪ መቆጠብ ተችሏል።

ባለፈው ዓመት ማዳበሪያን በወቅቱ ከማቅረብ አንጻር ችግሮች እንደነበሩ የጠቀሱት ዶክተር ግርማ፤ የነበሩትን ክፍተቶች በመለየትና የተንዛዛ አሠራሮችን በማስተካከል የግዥ ሥርዓቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲቀየር እንደተደረገ አብራርተዋል። ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ በምታገኝበት መንገድ ከአምራች ፋብሪካዎች ቀጥታ የማዳበሪያ ግዥ እንድትፈጽም ተደርጓል ሲሉም ገልጸዋል።

የግዥ ሥርዓት መቀየሩ፣ የቦርድ ቴክኒክ ኮሚቴ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ መደረጉና የማዳበሪያ ስርጭትን መከታተል በሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱ እንዲሁም የተናበበ የሎጀስቲክ እቅድ ተዘጋጅቶ መሠራቱ ለውጤቱ ተጠቃሽ ምክንያት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የማዳበሪያ ዋጋ በወቅቶች ይለዋወጣል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ቀደም ጭማሪ በሚያሳይበት ወቅት ማዳበሪያ ውድ በሆነ ዋጋ ይገዛ እንደነበር አስታውሰዋል። በማሻሻያ ሥራው ለማዳበሪያ የሚመደበው የውጭ ምንዛሬ በወቅቱ እንዲመደብና የሚገዛው አካልም በተሻለ ዋጋ የሚያገኝበትን ጊዜና ወቅት ለይቶ እንዲገዛ መደረጉን ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የተገዛው ማዳበሪያ በቂ ሲሆን፤ የአርሶ አደሩን የመግዛት አቅም በማገናዘብ በዘንድሮው ዓመት መንግሥት 16 ቢሊዮን ብር ድጎማ አድርጓል። የማዳበሪያ ግዥና ማጓጓዝ ሂደቱን ቀድሞ በመጀመር በበጀት ዓመቱ የተሻለ እንቅስቃሴ እንዲኖር ተደርጓል።

ባለፈው ዓመት ለማዳበሪያ ግዥ አንድ ቢሊዮን 59 ሚሊዮን ዶላር የተመደበ ሲሆን፤ በዚህም 13 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል መገዛቱን ሚኒስትሩ ጠቁመዋል። በዘንድሮው ዓመት 930 ሚሊዮን ዶላር ተመድቦ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመግዛት መታቀዱን ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ 18 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ መፈጸሙን አስታውቀዋል።

ለመግዛት የታሰበው ማዳበሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ በመጠን ትልቁ መሆኑን ጠቁመው፤ ከሚገዛው ማዳበሪያ 25 በመቶ ለመስኖ፣ 20 በመቶ ለበልግ እንዲሁም 55 በመቶ ለመኸር ወቅት እንደሚውል ነው የተናገሩት።

በአሁኑ ወቅት ለመስኖና ለበለግ የሚያስፈልገው ማዳበሪያ ሙሉ ለሙሉ መገዛቱንና የመጫን ሂደቱ እየተካሄደ እንዳለም አመልክተዋል። ከተገዛው 15 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ ሦስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ጅቡቲ መድረሱንና ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ያህል ወደ ክልሎች መጓጓዙንም ጠቅሰዋል።

ዜና

## ፋብሪካው በግብዓት እጥረትና በማሽነሪዎች አቅም መድከም በሚፈለገው ልክ ማምረት አልቻለም

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ወረቀትና ፐልፐል አክሲዮን ማህበር በፐልፐልና በሚካል ግብዓት እጥረት እና በማሽነሪዎች አቅም መድከም ምክንያት በሚጠበቀው ልክ እያመረተ አለመሆኑ ተገለጸ፡፡ ለጋዜጣ የሚሆኑ ወረቀቶችን ማምረት ካቆመም ከ20 ዓታት በላይ መቆጠራቸውን አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ወረቀትና ፐልፐል አክሲዮን ማህበር ምክትል ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን መንገሻ እንደገለጹት፤ ፋብሪካው ከ60 ዓመት በፊት ሲቋቋም በቀን 50 ሺህ ቶን የወረቀት ምርት እንዲያመርት ታስቦ ሲሆን በዋናነትም ካርቶኖችን፣ ለጋዜጣ የሚሆኑ የተለያዩ ስስ የወረቀት ውጤቶችን፣ ለማሸጊያና ለእስቴሽነሪ የሚሆን ወረቀቶችን እንዲያመርት ነበር፡፡

እንደ አቶ ጥላሁን ገለጻ፤ ፋብሪካው ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ እስከ 1990ዎቹ አካባቢ ድረስ ለጋዜጣ የሚሆን ወረቀት አምርቶ ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ያቀርብ ነበር፡፡ ይሁንና ከ1990ዎቹ ጀምሮ የማሽነሪዎች አቅም እየተዳከሙ መምጣት፣ የፐልፐልና የኬሚካል ግብዓቶችን ማግኘት አለመቻል ለጋዜጣ የሚሆኑ ስስ ወረቀቶችን ማምረት እንዳይችል አድርጎታል፡፡

ፋብሪካው በአሁኑ ጊዜ ለማሸጊያ ፣ ለመጽሐፍት፣ ለመጽሐፍት ሽፋን፣ ለደብተር፣ ለክላሰር ፣ ለደረሰኝና ለሆስፒታሎች ካርድ የሚሆኑ ወፍራም ወረቀቶችን በማምረት ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ካደረገ ለጋዜጣ የሚሆኑና ለተለያዩ የህትመት ውጤቶች የሚውሉ ወረቀቶችን የማምረት አቅም እንዳለው ግን ተናግረዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለጋዜጣ ወረቀት ግዥ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት እንደሚያስችል ተናግረዋል፡፡

ፋብሪካው ከፍተኛ የውሃ ፓምፕና የመለዋወጫ እቃ ችግር እንዳለበት የገለጹት አቶ ጥላሁን፤ መለዋወጫ እቃ በውጭ ምንዛሬ የሚመጣ በመሆኑ ችግሩ እንደቀጠለ ነው ብለዋል፡፡

እንዲሁም የማጠንጠኛ ማሽን ችግር ለሥራችን እክል እየፈጠረ ነው ያሉት አቶ ጥላሁን፤ ዘመኑ የደረሰበትን የካርቶን ማሽን ለማግኘት አለመቻል ከገበያ ውጭ እየሆንን እንድንመጣ አድርጎናል ብለዋል፡፡

መንግሥት ትኩረት ሰጥቶት ፋብሪካው ያሉበትን ችግሮች መቅረፍ ከቻለ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ወረቀቶችን የማምረት አቅሙ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚሻሻልም ገልጸዋል፡፡

እንደ ምክትል ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ይህ የወረቀት ፋብሪካ በቅርብ ከተመሠረቱት ፋብሪካዎች በፊት ብቸኛ ነበር፡፡ በመጽሐፍትና በተለያዩ የህትመት ሥራዎች ላይ ትልቅ ሚና እያደረገ በመሆኑ በሀገሪቱ በትምህርት ዘርፍ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በአሁኑ ወቅት በዓመት 15 ሺህ ቶን የወረቀት ምርቶችን ማምረት ይችላል፡፡ ይሁንና በመለዋወጫ እቃ እጥረትና በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት ከአቅሙ ባነሰ እያመረተ ይገኛል፡፡

ቀደም ሲል ለወረቀት መስሪያነት የሚውሉ ግብዓቶችን የሚያስገባው ከውጭ መሆኑን የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ በአሁኑ ጊዜ 95 በመቶ ግብዓቱን የተለያዩ ተረፈ ምርቶችን በመጠቀም ወደ ወረቀት በመቀየር ላይ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡ ይህም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን እያስቀረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## ቀጣዩ እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ቀናት የሚኖረው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሜቴዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መረጃ መሠረት፤ በሰሜን ምስራቅ፤ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ሊኖር ይችላል።

ይህም ሁኔታ ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ስለሆነ፤ የሚኖረው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ብሏል።

በመረጃው መሠረት በቀጣይ ቀናት ወደ ሀገራችን በሚገባው ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይስተዋላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን "የሰሜን ምሥራቅ" የምሥራቅ" የመካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻራዊ ጥንካሬ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። በአንጻሩ በቀጣይ ቀናት ያለው የአየር ሁኔታ የሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት ለማከናወን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በተለይም በምዕራብ እና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ፤ ደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራል።

ይህም ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚያከናውኑት የእንስሳት ልማትም ሆነ ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይጠበቃል። የእርጥበት ሁኔታው በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል።

በሚቀጥሉት ቀናት ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናት ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅና በደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ይኖረዋል።

በሌላ በኩል በሰሜን ህንድ ውቅያኖስ ላይ ከሚፈጠረው ዝቅተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን ከሚገባው እርጥበት አዘል አየር ጋር በተያያዘ ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል። ስለሆነም በሰሜን ምስራቅ፤ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛውና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።

በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በምዕራብ እና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ፤ ደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## ኮሚሽኑ የተሳታፊ ልየታ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ቀጥሏል፡፡ የምክክር ሂደቱን ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ለማሸጋገር የተሳታፊ ልየታ በተጠናቀቀባቸው ክልሎችም የአጀንዳ ሃሳቦችን ለመሰብሰብ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡

ተሳታፊ ልየታ ባልተጠናቀቀባቸውና ባልተጀመረባቸው ክልሎች ሥራው እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ ከዚህ ጎን ለጎን ተሳታፊዎች ተለይተው በተጠናቀቁባቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአጀንዳ ሃሳቦችን የማሰባሰብ ሂደቱ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ 700 ወረዳዎች የተሳታፊ ልየታ በመከናወን ላይ መሆኑን አመልክተው፤ 327 ወረዳዎች የአጀንዳ ሃሳብ የሚሰጡ ተወካዮችን መወከላቸውን ገልጸዋል፡፡

ከአማራ እና ትግራይ ክልሎች በስተቀር በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሁለቱ ክልሎች ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ ለማከናወን የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል።

ኮሚሽኑ ዲያስፖራው የአጀንዳ ሃሳቦችን እንዲያዋጡ እንዲሁም በምክክሩ ላይ በመሳተፍ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ለማድረግ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

የአጀንዳ ማሳባሰቡ የሚካሄደው በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር፣ በፌዴራልና በዲያስፖራ ደረጃ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ የአጀንዳ ሃሳቦችን የማሰባሰቢያ መድረኮች በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው ምክክር የሚሳተፉ ተወካዮች የሚወከልባቸው ናቸው፤ በዚህ ምክንያት ሥራው በክፍተኛ ጥንቃቄ የተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የአጀንዳ ሃሳቦችን ለመስጠት የተወከሉ የህብረሰተሰብ ክፍሎች ከወከላቸው ማህበረሰብ ሃሳቦችን በማሰባሰብ ዝግጅት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የአጀንዳ ሃሳብ አለን የሚሉ ተቋማትና ግለሰቦችም ሃሳቦቻቸውን ለኮሚሽኑ በቀጥታ በማቅረብ ወይም በኢንተርኔት፣ በስልክ፣ በፖስታ እና መሰል መንገዶች ማቅረብ እንደሚችሉ ገልጸው፤ ኮሚሽኑ እስካሁንም የአጀንዳ ሃሳቦች ከተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች እየደረሱት ነው፤ በተጨማሪም አጀንዳዎች ምን መሆን አለባቸው በሚለው ላይ ጥናት ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ነው ብለዋል።

ኮሚሽኑ በምክክሩ አስፈላጊነት ላይ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን መቆየቱን አስታውሰው፤ መገናኛ ብዙሃንም ግንዛቤ በመፍጠርና በተሳታፊ ልየታ ላይ ትኩረት ሰጥተው በመሥራት የድርሻቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ በቀጣይነትም አጀንዳ ሃሳቦች በማሰባሰብ ሂደቱም ትኩረት በመስጠት ከኮሚሽኑ ጋር በቅርበት እንዲሠሩ ጠይቀዋል፡፡

በተለይ በየአካባቢው የሚገኙ የማህበረሰብ መገናኛ አማራጮች የምክክሩ አስፈላጊነት ላይ የሚኖር የጋራ ግንዛቤ ለምክክሩ መሳካት ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ተገንዝበው በጉዳዩ ላይ በትኩረት እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## የኮይሻ የኃይል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማመንጨት ሥራችንን እና ጥረታችንን አቻ የሌለው ያደርገዋል ሲሉም አስፍረዋል፡፡

አንድ ሺህ 800 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ይዞ ከታላቁ ሕዳሴ ግድብ በመቀጠል በኢትዮጵያ ሁለተኛው ግዙፍ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ሆኖ በመገንባት ላይ ይገኛል፤ አፈፃፀሙም 62 በመቶ ላይ ደርሷል ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

በቅርብ ርቀት በጨበራ ጨርጨራ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኘውን የጨበራ የዝሆን ዳና ሎጅን በምንመርቅበት በአሁኑ ወቅት የኮይሻ ግድብ ለአካባቢው የቱሪዝም ዕድል ተጨማሪ አስተዋፅኦ ያደርጋልም ብለዋል።

"የተፈጥሮ ብልፅግና ከፈጣሪ የሚሰጥ ሀብት ነው። ኢትዮጵያ በዚህ የታደለች ናት። በተራሮች፣ በሸለቆዎች፣ በወንዞችና በሐይቆች፣ የተሞላች ሀገር ናት። ይህንን ውበት ሰዎችም አይተው ይረኩ ዘንድ የኮይሻ ፕሮጀክት እንዲህ ውብ ሆኖ ተሰናድቶልናል" ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የኮይሻ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ 201 ሜትር ቁመትና 1012 ሜትር ርዝመት የሚኖረው ሲሆን በዓመት በአማካይ ስድስት ሺህ 460 ጊጋ ዋት ሰዓት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም አለው። በዓመት እስከ አንድ ሚሊዮን ቶን የካርበን ልቀትም የመቆጣጠር አቅም እንዳለው የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

ፕሮጀክቱ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ በ560 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል።

## "ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት የምታደርገው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከገባችባቸው ጦርነቶች ውጭ ጉልበት አለኝ ብላ ጎረቤቶቿ ላይ ኃይል የተጠቀመችበት ጊዜ አለመኖሩን ገልጸዋል።

እንደተመራማሪው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ወረራ በመፈጸም በኃይል የወደብ ባለቤት ልትሆን ነው በሚል አንዳንድ ኃይሎች የሚነዙት አሉባልታ የኢትዮጵያ ጥቅም ምን ላይ እንደሆነ ያልተገነዘቡ ናቸው።

"ሃሳባችን ወደ ልማት ነው፤ ጦር የነካው ነገር ለልማት ቅመም ሊሆን አይችልም" ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ በጦርነት ለአንድ ወቅት እንጂ ለዘለቄታው አሸናፊ የሚሆን ወገን አይኖርም። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ም ያተኮሩት በሰላማዊ መንገድ የባህር በር ማግኘት የሚቻልበት መንገድ ላይ ነው ብለዋል።

አክለውም፤ ኢትዮጵያ ያቀረበችው በጋራ እንጠቀም የሚል ሃሳብ በጎ ነገር መሆኑን ጠቁመው፤ "ጥያቄውን በአወንታዊነት የማይቀበሉ ጎረቤት ሀገራት ካሉ ለሕዝባቸው የማያስቡ ናቸው" በማለት አንተ ቆርቁዝ ፤እኔ ልጠቀም የሚል አስተሳሰብ ስህተት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵያን ሰላማዊ ጥያቄ እንደሚደግፍ ሲያስረዱም፤ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዘላቂ ልማት ግቦች መካከል 16ኛው ትኩረቱን ያደረገው የባህር በር በሌላቸው ሀገሮች ላይ መሆኑን በመጠቆም፤ የባህር በር ከሌላቸው 44 ሀገሮች አብዛኞቹ ዝቅተኛ የድህነት ወለል ውስጥ የሚገኙ ናቸው ብለዋል። ይህ አሳሳቢ ስለሆነ የባህር በር ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት ሊታገዝ የሚችል ከሆነ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ርብርብ እንደሚያደርግበት እርግጠና ነኝ ብለዋል።

አያይዘውም፤ የባህር በር ከሌላቸው ሌሎች ሀገራት አንጻር ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት የባህር በር ባለቤት የነበረች ሀገር በመሆኗ በጣም የተለየ ሁኔታ ውስጥ መግባቷን አመልክተው፤ ያለፉትን 32 ዓመታት ወደብ አልባ በመሆኗ ብዙ ሀገር ወዳዶች አዝነውና ተቆርቁረው የተለያዩ ምክረ ሃሳቦችን ሲያቀርቡ ቢቆዩም በወቅቱ የነበረው መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት ባለመስጠቱ ምንም ማድረግ አለመቻሉን ገልጸዋል።

"አሁንም ቢሆን ከባህር በቅርብ ርቀት ላይ ነው የምንገኘው" ያሉት ተመራማሪው፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች በርትተው ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ጦርነት ጋባዥ እንዳልሆነች በመግለጽ የባህር በር ጥያቄዋ ሰላማዊና የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ መሆኑን ማስረዳት አለባቸው ሲሉ መክረዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# ወቅታዊ

# “በበጋ መስኖ 117 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ይጠበቃል”

**የኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስትር**
**ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)**



ፎቶ ፡- በረሁን ታደሰ

አስቴር ኤልያስ

ባለፉት አምስት ዓመታት በዋና ዋና የግብርና ዘርፎች ላይ የተሰሩ ሥራዎች ሰፋ ያሉ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና በዚሁ በግብርናው ዘርፍ በተለይ በበጋ መስኖ ስንዴ ስኬታማ የተሆነውን ያህል በአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ደግሞ ፈተና እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ፈተና በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ተቀርፏል? የሚለውን ጨምሮ ባለፉት አምስት ወራት የግብርና ዘርፉ አፈጻጸሙ ምን ይመስላል? በሚለው ዙሪያ የዛሬው የዘመን እንግዳችን የሆኑት የኢፌዴሪ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) የሰጡትን ሰፊ ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል። መልካም ንባብ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በግብርናው ዘርፍ ባለፉት አምስት ዓመታት በዋና ዋና የግብርና ዘርፎች ላይ የተሰሩት ሥራዎች ምን ይመስላሉ?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** በአስር ዓመቱ መሪ እቅዳችን ላይ እየተሰራ ያለው የግብርና አማካይ ዓመታዊ ምርት በስድስት በመቶ እንዲያድግ ነው፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታት ያሉትን አማካይ ውጤቶችን ስንመለስድ ስድስት በመቶ ያክሉን ዓመታዊ የምርት እድገት ግብርና አስመዝግቧል፡፡ ይህም በአፍሪካ የግብርና እድገት ፕሮግራም ከተቀመጠው ግብ ጋር ሲታይ ተመሳሳይ ነው ማለት ያስችላል፡፡ ግብርናው እንዲያድግ የሚጠበቀው በስድስት በመቶ ነው፡፡

ለዚህኛው ስኬት ባለፉት ዓመታትም ሆነ ባለፉት አምስት ወራት በዋና ዋና የግብርና ዘርፎች የተሰሩ ስራዎች ሲታዩ ባለፈው አምስት ወራት እንደሚታወቀው ትልቁ ሥራ የመኸር ወቅት ስራችን ነው፡፡ መኸር ላይ በባለፈው በጀት ዓመት በተለይ በአራተኛው ሩብ ዓመት ማሳ የማዘጋጀትና የመዝራት ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም ምርቱ እንክብካቤ ተደርጎለት ወደመሰብሰቡ የሚመጣው በዚህኛው ዓመት ከመሆኑ አንጻር መኸር ላይ 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በተለይ በአነስተኛ አርሶ አደር ማሳ ላይ የተዘራ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ወደ ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሔክታር በኩታ ገጠም እርሻ የተዘራ ነው፡፡

በመኸር የኩታ ገጠም እርሻን የምንሰራው ወደ 50 በመቶ የሚሆነው በአነስተኛ ማሳ ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ግብርናችን በኩታ ገጠም እየተሰራ መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን፣ በጣም ትልቅ እድገት ነው፡፡ የኩታ ገጠም እርሻን ስንወስድ አርሶ አደሩ አንድ ላይ ተደራጅቶ ቴክኖሎጂውን ከመጠቀም አንጻርና እርስ በእርስ ከመማማር አንጻር ጥቅም ያለው ነው፡፡ እርሻውን ሜካናይዜሽን ከማድረግና አርሶ አደሩ የቴክኖሎጂ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር በጣም ትልቅ ለውጥ የመጣበት ነው ብለን መውሰድ እንችላለን።

ወደ አራት ሚሊዮን ሔክታር የሚደርስ መሬት በሜካናይዜሽን የታረሰ ነው፡፡ ይህን ከባለፈው ዓመት ጋር ስናነጻጽረው ወደ አንድ ሚሊዮን ሔክታር ብልጫ ያለው ነው።

የተዘራውን ዘር የመንከባከብ፣ ጸረ ተባይ ኬሚካሎች የመርጨት ሥራዎች በስፋት ሲሰራባቸው ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ባለፈው ዓመት የአንበጣና የተምች ክስተቶች ነበሩ፡፡ ምርቱ ሲደርስ ደግሞ የግሪሳ ወፍ ችግር ነበር፡፡ እነዚህን ችግሮች በጣም በተቀናጀ ሁኔታ ሰፊ ጉዳት ሳያደርሱ የመከላከል ሥራ ተሰርቷል፡፡

ከ17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ላይ የተዘራውን ምርት የመሰብሰብ ሒደት ላይ እንገኛለን፡፡ በአሁኑ ወቅት ተሰብስቦ የተጠቃለለም ባይሆን እስካሁን ወደ 11 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሔክታር አካባቢ ምርት የመሰብሰብ ሒደት ተካሂዷል፡፡

ምርት የደረሰባቸው ቦታዎች ብለን ግምት የወሰድነው 12 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሔክታር አካባቢ ላይ ነው። ስለዚህ አሁን ያለው 11 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በጣም በበቂ ሁኔታ የደረሱ ምርቶች የተሰበሰቡበትን ሁኔታ እንዳለ የሚያሳይ ነው። በተለይ ባለፉት ወራት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ከመኖሩ አንጻር የአርሶ አደሩን ምርት የማሰባሰብ ሌሎቹም የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማነቃነቅ ምርት እንዲሰበሰብ ጥረት ሲደረግ ነበር።

ምርት ሲሰበሰብ በሁለት አኳኋን ነው፡፡ አንዱ በባህላዊ መንገድ ሲሆን፣ ሁለተኛው መካናይዝድ በሆነ መንገድ ነው። በተለይ በባህላዊ መንገድ የሚሰበሰበው አርሶ አደሩ ሰብስቦ፣ ወቅቶና አስግብቶ እስኪረጋጋ ድረስ የተወሰነ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፡፡ ነገር ግን በሜካናይዜሽን የሚሰበሰበው ጊዜ ቆጣቢ ሲሆን፣ እስካሁን የተወቃውም ወደ 140 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ነው፡፡ ይህ ማለት አብዛኛው ምርት የሚሰበሰበው በባህላዊ በመሆኑ የታጨደው ሁሉ ወደምርት ተቀይሯል ማለት አይደለም። በአጠቃላይ ከመኸር ምርት የምንጠብቀው ወደ 513 ሚሊዮን ኩንታል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ባለፈው በአምስት ወራት ውስጥ በስፋት ከተጀመረው ሥራ አንዱ የበጋ መስኖ ነውና በዚህስ ዙሪያ ምን እየተሰራ ነው?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** ሁለተኛው የማነሳው ነጥብ የበጋ መስኖ ነው፡፡ ባለፈው በአምስት ወራት ውስጥ በስፋት ከጀመርናቸው ስራዎች አንዱ የበጋ መስኖ ሥራ ነው፡፡ ይህ በሁለት የሚከፈል ሥራ ነው፡፡ አንዱ የበጋ የመስኖ ስንዴ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የአትክልትና ፍራፍሬ ሥራ ነው፡፡

የበጋ መስኖን በተመለከተ ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሔክታር በበጋ መስኖ ስንዴ ተሸፍኗል፡፡ ዘንድሮ ደግሞ ሶስት ሚሊዮን ሔክታር ስንዴ ለመሸፈን አቅደናል፡፡ ከዚህ የምንጠብቀው ወደ 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ነው፡፡

አሁን እስከዚህ ሳምንት ድረስ ያለን አጠቃላይ እድገት ሲታይ ወደ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ታርሶ ዝግጁ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ደግሞ ወደ አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሔክታር በዘር ተሸፍኗል፡፡

ይህ አምና የበጋ መስኖን ከሰራንበት ፍጥነት አንጻር ሲታይ በጣም የፈጠነ ነው፡፡ እንደሚታወቀው መሬቱ ወደመስኖ የሚሸጋገረው የቀደመው ምርት ታጭዶ ሲሰበሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሔክታር አርሰን ከማዘጋጀት አንጻር የተኬደው ርቀት ሶስት ሚሊዮን ሔክታር ለመሸፈን ብዙ የሚቸግረን እንዳልሆነ ነው፡፡

ብዙ ጊዜ የስንዴ ጉዳይ ሲነሳ አብሮ የሚነሳው ነገር ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ስራዎች በመዘንጋት የሚሰራ ይሆን የሚል ስጋት ነው፡፡ ባለፈው አምስት ወራት 652 ሺ ሔክታር ለመሸፈን አቅደን ወደ 460 መሸፈን ችለናል። ይህም ማለት የእቅዱን 80 በመቶ አካባቢ እንደማለት ነው፡፡ ይህ ማለት አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ስራስር ሌላውን ጨምሮ የሚሰራ ነው፡፡ ስለዚህ የስንዴው ሥራ በመስኖ እንደሚሰራ ሁሉ በበጋ ወቅት የአትክልትና ፍራፍሬ ስራዎችንም በዚሁ ልክ እየሰራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚሁ በግብርናው ውስጥ ከሚካተተው ዘርፍ አንደኛ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ነውና ከዚህ አንጻር እየተከናወነ ያለ ተግባር ምንድን ነው?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** ከሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ ምርታችን ባለፈ ሁለተኛው ትልቁ የግብርናው ዘርፍ የእንስሳትና የዓሳ ሀብት ዘርፋችን ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ባለፈው ዓመት ያስጀመሩት የሌማት ትሩፋት ሥራ ይገኛል፡፡ የሌማት ትሩፋቱ ሥራ በተለይ ወተት፣ ማር፣ ዶሮና የእንቁላል ምርቶችን በስፋትና በብዛት ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የተሰራ ሥራ ነው፡፡ ከዚህ ምርት አንጻር ቁጥሮቹ እንደሚያመለክቱት በወተትም በማርም እንዲሁም በዶሮና እንቁላል ምርቶች ባለፉት አምስት ወራት ያቀድናቸው እቅዶች ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል መልኩ ስኬታማ ሆነዋል፡፡

ይህን ለማሳካት እንደ አማላካችነት አንዱ ከምንወስዳቸው ማሳያዎች በሚቀርቡ ግብዓቶች ላይ የሚያደርገው ክትትል በጣም ሰፊ መሆኑ ነው፡፡ ግብዓት ካልቀረበ ውጤት አይኖርም። ከዚህ ውስጥ አንዱና ዋንኛው ግብዓት በተለይ በዶሮ ልማት ላይ የአንድ ቀን ጫጩት ዶሮን ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ባለፈው ዓመት፣ ዓመቱን ሙሉ 42 ሚሊዮን ያህል ሰርተናል፡፡ ዘንድሮ የዓመት እቅዳችን 62 ሚሊዮን ነው፤ ይህ ከአምናው ጋር ሲተያይ በ20 ሚሊዮን ያደገ ነው፡፡

ባለፈው አምስት ወራት ለመስራት ያቀድነው 25 ሚሊዮን ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ አሁን 29 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሰርተናል፡፡ ይህ በጣም ትልቅ እድገት ነው። ከአምናው እቅድ ጋር ስናስተያይ ግማሽ ዓመት ላይ የባለፈው እቅዳችንን ልናሳካ የምንችልበት ሁኔታ እንዳለ ነው፡፡ ሁለተኛው አመላካች በተለይ ወተቱ ልማት ላይ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶና ለአርብቶ አደሩ ከማቅረብ አንጻር በጣም ትልቅ ተግዳሮት ነበር፡፡ በተለይ በአካባቢው ያሉ መሰረት ልማቶች አነስተኛ ከመሆን አንጻር ባለፈው ዓመቱን ሙሉ ማቅረብ የተቻለው አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ነው፡፡ ዘንድሮ ወደ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ለማቅረብ አቅደናል፡፡ ባለፈው አምስት ወራት ውስጥ 920 ሺ ወይም ደግሞ ለአንድ ሚሊዮን የቀረበ ለማቅረብ ችለናል፡፡ ይህ ከእቅዳችን ጋር ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ዘመናዊ ቀፎ ከማቅረብ አንጻር ከማሩ ጋር ተያይዞ ወደ 250 ሺ አካባቢ ለማቅረብ ታስቦ ወደ 315 ሺ ማቅረብ ችለናል። ለዚህ የግብዓት አቅርቦት ለውጥ በአምስት ወራት የተወሰደ እርምጃ ለመግለጽ ያህል ለመጀመሪያ ጊዜ 30 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ እንዲፈቀድ አድርገን በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ባለሀብቶች ማን ምን ያደርጋል? የሚለው እቅድ ለይተንና አውጥተን በዚህ መሰረት እንዲያስገቡ ማድረጋችን ተጠቃሽ ነው፡፡

በዚህ አምስት ወር በእንስሳት ዘርፉ ወደ 84 ሚሊዮን እንስሳትን ለመከተብ ታቅዶ ወደ 71 ሚሊዮን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ትልቅ ትኩረት ሲሰጠው የተገባው የተፈጥሮ ሀብት ሥራ ምን ያህል ውጤት እያስገኘ ነው?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** ሶስተኛው በግብርናችን ላይ ያለው ዘርፍ የተፈጥሮ ሀብት ዘርፉ ሲሆን፣ በዚህ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዙሪያ አንደኛው ከአረንጓዴ አሻራ ጋር ተያይዞ የተሰራ ሥራ ነው፤ ሁለተኛ ደግሞ መሬትን ከመመዝገብና ሰርተፍኬት ከመስጠት አኳያ የተሰራ ሥራ አለ፡፡

በአረንጓዴ አሻራ ላይ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችንም በተደጋጋሚ እንዳስቀመጡት በሁለት ምዕራፎች የሚሰራ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ 25 ቢሊዮን ችግኝ፤ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ 25 ቢሊዮን ችግኝ ነው፡፡ በጥቅሉ በ2018 ዓ.ም 50 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል በዓለም ላይ ትልቁ የአረንጓዴ ልማት ፕሮግራም ኢትዮጵያ ነድፋ እየሰራች ነው፡፡

ከ50 ቢሊዮን ችግኝ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት ያለፈውን ዓመት ጨምሮ 32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ተክለናል፡፡ ይህ ባለፈው በዱባይ በተካሔደው ኤክስፖ ኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራሟ ምን አይነት እንደሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልምድ እንዲወሰድ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በተለይ በ2015/16 ክረምት የተተከሉ ችግኞች ባለፈው ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል አቅደን የ2015ቱ ወደ ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች መትከል ችለናል፡፡

ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ባስቀመጡት መሰረት ወደ 60 በመቶ የጥምር ግብርናን እና የፍራፍሬ ችግኞች እንዲሆኑ በሚል በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ወደ 57 በመቶ የጥምር ግብርና እና የፍራፍሬ ችግኞች ተተክለዋል፡፡ ቀሪው ደግሞ ትልቁ ወደ 42 በመቶ የደን ችግኞች መተከል ችለዋል፡፡ ወደ አንድ በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የውበት ችግኞች ናቸው፡፡

የጽድቀት መጠኑን በተመለከተ የሚሰራው ሁለት ጊዜ ነው፡፡ አንደኛው ወዲያው ክረምቱ እንዳለፈ የሚታይ አሰሳ አለ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በጋው አለ፡፡ በመጀመሪያ ዙር ላይ በተደረገው አሰሳ ባለፈው ክረምት ከተከልናቸው ችግኞች 85 በመቶ ጸድቀዋል፡፡ በቀጣይም እንክብካቤውን አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡

የ2016/17 ላይ 50 ቢሊዮን ችግኙ ጋር ለመድረስ የሚቀሩን ሶስት ዓመታት ናቸው፡፡ ስለሆነም የሚቀረን ወደ 18 ቢሊዮን ነው፡፡ በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት በእኛ በኩል እንደግብርና ሚኒስቴር ቢያንስ በየዓመቱ ከስድስት ቢሊዮን እስከ ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብንሰራ የቀረ የሶስት ዓመት እቅዳችንን ለማሳሳካት ከክልሎች ጋር ስለምንሰራ ሁለት ዙር ውይይት አድርገናል፡፡

ከክልሎቻችን የመጣው እቅድ በባለፈው ዓመት የተገኙ የችግኝ ጣቢያዎች ልምዶች አሉ፡፡ ብዙ የተቋቋሙ ችግኝ ጣቢያዎች አሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ወደ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኞች ማዘጋጀት ይቻላል የሚል እቅድ ከክልሎቻችን መጥቷል፡፡ ይህ ማለት ከእቅዱ በላይ ነው። ከክልሎች ጋር ባረግነው ውይይት በጥራት ላይ ትኩረት እንድናደርግና ቦታዎች ቀድሞ የመለየት ሥራ ከመስራት አንጻር በስፋት እንዲሰራ አቅጣጫ አስቀምጠን እየሰራን ነው፡፡ እቅድ ተዘጋጅቶ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ወደስራም ተገብቷል፡፡

ሁለተኛው ከተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ አንጻር ከወሰድን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# "በበጋ መስኖ 117 ሚሊዮን...



ከ6ኛው ገጽ የዞረ

የገጠር መሬት የመመዝገብና ይዞታ ማረጋገጫ የመስጠት በጣም ትልቁ የግብርና ዘርፍ ሥራ ነው፡፡ ባለፉት አምስት ወራት ለመመዝገብ ያቀድነው 600 ሺ ማሳዎችን ነበር። የመጀመሪያ ደረጃ ማረጋገጫ የሰጠነው ወደ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ይዞታዎችን ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ሰርተፍኬት የሚባል አለ፤ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ በተሻለ ጂፒኤስና በቴክኖሎጂ ተወስዶ የሚሰጠው ሁለተኛ ደረጃ ማረጋገጫ በተመለከተ ወደ 170 ሺ ለመስጠት አቅደን ወደ 317 ሺ ማሳዎች ላይ ሁለተኛ ደረጃ ሰርተፍኬት ለመስጠት ችለናል፡፡

እስካሁን ይህ የመሬት ምዝገባ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ወደ 25 ሚሊዮን ይዞታዎች የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም ወደ ሰባት ሚሊዮን ባለይዞታዎች ይህ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሰባት ሚሊዮን አርሶና በእርሻ ላይ የሚተዳደሩ አርብቶ አደሮች ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት በጣም ትልቅ ቁጥር ነው፡፡ ከዚህ ቁጥር ግንዛቤ ሊወሰድ የሚገባው ነገር ከሰባት ሚሊዮን ውስጥ ወደ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን አባወራዎች በተለይ በወንድ የሚመሩ አባወራዎችና ሁለት ነጠብ አምስት ሚሊዮን እማወራዎችን የሚያካትት መሆኑ ነው፡፡ በምዝገባው ሒደት ያየነው ነገር ቢኖር የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ትልቅ የመሬት ባለቤትነትን ያረጋገጠ የለውጥ ሒደት ነው፡፡

በገጠሩ አካባቢ ትልቁ ሀብት የሚባለው መሬት ነው። በዚህ በመሬት ባለቤትነት ደግሞ ሴቶችን ወደፊት ካመጣን ቀጥሎ ያንን በማስያዝ ብድር ከመበደር አንጻር እያዘጋጀን ያለነው የመሬት አዋጅ እሱ ነውና ብድር ሲሰጥ ዋስትና ከመስጠት አንጻር የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሥራ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ባለፈው ዓመት ትልቅ ችግር ሆኖ ከሰነበተው ከአፈር ማዳበሪያ ጋር ተያይዞ ምን የተሰራው ሥራ አለ?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** አራተኛው የግብርና ዘርፋችን የኢንቨስትመንትና ግብዓት ጋር ተያይዞ ያለ ነው፡፡ በተለይ በ2016/17 የምርት ዘመን ከማዳበሪያ አቅርቦት ጋር ተያይዞ እየሰራን የነበረው ወደ 23 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለማቅረብ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ባለፈው ዓመት ማዳበሪያን በብዛትም ሆነ በወቅቱ ከማቅረብ አንጻር በተለይ ኤል.ሲን ከመክፈት አንጻር ትልልቅ ግዢዎች ነበሩ፡፡ የነበሩ ክፍተቶችን በመለየት፣ ለዚያ ያጋለጡንና የተንዛዙ የአሰራር አካሄዶችን በማየት የማዳበሪያ ግዥ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ እንዲቀየር አድርገናል፡፡ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ በምታገኝበት ሒደትና መንገድ የማዳበሪያ ግዥን የመፈጸም ሥራ ተሰርቷል። ግዥው በቀጥታ ከፋብሪካው መግዛት የሚቻልበት ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡ እሱ ብቻ ሳይሆን የማዳበሪያ ዋጋ የሚወርድበትና የሚወጣበት ጊዜ አለ፡፡ ከዚህ በፊት በሚቀንስበት ጊዜ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት የማቅረብ ጉዳይ ስለነበረ በሚቀንስበት ጊዜ ሳንገዛ በሚጨምርበት ጊዜ ጨረታው ሲያልቅ የሚገዛበት ሁኔታና ማዳበሪያው በውድ ዋጋ የሚገዛበት ሁኔታ ነበር፡፡

ስለዚህ ለማዳበሪያ የሚመደበው ብድር በወቅቱ እንዲመደብና ይህንን የሚገዛው አካል የተሻለ ዋጋ በሚኖርበት ጊዜ እና ወቅት ላይ እንዲገዛ ትልቅ ኃይል ነው የተሰጠው፡፡ በተለይ ደግሞ የግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ቦርድ እንደ አዲስ ተቋቋመ። ቦርዱ ውስጥ ውሳኔ መስጠት የሚችሉ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ባንክ፣ ሎጂስቲኪና ትራንስፖርት ሚኒስቴርን ጨምሮ ሌሎችም አካላት ተካተው ወደሥራ ተገብቷል፡፡

ከዚህ አንጻር አምና ለማዳበሪያ የተመደበው ግዥ አንድ ቢሊዮን 59 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን፣ ይህ ትግራይን ጨምሮ ነው፡፡ ባለፈው ዓመት የገዛነው ማዳበሪያ ትግራይን ጨምሮ በ13 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ነበር፡፡ ይህ ማዳበሪያ በቂ እንዳልነበር ይታወቃል፡፡ ተቆራርጦ ያለወቅቱ መግባት ብቻ ሳይሆን በመጠንም በቂ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡

ዘንድሮ የተመደበልን ዶላር ወደ 930 ሚሊዮን ነው። ከአምናው ጋር ሲነጻጸር በመቶ ሚሊዮን ዶላር ያነሰ ነው። ነገር ግን ባደረግነው የአሰራር ለውጥ መሰረት በ930 ሚሊዮን ዶላር ወደ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ መግዛት እንደምንችል ባደረግናቸው ጥረቶች ለማወቅ ችለናል፡፡

ይህ የሚያንስ ከሆነ ተጨማሪ ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አሁን በተፈቀደልን 930 ሚሊዮን ዶላር ሊገዛ የሚችለው ወደ 19 ነጥብ አራት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ከዚህ ውስጥ 15 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ተገዝቷል፡፡

ይህን 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል እንኳን ብንገዛ ከባለፈው 13 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል ጋር ሲተያይ ወደ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ አለው። ኢትዮጵያ በታሪኳ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ገዝታ አታውቅም። በመጠንም ትልቁ ሲሆን፣ የተገዛበትም ዋጋ የተሻለ ከመሆኑ አንጻር የተሻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ዋናው መግዛቱ ብቻ አይደለም፡፡ በወቅቱ ማምጣት መቻል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ዘንድሮ ያደረግነው በአጠቃላይ በዓመት ከምንገዛው ማዳበሪያ ለመስኖ፣ ለበልግ እንዲሁም ለመኸር ምን ያህሉ ነው የሚያስፈልገው የሚለውን ከክልሎች ጋር ሆነን ለይተናል፡፡ በአጠቃላይ ከሚገዛው ማዳበሪያ 25 በመቶ የመስኖ ስንዴን ጨምሮ ለመስኖ ጊዜ የሚፈለግ ነው። ወደ 20 በመቶ ደግሞ በልግ አካባቢ የሚፈለግ ሲሆን፣ 55 በመቶው በመኸር ጊዜ የሚፈለግ ነው፡፡ ሲገዛም ይህ ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡

ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት ለመስኖና ለበልግ የሚያስፈልገው ማዳበሪያ ሙሉ በሙሉ ተገዝቷል። ሙሉ በሙሉ ኤል.ሲ ተከፍቷል፡፡ ሙሉ በሙሉ የመጫን ሂደቱም እየተካሄደ ነው። ባለኝ መረጃ ከተገዛው 15 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ ወደ ሶስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ጂቡቲ ደርሷል፡፡ ጂቡቲ ከደረሰው ሶስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ማዳበሪያ ውስጥ ወደ ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ወደክልሎች ተጓጉዟል፡፡

ማዳበሪያ የጫነችው የመጀመሪያዋ መርከብ ዘንድሮ ጂቡቲ የደረሰችው ጥቅምት ወር ነው፡፡ ይህም በየትኛውም ጊዜ የማዳበሪያ ግዥ ካደረግናቸው ሁሉ የፈጠነ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ጂቡቲ ከደረሰው መካከል 74 በመቶ ማዳበሪያ ወደሀገር ውስጥ እንዲገባ እኔና የሎጂስቲክና ትራንስፖርት ሚኒስትሩ የምንመራው የሎጂስቲክ ኮሚቴ ተቋቁሞ በባቡርም በመኪና በፍጥነት እስከ ክልሎች የሚደርስበት ሁኔታ በጥልቅ ዲሲፒሊን እየተመራ ነው፡፡

ከማዳበሪያ አንጻር መንግሥት ትልቅ ውሳኔ ወስኗል። ምንም እንኳ በግዥ ሒደቱ ላይ ከአምና ጋር ሲተያይ በተሻለ ዋጋ ማዳበሪያ መግዛት ብንችልም ከአምናው ጋር ሲተያይ ወደ 20 ቢሊዮን ብር የሚሆን ቁጠባ ማድረግ ተችሏል፡፡ ነገር ግን እንዲያም ሆኖ አሁን በዓለም ላይ ያለው የማዳበሪያ ዋጋ ከአርሶ አደሮች የመግዛት አቅም ጋር ሲታይ ከፍ ያለ ከመሆኑ አንጻር ወደ 16 ቢሊዮን ብር መንግሥት ድጎማ በማድረጉ አምና ከነበረው የማዳበሪያ ዋጋ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ዋጋ ጭማሪ ሳይደረግበት ለአርሶ አደሩ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ እንዲህ ሲባል የተደጎመው አርሶ አደሩ ብቻ ነው ማለት አይደለም፡፡ አርሶ አደሩ ሲደጎም ኅብረተሰቡ በሙሉ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

ማዳበሪያ በወቅቱ መግዛቱና ወደሀገር ውስጥ ማስገባቱ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን በስርጭት ሒደት ባለፈው ዓመት ያጋጠመው ተግዳሮቶችን ከመቀነስ አንጻር የተሰሩ ስራዎች አሉ፤ ቀሪ ስራዎችም አሉ፡፡ የተሰሩ ስራዎች ስንል አንደኛው አቅርቦቱን ስለጨመርን የዘንድሮ የማዳበሪያ አቅርቦት ከአምናው አቅርቦት ጋር ሲተያይ በስድስት ሚሊዮን ብልጫ አለው፡፡ ይህ አምና የተፈጠረውን እጥረት ስለሚፈታ በገበያው ላይ ያለው ሽሚያ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብለን እናምናለን፡፡

ስርጭቱን በሚመለከት ከክልል አመራሮች፣ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እስከ ታች ድረስ ኮሚቴዎች ተቋቁሞ በክትትልና በድጋፍ በሥርዓቱ እንዲደርስ እየተኬደበት ይገኛል፡፡ በተጨማሪ ይህን የሚያክል ማዳበሪያ በሚንቀሳቀስበት የአሰራር ሥርዓት ውስጥ በማኑዋል ብቻ መከታተሉ ችግሮቹን ሙሉ በሙሉ ስለማይቀርፍ ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፣ ከኢትዮ ቴሌኮምና ሌሎቹም የሳይንስና ኢኖቬሽን ጋር አብረን እየሰራን እንገኛለን፡፡ ዲጂታል ትራኪኒግ ሲስተም እየዘረጋን ሲሆን፣ ዘንድሮ ለሙከራ የምንሄድበት ይሆናል፡፡

ይህ ማለት ማዳበሪያው ከጂቡቱ ሲጫንና ሲታሸግ እዛ ላይ ምልክቶች ማለትም ባር ኮዶች የሚደረጉ ይሆናል። ለምሳሌ ለአማራ ክልል ከተጫነው ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ የደረሰው ስንቱ ነው? በሕገ ወጥ መንገድ የሚዘዋወር ማዳበሪያ ካለ የትኛው ክልል ነው? የሚለውን በቀላሉ መለየት ያስችላል። እንዲሁም ለሕገ ወጥ ንግዱ የተጋለጠው የት አካባቢ ነው? የሚለውን መለየት ስለሚያስችል የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግብርናው በውጤት የታጀበ ይሆን ዘንድ የምርጥ ዘር አቅርቦት ላይ ምን እየተሰራ ነው?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** ከግብዓት አቅርቦት አንጻር ከማዳበሪያው ቀጥሎ በጣም በትልቁ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚፈለገው የምርጥ ዘር አቅርቦት ነው፡፡ ምርጥ ዘር ባለፉት ዓመታት በአማካይ ወደ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የሚቀርብበት ሁኔታ አለ፡፡ ከዘንድሮ ጀምሮ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የዘር አቅርቦትን በእጥፍ ለመጨመር እየሰራን ነው። ዘንድሮ ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ዘር እናቀርባለን ብለን አቅደናል፡፡ በተለይ በዚህ በመስኖ ወቅት ወደ 128 ሺ ኩንታል ዘር ባለፉት አምስት ወራት ቀርቧል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ግብርና የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት አኳያ ሰፊ እድል ያለው በመሆኑ ከዚህ አንጻር የተገኘው ውጤት ምን ይመስላል?**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** ከግብርና ኢንቨስትመን ጋር ተያይዞ አንዱ በግብርናው ዘርፍ የሚመጣው የውጭ ምንዛሪ ነው። ኤክስፖርቱን እንደ ማሳያ ለመጥቀስ ያህል የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በተመለከተ ከ70 እስከ 80 በመቶ አስተዋጽኦ የሚያደርገው የግብርናው ዘርፍ ነው፡፡ ሁለት ቦታ ላይ ለግብርና ምርቶች ክትትል የሚደረግባቸው ቦታዎች አሉ። ይህም በግብርና እና በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ስር ነው፡፡ በተለይ በእኛ በኩል ቡና፣ ቅመማቅመም፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳት ተዋጽኦ ሲሆኑ፣ የቅባት እህሎችንና የጥራጥሬ ሰብሎችን ጨምሮ ደግሞ ንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር የሚከታተላቸው ናቸው፡፡

እኛ ከምንከታተላቸው ዘርፎች ባለፉት አምስት ወራት ወደ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ለመሰብሰብ አቅደን ያስገኘነው ወደ 764 ሚሊዮን ዶላር አካባቢ ነው፡፡ ይህ ከእቅዱ አንጻር ሲታይ ወደ 65 በመቶ ያህል ነው፡፡ ስለዚህ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችንን በተመለከተ ከእቅድ አንጻር ብዙ ስራዎችን በቀጣዮቹ ወራት መስራት እንዳለብን ያመላክተናል።

ይህ እንዳለ ሆኖ በዓለም ላይ የቡና ዋጋ ከመቀነስና ከመቀዛቀዝ ጋር ተያይዞ በአበባም ዋጋና ፍላጎት ላይ መጠነኛ መቀዛቀዝ ከመኖሩ አንጻር የተወሰነ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ ስለዚህም በቀጣዮቹ ወራት ተጨማሪ ስራዎችን እንሰራለን፡፡

የግብርና ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር ሰፊ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም አንዳንድ አካባቢዎች በተለይ ዝናብ አጠር የሆኑና በሴፍቲኔት የሚተዳደሩ አካባቢዎች አሁንም አሉ፡፡ እነዚህን ባሉን ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራሞች ለማስኬድ እንሞክራለን፡፡ በመደበኛ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራምና የእለት ደራሽ አሰራርም አለን፡፡ በመሆኑም ከልማት አጋሮቻችን ጋር በመሆን ባለፉት አምስት ወራት ወደ ሶስት ነጥብ 27 ቢሊዮን ብር በልማታዊ ሴፍትኔትና በዕለት ደራሽ ለክልሎች ተላልፏል፡፡ ክልሎች የተላለፈላቸውን ፋይናንስ ወስደው እንደየአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ በተለይ ድርቅና የዝናብ እጥረት የተከሰተባቸው አካባቢዎችን እንዲደግፉ ታስቦ የሚደረግ ነው፡፡ በታህሳስ ወር ወደ 523 ሚሊዮን ተጨማሪ ድጋፍ ለክልሎች ለማስተላለፍ ጥያቄ ቀርቦ እየተሰራበት ነው፡፡

ሌላው ለክልሎች ድጋፍ ከመስጠት አንጻር ባለፉት አምስት ወራት ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ሰርተናል፡፡ ባለፈው ሳምንት በተለይ ለመስኖ ስንዴ ሊያግዝ የሚችል ወደ 12 ሺ 617 ፓምፖችን ለክልሎች ግዥ ተፈጽሞ እየተጓጓዘ ይገኛል፡፡ ከዚህ ውስጥ ወደ አንድ ሺ 600 ፓምፖች ሀገር ውስጥ ገብተው ባለፈው ሳምንት ክፍፍል ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህ የቀረበው ከመሬቱ ስፋት አንጻር ሲሆን፣ ወደ አንድ መቶ ሺ ሔክታር አካባቢ ላይ ድጋፍ ማድረግ የሚችልና 503 ሚሊዮን ብር የወጣበት ድጋፍ ነው፡፡

ሁለተኛው የሎጂስቲክስ ድጋፍ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ባለፉት አምስት ወራት ወደ 221 ተሽከርካሪዎች እና አንድ ሺ 800 አካባቢ ሞተር ሳይክሎች በመግዛት ለክልሎች ተሰራጭተዋል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አምስት ወራት የግብርናው ዘርፍ በዋና ዋና ዘርፎች ላይ የመኸር ሰብሉ ከመሰብሰብ፣ የበጋ መስኖ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በፍጥነት ከማስኬድና በተለይ በአረንጓዴ አሻራ የተተከሉትን ችግኞች ከመከታተል ብሎም የጽድቀት መጠናቸውን ከማሳደግ አንጻር መስራት አለበት፡፡ በቀጣዮቹም ወራት ለሚቀጥለው ክረምት ዝግጅት ከማድረግ አንጻር እንዲሁም አምና ካጋጠመን ችግር ትምህርት ወስደን በተለይ በማዳበሪያ ላይ ያደረግነው ለውጥ በዚህ አምስት ወር ከሰራነው ሥራ ትልቁና ውጤታማ ሥራ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ ባለፉት አምስት ወራት ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም በሀገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ ውስጥ የግብርናው ዘርፍ የተሰጠውን ተልዕኮና ሥራ እየተወጣ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ውጤት ግን በግብርና ተቋም ብቻ የተገኘ ሳይሆን ከሚኒስቴሩ እስከ ቀበሌ ድረስ ባለው ርብርብ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ስራውን የሰሩት አርሶ እና አርብቶ አደሮቻችን እንዲሁም የልማት ሠራተኞቹ ናቸው፡፡ ለዚህም ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የሌሎችም ሴክተሮችና የልማት አጋሮች ድጋፍ ከጎናቸው ስለነበር ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ያለ ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን፡፡**

**ግርማ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ማህደረ ጤና

# የጥርስ ጤና ችግርና የ‹‹ብሬስ›› ሕክምና

**መክሊት ወንድወሰን**

ጥርስ ከማኘክና ከመካነ ድምጽነት ዋና ሚናው ባሻገር የውበት መገለጫም ነው፡፡ የጥርስ ደህንነት መጓደል መንታ ጉዳት ያስከትላል የሚባለውም ጥርስ ጤናም ውበትም ስለሆነ ነው። እንደዛሬው የጥርስ ክትትልና ሕክምና ማዕከሎች ከመስፋፋታቸው በፊት ሰዎች የተለያዩ ባህላዊ የጥርስ አጠባበቅ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል። እንደ ንቅሳት፣ ከሰል፣ መፋቂያ፣ ጨውና የመሳሰሉት ከጥርስ መጠበቂያ ዘዴዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ጥርስ የውበት መገለጫ ስለመሆኑ በርካታ የሀገራችን ድምጻውያንና ባለቅኔዎች ከጥንት ጀምሮ ሲቀኙለት ኖረዋል፡፡ ለአብነትም- ‹‹ጥርሴማ ወዳጅሽ ያላንቺ አልስቅ አለ››፣ ‹‹ እርሷ ቆንጆ ጥርሷ የሚያምር- ያዘኝ ፍቅር››፣ ‹‹ያቺ ቆንጆ ጥርሰ በረዶናት-ውብ ዓይናማ ናት››፣ ‹‹ፍንጭቷ-ነው ምልክቷ›› የሚሉትን ስንኞችና ሐረጎች ማስታወስ ይቻላል፡፡ ዛሬ ደግሞ የጥርስ ጤንነት በዓለማችን ጥልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሆኗል፡፡ የተለያዩ የጥርስ ሕክምና መስጫ መሳሪያዎችም በየጊዜው እየዘመኑ መጥተው ለዚሁ ተግባር እየዋሉ ይገኛሉ፡፡

የሰው ልጅ የእድገት ደረጃውን ሲጨርስ 32 የሚሆኑ የተለያየ ተፈጥሯዊ ባህሪ ያላቸው ጥርሶች እንደሚኖሩት ሳይንስ ይናገራል፡፡ እነዚህም ጥርሶች በተለያዩ ቅርጾችና መጠን ተግባራቸውን ለማከናወን አብረው የሚሠሩና የተለያዩ ንብርብሮች ያሏቸው ናቸው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዲያ በከፍተኛ ሁኔታ የጥርስ ሕመም ችግር እየተስፋፋ እንደሚገኝ ይነገራል፡፡ የዓለም የጤና ድርጅት ባወጣው መረጃ መሠረት በዓለም ላይ ወደ 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ የጥርስ ጤና ችግር አለበት፡፡ ከዚህ ቁጥር ውስጥ ከአራት ሰው ሶስቱ የሚገኙት በታዳጊ ሀገር መሆኑ ደግሞ ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡

እንዲሁ ሲታዩ ጥርሶች ቀላልና ያልተወሳሰቡ ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን በቅርበት ሲመረመሩ የተለያዩ ንብርብሮች ያሉባቸው ናቸው፡፡ ጥርስ ‹‹ኢናሜል፤ ዲንቲን፤ ፐልፐ እና ሲሜንቲን›› የተሰኙ ድርብርቦሽ አሉት፡፡ የጥርስ ጤንነት እና ደህንነት መጠበቅ ከማኘክ እና ከመናገር በዘለለ ለሰው ልጆች ትልቅ ውበትን የሚያጎናጽፍ በመሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀ ጥርስ በራስ መተማመንን ይጨምራል፡፡ ለዚህም ነው በርካታ ሰዎች ጥርሶቻቸውን የሚያሳጥቡት፣ የሚያስሞሉትና የጥርስ ብሬስ የሚያደርጉት። የዛሬው የአዲስ ዘመን የማህደረ ጤና አምድም በብሬስ የጥርስ ደህንነትና አጠባበቅ ላይ ያተኩራል።

ዶክተር ዳንኤል ሹካሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሕክምና ትምህርት ቤት የጥርስ ሕክምና ማዕከል ኃላፊና የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፣ ጥርስ የሚገኘው የመንጋጋ አጥንት ውስጥ ሲሆን ከመንጋጋ ወደ ጭንቅላት ከሚሄድ ነርቭ ጋር ይገናኛል፡፡ አንድ ጥርስ ለብቻው ነርቭ፣ የደም ስር እና ከላይ ከሚገኘው ጠንካራ ክፍል የተዋቀረ ነው፡፡

ጥርስ የተሠራው ከካልሺየምና ካልሺየም ካለባቸው ንጥረ ነገሮች ነው፡፡ አፍ ውስጥ በተፈጥሮ የሚገኙ ባክቴሪያዎች ምግብ ከተበላ በኋላ አፍና ጥርስ የማይፀዳ ከሆነ በፈርመንቴሽን ወደ አሲድነት ይቀይረዋል፡፡ ይህም የጥርስን ጠንካራ ክፍል ይበላዋል፤ ለጥርስ መቦርቦርም መንስዔ ይሆናል፡፡

የጥርስ ሐኪሙ ዶክተር ኢዮኤል ገብሬ በበኩላቸው እንደሚናገሩት ጥርስ ከተቦረቦረ በኋላ ውስጠኛው ክፍል ላይ ነርቭ ስላለ በቅዝቃዜ ወቅት



ዶክተር ኢዮኤል ገብሬ፣

ሲታኘክበት ሕመም ይፈጥራል፡፡ ዳቦ፤ መኮረኒ እና ፓስታ የመሳሰሉ ካርቦሃይድሬት ያለባቸው ምግቦችን ከተመገቡ በኋላ ጥርስ የማይፀዳ ከሆነ የምግብ ትራፊዎቹ በባክቴሪያዎቹ ወደ አሲድነት ተቀይረው ጥርስን ይጎዳሉ፡፡ ይህ ችግር ትኩረት ከማጣት የተነሳ በሕፃናቶች ላይ በብዛት ይታያል። በተጨማሪም በተለምዶ ‹‹ሴቶች ጣፋጭ ነገር ስለሚያዘወትሩ እና አረጋውያን ጥርሳቸው ለረጅም ጊዜ ከማገልገሉ የተነሳ ደህንነቱ ላይጠበቅ ይችላል››።

በበርካቶች ዘንድ የጥርስ ደህንነትና ጤንነት እንዳይጠበቅ የሚያደርገው ምክንያት ጥርስ በተገቢው መንገድ አለማጽዳትና በየስድስት ወሩ በቋሚነት ባለሙያ ጋር እየሄዱ አለመታየት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ግን እንደ ሲጋራ እና አልኮል ሱስ ተጠቂ የሆኑ ሰዎች ለጥርስ ደህንነት ችግር ብቻ ሳይሆን ለአፍ ውስጥ ካንሰር ጭምር ተጋላጭ ናቸው፡፡ የአፍ ውስጥ ካንሰር በራሱ የጥርስ አቃፊዎችን የሚጎዳ ሕመም በመሆኑ የጥርስ ሕመምን ይፈጥራል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ እንደ ቡናና ሻይ ያሉ ትኩስ ነገሮች በራሳቸው ጥርስን የማበለዝ ባህሪ ያላቸው ሲሆን ውስጣቸው በሚጨመርባቸው ስኳር አማካኝነት ደግሞ ጥርስ እንዲቦረቦር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እንደ ዶክተር ዳንኤል ገለጻ በተገቢው መንገድ ጥርስን ካለማጽዳት በተጨማሪ የጥርስ ጤንነትን የሚጎዱ የውስጥ ደዌ ሕመሞች አሉ። ለአብነትም የጨጓራ ሕመም፤ የደም ግፊት ሕመም እና የስኳር ሕመምን መጥቀስ ይቻላል። በተለይ የጨጓራ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ጨጓራቸው ውስጥ የሚፈጠረው አሲድ ወደ አፍ በመምጣት የጥርስ ክፍሎችን እና ድድን ሊያጠቃ ይችላል፡፡ ስኳር ያለባቸው ታማሚዎችም ሌሎች የሰውነት ክፍሎቻቸውን በየጊዜው እየሄዱ እንደሚመረመሩት ሁሉ ጥርሶቻቸውን ስለማይታዩ የጥርስ አቃፊዎቻው ተጎድተው ጥርሶቻቸው እስከመውለቅ ይደርሳሉ። የደም ግፊት መድኃኒት የሚወስዱ ሰዎች ደግሞ መድኃኒቱ በራሱ የድድ እብጠት ስለሚያመጣ የጥርስ ደህንነትን ይጎዳል፡፡

የጥርስ አፈጣጠር የሚጀምረው ልጆች ከመወለዳቸው በፊትና ከተወለዱ በሳምንታት እድሜ ውስጥ በአጥንት ውስጥ እንደሆነ ይታመናል። ልጆች ከተወለዱ ከስድስት ወር ጀምሮ ደግሞ መብቀል ይጀምራል፡፡ እስከ ሁለት ዓመት ተኩል 20 ጥርሶች አብቅለው ይጨርሳሉ፡፡ ስድስት ዓመት ሲሞላቸው ሁሉም ጥርሶች በየተራ ይወልቃሉ፡፡



ዶክተር ዳንኤል ሽካሬ፣

በአሁኑ ጊዜም በርካታ ሰዎች ውበታቸውን ለመጠበቅ ከፍተኛ ወጪ አውጥተው እራሳቸውን ለማስዋብ ይሞክራሉ፡፡ ከዚህ ውስጥም የውበት መለኪያ ተደርጎ የሚወሰደው የጥርሳቸውን አቀማመጥ ለማስተካከል በርካታ ወጪ አውጥተው የሚያሰሩት የጥርስ ብሬስ ነው፡፡ ይህን የሚያሰሩት ደግሞ በአበቃቀል ምክንያት የተበላሸውን ጥርስ ለማስተካከል ነው፡፡

ለአበቃቀል ችግር እንደምክንያትነት የሚቀርበው የወተት ጥርሶች በጊዜው ሳይወልቁ ሲቀሩ እና ቀድመው ተቦርቡረው እንፌክሽን ፈጥረው ከወለቁ ቋሚ ጥርሱ እሱን ተከትሎ የሚበቅል በመሆኑ ከተገቢው አቀማመጥ ተንሻፈው ሊበቅሉ ይችላሉ፡፡ ሌላኛው ደግሞ ሰዎች የጥርስ አቀማመጣቸውንና መጠናቸውን ከወላጆቻቸው የሚወርሷቸው በመሆኑ ከዛ ጋር ተያይዞም የአበቃቀል ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ ለአበቃቀል ችግር እንደመፍትሔ የሚወሰደውም የጥርስ ብሬስን ማሰር ነው፡፡

ዶክተር ኢዮኤል እንደሚሉት ሰዎች የጥርስ ብሬስን ለአበቃቀል ችግሮች ብቻ ሳይሆን ከሕመም ጋር ለተያያዘ ሁኔታም ሊጠቀሙት ይችላሉ፡፡ የጥርስ ማስተካከያ ብሬሶች ከውበት ባሻገር ለጥርስ ጤና ጥቅምም ይደረጋሉ፡፡ ጥርሶች ተደራርበው የተቀመጡ ከሆነ ለማጽዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን የጥርስ ብሬስ ሊታሰር ይችላል፡፡ የአበቃቀል ችግር ሲኖርና የአነካከስ ችግር ካለም የጥርስ ብሬስ እንዲያደርጉ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ ዘመን በርካታ የተለያዩ የብሬስ ዓይነቶች እየተዋወቁ ቢሆንም በዋናነት ግን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነርሱም ቋሚ እና ወጪ ገቢ የሚባሉ የጥርስ ብሬስ (የጥርስ ማስተካከያ) ዓይነቶች ናቸው፡፡ ቋሚ የጥርስ ማስተካከያዎች ጥርስ ላይ ተጣብቀው ጥርሶችን እንዲያስተካክሉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ቋሚ የጥርስ ብሬስ ዓይነቶች የተለያዩ ቢሆኑም በስፋት የተለመዱት ከስይንለስ ስቲል የተሰሩ እና ከሴራሚክ የተሰሩት ናቸው። እነዚህን የጥርስ ብሬስ ዓይነቶች ታካሚዎች እንዲጠቀሙ የሚደረገው እንደ ታካሚዎቹ የጥርስ አቀማመጥ እና እንዳሉበት የጤና ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡

ዶክተር ዳንኤል እንደሚናገሩት ብሬስ ሲሰራ ከሐኪሞች በኩል ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄ በቅድሚያ ብሬሱን ከማሰራቸው በፊት ችግሩን በተገቢው መንገድ በመለየት የትኛውን የብሬስ ዓይነት ማድረግ እንደሚገባቸው፤ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት፤ የታካሚውን የጥርስ አቀማመጥ በማሳየት ስለሁኔታው ማስረዳት፤ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በሙሉ መኖራቸውን ማረጋገጥና እና እቅድ በማውጣት የክትትል ጊዜውን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

በጥርስ ብሬስ ታካሚዎቹ በኩል ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች መካከል በቅድሚያ ከሐኪሞቻቸው ጋር በመመካከር የሚሰራው ሥራ ምን እንደሆነ ሊያውቁ ይገባል፡፡ የጥርስ ማስተካከያ ብሬሱ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል በመሆኑ በተገቢው መንገድ ክትትል ሊያደርጉ እንደሚችሉ ማረጋገጥና በቀጠሮ ቀናት እየተገኙ ተገቢውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ራቅ ወዳለ ቦታ የሚሄዱና ለክትትል የሚመች የሥራ ሁኔታ ከሌላቸው ሕክምናውን ማድረግ መጀመር የለባቸውም፡፡

ብሬስ ሲደረግ ጥርስ ላይ የሚቀመጠው የምግብ ትራፊ ስለሚበራከት በተደጋጋሚ ማጽዳትና ጥርሶችን ለማጽዳት እንደማይመች በመረዳት ለብሬስ ተብለው የሚሰሩ የጥርስ ማጽጃ ብሩሾችን በመጠቀም በብሬሶቹ መካከል ማጽዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ብሬሱ ሲደረግ የጥርሶች እንቅስቃሴ ስለሚኖር የጥርስ አቃፊ ደህንነት ለመጠበቅ የተለያዩ የአፍ መጉመጥመጫዎች መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ከፍተኛ የሕመም ስሜት ካላቸውም ከሐኪሞች ጋር በመነጋገር በቶሎ ችግሩን ሊፈቱት ይገባል፡፡

ይህ ዓይነቶቹ ጥንቃቄዎች በሐኪሙና በታካሚው በኩል ካልተደረጉ የጥርስ አቃፊዎቻቸው መድማት ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ወቅት ተገቢውን የሕክምና ርዳታ ሳያገኙ ከቀሩ ጥርሶቻቸው መነቃነቅ እና ሙሉ ለሙሉ እስከመውለቅ ሊደርስ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተገቢው መንገድ ክትትል ካላደረጉና በባለሙያ የጥርስ ብሬሱ ካልታሰረ በፊት ከነበረው በባሰ መልኩ የጥርሱ አቀማመጥ ሊበላሽ ይችላል። ከዚህም አለፍ ሲል ለአፍ ውስጥ ጤና ችግሮች ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ታካሚዎች በተገቢው መንገድ ጥርሶቻቸውን ካላጸዱ ለአፍ ውስጥ እጢ ችግር፤ የድድ ሕመም፤ ለጥርስ መነቃነቅ እና መውለቅ ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

የጥርስ አቀማመጥ ችግር ክትትሉ ገና በልጅነት የሚጀመር ቢሆንም ብሬስን ወይም የጥርስ ማስተካከያን ማድረግ የሚገባቸው ግን የልጅነት ጥርስ (የወተት ጥርስ) ሙሉ በሙሉ ወልቆ ሲያልቅና ቋሚ ጥርሶች ሲበቅሉ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም እድሜያቸው የገፉ ሰዎች የጥርስ ብሬስን እንዲያደርጉ አይመከርም፡፡ ከተደረገም ተጨማሪ ጥንቃቄና ክትትል ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሌላው የጥርስ ብሬስን እንዳያደርጉ የሚመከሩት ያልተቆጣጠሩት የስኳር ሕመም ያለባቸውና የደም ግፊት መድኃኒትን የሚወስዱ፤ የልብ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ናቸው፡፡

እንደ ዶክተር ዳንኤል ማብራሪያ ስኳር ሕመም ያለባቸውና የስኳር መጠናቸውን መቆጣጠር ያልቻሉ ሰዎች የጥርስ አቃፊያቸው ላይ ችግር ስለሚኖር ብሬስ አድርገው ንጽህናውን የማይጠብቁ ከሆነ ችግሩን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል፡፡ የልብ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ካሉና ጥርሶቻቸው ተደራርበው ከተቀመጡ የብሬስ ሕክምናውን ለመጀመር በሐኪሙ ትእዛዝ ጥርስ መውለቅ ሊኖር ስለሚችል ያለባቸውን የጤና ችግር በቅድሚያ ለሐኪሙ በመናገር ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግላቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሰዎች ጥርሶቻቸውን ከመታከማቸው በፊት ተገቢውን የጤና ተቋም መምረጥና ስለሐኪሙ የሙያ ደረጃ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በጥርስ ሕክምና ስፔሻላይዝድ ያደረጉ ሐኪሞች ጋርም መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ተጨማሪ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ከሐኪሞቻቸው ጋር በመመካከር ተገቢውን የጤና ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# የቅኝ ገዢዎች ፍላጎት ማስፈጸሚያ የነበሩ የዓባይ ውሃ አጠቃቀም ውሎች

**እስማኤል አረቦ**

ዓባይ የሚለው የአማርኛ ቃል አንዳንዶች የወንዞች ሁሉ አባት ከሚለው የመጣ ነው ይላሉ፤ ሌሎች ደግሞ አታላይ፣ ቀጣፊ፣ ለኢትዮጵያ ያልጠቀመ ከሃዲ በሚለው ይበይኑታል፡፡ ቃሉ ላልቶ ሲነበብ ከሚፈጥረው ትርጓሜ በመነሳት ዓባይ ውሸታም ማለት እንደሆነም የሚናገሩ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2፤ ቁጥር 13 ላይ ወንዙ ፈለገ-ጊዮን ተብሎ የሚጠራው ይኸው ወንዝ እንደሆነ የሚስማሙ አሉ።

የዓባይ ተፋሰስ የአፍሪካን አንድ አስረኛ ግዛት የሚሸፍን ከመሆኑም በተጨማሪ የተለያዩ የአየር ፀባዮችን ያስተናግዳል። በታላላቅ ሐቆይች አካባቢ የኢኩዋቶሪያል አየር ንብረትን፣ ከምስራቅ አፍሪካ የታቿኛው ክፍል ሲነሳ የትሮፒካል፣ ከዚያም ነፋሻማውን የኢትዮጵያ ከፍታ አምባ አቋርጦ በረሃማና ምድረ በዳማ በሆነው የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክልል ዘልቆ ሜዲትራኒያን ባህር በመግባት ጉዞውን ይጨርሳል፡፡

በዚህ ረዥም የጉዞ ሂደት ውስጥ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ሱዳን፣ ግብጽና ደቡብ ሱዳን አቋርጦ ያልፋል። ኢትዮጵያ የዓባይ ንዑስ ተፋሰስ የሆነው የጥቁር ዓባይ ምንጭ ነች፡፡ እስከ 86 በመቶ የሚደርሰውም የናይል ወንዝ ውሃ የሚመነጨውም ከዚቹ ሀገር ነው፡፡ ይህ የውሃ ድርሻዋም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ባለሙሉ መብትና ባለብዙ ተጽዕኖ አሳራፊ ሀገር እንድትሆን አስችሏታል፡፡

ታሪክ ፀሐፊው የአረብ ተወላጅ አልማኪን እንደፃፈው፤ በፋቲሚድ ሥርወ-መንግሥት በሱልጣን አቡታምሊን አልሙስታንዚር የአገዛዝ ዘመን (1035-1094) ግብጽ የሚደርሰው የዓባይ ወንዝ ውሃ መጠን ከ1089-1090 ባለው ጊዜ አካባቢ በመቀነሱ ሱልጣኑ የግብጽ ቤተ-ክርስቲያንን ፓትርያርክ አባሚካኤልን ከፍ ያለ ገጸ-በረከትአስይዞ በኢትዮጵያውያን የተቋረጠውን የዓባይን ወንዝ እንዲለቁ ለመለመን ወደ ኢትዮጵያ ልኳቸዋል። ጉዞውም በ1092 እና 1094 ዓ.ም መሀከል ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር።

ሌላው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አንድ ኮረብታ እንዲፈርስ ባዘዘ ጊዜ የውሃው መጠን በአንድ ሌሊት ሶስት ጫማ ከፍ ብሎ አደረ ሲል ተርኳል፡፡ በዘመኑ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሥ የዛግዌውይምርሀነ ክርስቶስ እንደነበር ዘውዴ ገ/ሥላሴ የተባሉ ምሁር ‘የዓባይ ተፋሰሶች ዓለም አቀፋዊ ችግር’ በሚል ርዕስ በሳፈሩት ጽሑፍ ላይ ጠቁመዋል፡፡

ሆኖም ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ያላትን መብትና ተጽዕኖ ፈጣሪነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጣች መጥታለች፡፡ በተቃራኒው ቀደም ሲል ለኢትዮጵያ ሲገብሩና ሲመለዱ የነበሩት ግብጾችና ሱዳኖች የቅኝ ገዢዎችን በተለይም የእንግሊዝን ተጽዕኖ ፈጣሪነት በመጠቀም የበላይነቱን ለመያዝ ሞክረዋል። የተዛባ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መብቶችን በመጠቅስ የመከራከሪያ አጀንዳ አድርገው ማቅረብ ጀምረዋል፡፡

በታሪካዊ እና ተፈጥሯዊ መብቶች ላይ ተመስርተው በታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ከሚቀርቡ የመብት ክርክሮች መለስ ዓባይን አስመልክቶ እስከአሁን ያለውን ሕጋዊ ሁኔታ በዋናነት የሚወስኑ ሁለት ሰነዶች ናቸው፣ የመጀመሪያው በቅኝ ግዛት ዘመን እ.ኤ.አ ግንቦት 7 ቀን 1929 በታላቋ ብሪታኒያና በግብፅ መካከል የተደረገው ስምምነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከሰላሳ ዓመት ቆይታ በኋላ ከነጻነት ወዲህ እ.ኤ.አ ኅዳር 8 ቀን 1959 በሱዳንና ግብጽ መካከል የተፈረሙ ስምምነቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለት ስምምነቶች በሚፈረሙበት ወቅት እንግሊዝ ከላይኛው ተፋሰስ ሀገራት ሱዳንን፣ ታንዛኒያን፣ ኡጋንዳን፣ እና ኬንያን በመወከል ግዴታ ከመግባትዋ ውጭ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎቹ የተፋሰሱ ሀገራት ተካፋይ አልነበሩም፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ በወቅቱ ነፃ ሀገር ከመሆኗ ጋር ተያይዞ በስምምነቱ ተካፋይ መሆን ቢገባትም በሂደቱ በጋራ መብትዋን እንድትወስን ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳይቀርብላት ቀርቷል፡፡

በ1929 እና 1959 በተደረጉት ስምምነቶች መሠረት ግብጽ በዓባይ ላይ የፍሰቱን ባለቤትነት መብት ስትጎናፀፍና በተጠቃሚነት ረገድም ከ55ቢሊዮን ኪዩብ በላይ ድርሻ እንዲኖራት ሱዳንም 18 ቢሊዮን ኪዩቢክ የውሃ መጠን ድርሻ እንዲኖራት ተደርጓል። ከ86 በመቶ በላይ የውሃው ባለቤት የሆነች ኢትዮጵያ ግን ቅንጣት ታክል የውሃ ድርሻ እንዲኖራት አልተደረገም፡፡

እነዚህ ሁለቱ ስምምነቶች እስከዛሬም ድረስ በሕዳሴ ግድብ ላይ በሚደረጉ ውይይቶች እንደማጣቀሻ እየቀረቡ ግብጾች በማደናገርያነት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። ሰሞኑንም አራተኛው ዙር የመጨረሻው ድርድርም በአዲስ አበባ ለሦስት ቀናት ያህል ሲካሄድ ቆይቶ ያለ ውጤት ተበትኗል፡፡ ለውይይቱ ያለ ውጤት መበተን ዋነኛው ምክንዓትም ግብጽ የቅኝ ግዛት ዘመን አቋሟን በመያዟ ኢትዮጵያ ባልፈረመችው ውል እንድትገዛ በግብጽ በኩል ከፍ ያለ ፍላጎት በመኖሩ ነው። ይህ ደግሞ “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” የሚለውን ሀገራችንን ተረት የሚያስቀውሰን ነው፡፡

ለዛሬ በግብጽ በተደጋጋሚ በመከራከሪያነት የሚቀርቡትን በታሪክ ሰነድም የቅኝ ግዛት ውሎች ተብለው የሚጠሩት የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ውሎች ከኢትዮጵያውያን ጋር ያላቸውስ ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን በአጭሩ እንመልከት ፡፡

## 1929 ውል

በ19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ፣ እንግሊዝ ግብጽን በቁጥጥሯ ካስገባች በኋላ፣ ግብጽን አረጋግቶ ለመግዛት ዋናው ቁልፍ የዓባይ ውሃ መሆኑ እንግሊዝ ተረዳች፡፡ ግብጽ ውስጥ ለመደራጀትና በስዊዝ ቦይ ላይ እንግሊዝ ያላትን ስትራቴጂ ይዛ ለመቀጠል ከፈለገች፣ የዓባይ ውሃ ያላንዳች እክል ወደ ግብጽ ግዛት እንዲዘልቅ ማድረግ ዋናው ዘዴ መሆኑን ተገነዘበች፡፡

ይህንኑ መነሻ በማድረግ እንግሊዝ በቅኝ ግዛት የያዘቻቸውን ሀገራት (ሱዳን፣ ኬንያ፣ ታንጋኒካና ኡጋንዳን) በመወከል ከግብጽ ጋር በ1929 ባደረገችው ስምምነት ወደ ግብጽ የሚደርሰውን የዓባይን ውሃ መጠን የሚቀንስ ማንኛውም ተግባር በወንዙ ላይ እንደማይከናወን ቃል ገብታለች፡፡ ስምምነቱ በእንግሊዙ የግብጽ ኮሚሽነር እና በግብጽ የሚንስትሮች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሞሃመድ መሃመድ ፓሻ መካከል የተፈረመ ሲሆን በአስዋን አናሳው ግድብ ያለው ውሃና ወንዙ ከጥር እስከ ሐምሌ በየዓመቱ የሚኖረው ፍሰት ሙሉ ለሙሉ ለግብጽ ጥቅም እንዲውል ደንግገዋል።

መነሻ በሆነው የናይል ኮሚሲዮን ሪፖርት መሠረት ሱዳን በየዓመቱ 4 ቢ.ኩ.ሜ. ውሃ ከተጠቀሱት ወቅቶች ውጭ ብቻ ለመጠቀም ሲፈቀድላት ግብጽ ትልቁን ድርሻ በመውሰድ በአማካይ 48 ቢ.ኩ.ሜ. የወንዙን ፍሰት እንድትቆጣጠር አስችሏታል፡፡ በተጨማሪም በወንዙ ላይ የሚከናወኑ ማናቸውንም ፕሮጀክቶች ግብጽ የመቆጣጠርና የመከታተል መብትን ተጎናጽፋለች፡፡

በዚህ ስምምነት መሠረት የእንግሊዝ ግዛት በሆኑት በሱዳን፣ በኬንያ፣ በታንጋኒካና በኡጋንዳ በዓባይና በገባር ወንዞቹ ላይ ወይም መነሻ በሆኑት ሐይቆች ላይ ማንኛውም የግንባታ ሥራ በተለይም ከመስኖና ከኃይል ማመንጨት ጋር የተያያዙ፣ ወይም ግብጽ የሚደርሰውን የውሃ መጠን የሚቀንሱ ወይም በሌላ መንገድ በግብጽ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የግንባታ ሥራዎች ያለ ግብጽ ፈቃድ እንዳይሰሩ ይከለክላል፡፡

የ1929 ስምምነት በቀዳሚነት ሁለት ነጥቦችን የሚመለከት ሲሆን በመጀመሪያ የግብጽን ጥቅም የሚጐዳ ማናቸውም ተግባር የግብጽ መንግሥት ካልተስማማ በቀር በዓባይ ውሃ ላይ ሊከናወን እንደማይችል፤ በሌላም በኩል ደግሞ ወንዙ ላይ የሚካሄድ የግንባታ ተግባር በግብጽ መንግሥት ቁጥጥር ሥር እንደሚከናወን የሚገልፅ ነው፡፡

የአካባቢው ቅኝ ገዢ የነበረችው እንግሊዝ በዓባይ ወንዝ ላይ የበላይነቷን ለማረጋገጥ ኢትዮጵያን በከፊል የውሉ አካል ለማድረግ ሞክራለች፡፡ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ እና እንግሊዝ ግንቦት 15 ቀን 1902 አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ስምምነት ኢትዮጵያ የዓባይን፣ የጣና እና ሰባት ወንዞችን የተፈጥሮ ፍሰት ሙሉ ለሙሉ የሚደፍን ተግባር እንዳታከናውን የሚከለክል ቃል ኪዳን ነው፡፡

> **በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ከፍተኛ ቁጭት እና ሀገራዊ እልህ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ይህ ሀገራዊ ቁጭትና እልህም ጊዜው ፈቅዶ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሕዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ፡፡ የኢትዮጵያውያንም የዘመናት ቁጭት ተመለሰ**

በውሉ የእንግሊዝኛ ቅጂ መሠረት ከታላቅዋ ብሪታኒያ እና ሱዳን መንግሥት ጋር አስቀድሞ ሳይስማሙ፣ በአማርኛው ቅጂ ደግሞ ከብሪታኒያ መንግሥት ብቻ ጋር አስቀድመው ሳይስማሙ ንጉሠ-ነገሥት ምኒልክ ወንዝ ተዳር ዳር የሚደፍን ሥራ እንዳይሰሩ ወይንም ለመሥራት ፈቃድ እንዳይሰጡ ግዴታ ገብተዋል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳን ግብጽ በወቅቱ በሱዳን ላይ የጋራ አስተዳደር ስልጣን (co-domini) የነበራት ቢሆንም ስምምነቱ በዋናነት እንግሊዝ፣ ሱዳንን እና ኢትዮጵያን ብቻ የሚያሳትፍና የሚስገድድ መሆኑ ግልጽ ሆኖ እናገኘዋለን።

ባጠቃላይ በዓባይ ውሃ ላይ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መብት ለግብጽ ያበረከተው የ1929 ስምምነት የግብጽን መንግሥት ወዳጅነት ለማፍራትና የእንግሊዝን የፖለቲካ ጥቅም ለማዳበር የታቀደ እንጂ በተለመደው የኢንተርናሽናል ሕግ ውስጥ ዋጋ እንደሌለው የሕግ ሊቃውንት እና ጸሐፍት በተለያዩ ወቅቶች ሲወተውቱ ኖረዋል፡፡

## 1959 ውል

በእንግሊዝና ግብጽ መካከል የተደረገው እ.ኤ.አ የ1929 ስምምነት በሌላ ፍትሐዊና ሚዛናዊ በሆነ ስምምነት እንዲተካ ግብጽ ጽኑ ፍላጎት ነበራት። በተለይም ስምምነቱ ሱዳንን ያላሳተፈ በሁለቱ ቅኝ ገዢ ሀገራት መካከል ብቻ የተደረገ በመሆኑና በተጨማሪም የሱዳንን ጥቅም በሚጐዳ አኳኋን የተፈጸመ መሆኑን ሱዳኖች አበክረው ያነሱ ነበር፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው እ.ኤ.አ በ1929ኙ ስምምነት ሁለቱ የግርጌ ሀገራት ማለትም ግብጽ በዓመት 48 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ስታገኝ ሱዳን 4 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ብቻ እንዲደርሳት ተደርጎ ነበር፡፡

በዚህ የውሃ ክፍፍል ያልተደሰቱት ሱዳኖች በየጊዜው በርካታ ጥያቄዎችንና ተቃውሞዎችን ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ይህ የሱዳኖች ኩርፊያ ያሰጋቸው ግብጾችም አዲስ ውል ለመፈራረም ተዘጋጁ። በዚህም የ1929ኙ ስምምነት እንዳለ ሆኖ ኅዳር 8 ቀን 1959 ወንዙን የሚከፋፈሉበትን የማሻሻያ ስምምነት ፈርመዋል፡፡ በአዲሱ ስምምነት መሠረት ግብጽ በዓመት 55.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር እንዲሁም ሱዳን በዓመት 18.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር እንዲያገኙ ዕድል የሚሰጥ ነው፡፡

አድሏዊና ኢፍትሃዊ የሆኑት የ1929ኙም ሆነ የ1959ኙ ስምምነቶች ከ86 በመቶ በላይ የናይል ውሃ ምንጭ የሆነችውን ኢትዮጵያን ያገለሉ ነበሩ፡፡ በዚህም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ከፍተኛ ቁጭት እና ሀገራዊ እልህ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ይህ ሀገራዊ ቁጭትና እልህም ጊዜው ፈቅዶ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የሕዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ፡፡ የኢትዮጵያውያንም የዘመናት ቁጭት ተመለሰ፡፡

በሌላ በኩል የወንዙ አካባቢ ሕዝቦች ቁጥር እየጨመረ በመሄዱና ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥቅም ላይ የማዋል ፍላጎታቸው እያደገ በመሄዱ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሌሎች በወንዙ የላይኛው ክፍል የሚገኙ ሀገራት ስለዓባይ ውሃ አጠቃቀም ከዚህ በፊት የተፈረሙትን የቅኝ ግዛት ስምምነቶች በመንቀፍ እንደማይቀበሉት በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ አሳውቀዋል፡፡

እ.ኤ.አ ከ1999 ጀምሮም የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ (Nile Basin Initiative) የተሰኘ ጊዜያዊ የትብብር ማዕቀፍ በማቋቋም አንድ ልዩ የናይል ቤዚን ኮሚሽን ለመመስረትና በዓለም አቀፍ ሕግ ይዘት የተቃኘ ተፋሰስ-አቀፍ ውል ለማዘጋጀት በናይል የሚኒስትሮች ካውንስል በኩል ድርድር ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

ግብጽና ሱዳን የፈረሙት የ1959 ስምምነት የዓባይን ውሃ ሀብት ከአሥር የተፈሰሱ ተጋሪ ሀገሮች ለሁለቱ ብቻ የሚያከፋፍል በመሆኑ ጊዜያዊ መፍትሔ እንጂ ዘላቂ ስምምነት ሆኖ ሌሎቹን ተጋሪ ሀገሮች ለማስገደድ እንደማይችል የሕግ ሊቃውንቱ እና ጸሐፍት ሲወተውቱ ኖረዋል፡፡ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ጨምሮ በሁሉም ዘንድ የሚነሳ ነው፡፡

ኢትዮጵያም ይህንኑ መነሻ በማድረግ ከግብጽ እና ሱዳን ጋር ተከታታይነት ያላቸውን ድርድሮች በማድረግና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ አካሄድን በመከተል ዛሬ ላይ ደርሳለች፡፡ እግረ መንገዷንም የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ከ94 በመቶ በላይ በማድረስ መጪውን ብሩህ ተስፋ በመጠባበቅ ላይ ትገኛለች፡፡

ሆኖም ከድሮ እስከ ዘንድሮ ውዝግብ የማያጣው የዓባይ ውሃ ከሀገርና አህጉር አልፎ ዓለም አቀፍ መወያያ እስከመሆን ደርሷል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም በፀጥታው ምክር ቤት የታየ አነጋጋሪ አጀንዳ ለመሆን በቅቷል፡፡ ይህም ሆኖ ግን አይበገሬዎቹ ኢትዮጵያውያን የግድቡ ግንባታ ዳር እስኪደርስ ድረስ የሚያግዳቸው ተራራ፤ የሚያዳልጣቸው ቁልቁለት አይኖርም፡፡

**ጽሑፉን ስናዘጋጅ- ‹‹የዓባይን ወንዝ የባለቤትነትና አጠቃቀም ዙሪያ የሚነሱ የሕግ እና የፍትህ ጉዳዮች›› በሚል ርዕስ በታደለ ተካ እና በአሮን ደጎል የተሰናዳውን ጥናታዊ ጽሑፍ በመነሻነት ተጠቅመናል፡፡**

# ተናጋሪው ዶሴ

# መጠጥ ቤት ውስጥ የተፈጠረ ጊዜያዊ ፀብ ያስከፈለው ዋጋ

አስመረት ብስራት

ሐምሌ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ነበር። ክረምቱ ከባተ አስረኛው ቀን ላይ ደርሷል፡፡ ክረምቱ ጫን ያለ ነበር። በወሩ የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ከፍተኛ የሆነ ነጎድጓዳማና በረዶ የቀላቀለ ዝናብ እየዘነበ ስለሰነበተ ሰው ብርዱን ለማጥፋት መላዬ የሚለውን በሙሉ እየሞከረ ነው፡፡ ያለ የሌለ ልብስ ደራርቦ ወደ ጉዳዩ ጣደፍ ጣደፍ ከሚለው ሰው አንስቶ ከአልጋው መውጣት እስካቃተው ሰው ድረስ ሁሉም ከብርዱ አመልጥበታለሁ የሚለውን መላ በሙሉ ይሞክራል።

በየመንገዱ ዳር የተቀመጡት ሐምሌ በብዙ ነገሩ የክረምትን ውበትና ጣዕም የሚያሳየን ሰዎችም ይታያሉ፡፡ ክረምትን ተከትለው የሚመጡት ለመብል የሚውሉት እነ በቆሎ፣ በለስና ስኳር ድንች ወዘተ ብርዱ ላራቆተው ሆድ መሙያነት ያቀርባሉ። ሐምሌ ክረምት ለማሰላሰያ ዕድል የሚሰጥ ወርም ነው። ለገበሬው የምርት ጊዜ፤ ተማሪዎችና መምህራን ሌሎችም ባመዛኙ የሚያርፉበት በመሆኑ የጽሞና ጊዜን እንዲያሳልፉ ዕድል ይሰጣል። ክረምት ሥራ የሳጣቸው የግንባታ ሠራተኞችም እንዲሁ ቤት አካባቢ መታየታቸው የተለመደ ነው።

ወሩ ሰማዩ በደመና የሚሸፈንበት ለምድርም ዝናብ የሚዘጋጅበት ሣር በተራሮች ላይ የሚበቅልበት ለምለሙ ሁሉ ለሰው ልጆች ጥቅም የሚውልበት ነው ክረምት፡፡ በረዶውና ውሽንፍሩ ብርቱውም ዝናብ በምድር ላይ የሚወድቁበት ነው። ከመብሉም አልፎ ጠንካራ መጠጥንም ለብርዱ ማጥፊያ የሚጠቀሙትም አልታጡም።

የዛሬዎቹ ባለ ታሪኮቻችንም የከበደውን ክረምት ማምለጫ ከቅዝቃዜው መሸሻ ይሆናል ሲሉ አረቄ ቤት ተቀምጠው በጠንካራው አልኮል ብርዱን ሊያባረሩ የመረጡ ወጣቶች ናቸው። ለዚህ ታሪክ መነሻ ሃሳብ እንድናገኝ የተባበሩንን የአዲስ አበባ ፖሊስ የመዝገብ ቤት ሠራተኞችን ከልብ እያመሰገንን ታሪኩን እንዲህ ይዘንላችሁ ቀርበናል።

### ምሽቱን መኮንን አረቄ ቤት

በነጩ የያዘው ዝናብ ክፍ ክፍ ሲል፤ ደግሞ ጠንከር፤ ደግሞ እንደማባራት ሲል ነው የዋለው። የክረምቱን ማየል ተከትሎ ረገብ ያለው የግንባታ ሥራ ሥራአጥ ያደረጋቸው ወጣቶች ቀኑን ሙሉ ተኝተው ውለው እኩለ ቀን ሲያልፍ ከቤት ይወጣሉ። ያገኟትን ቀማምሰው ምሽት ላይ የበረታውን ብርድ ለማባረር ብሎም ሰዓት ለማሳለፍ ብለው ከመኖሪያቸው አቅራቢያ የሚገኝ አረቄ ቤት ገቡ።

ጠበብ ያለችው አረቄ ቤት ከአፍ እስከ ገደፉ ሰው ሞልቶታል፡፡ የቤቱን ግድግዳ ተከትለው የተደረደሩት አግዳሚ ወንበሮች ላይ ተጠባብቀው የተቀመጡት ጎረምሶች ብርዱን በትቅቅፋቸው የሚያባርሩ ይመስላሉ።

ከቤቱ መካከል ትርክክ ብሎ የተያያዘ የከሰለ ምድጃ ይታያል። ምድጃው ዳርና ዳር ተቀምጠው አጠገቡ በተቀመጠችው ልጅ እጅ እየተገላበጡ የሚጠበሱት በቆሎዎችን ተራቸውን እየጠበቁ እየከፈሉ ለሚወስዱት ጠጪዎች እየተዳረሱ ነው። የጠጪውን እጅ እየተመለከቱ ቶሎ ቶሎ የሚቀዱት ተፍ ተፍ የሚሉት ወጣት ሴቶችም ቤቱን ድምቀት አላበሰውታል። ከቤቷ አቅም በላይ የተለቀቀው ሙዚቃም የደጁን ብርድ ሙሉ በሙሉ እንዲረሱት አድርጓቸዋል።

ጠባቧ አረቄ ቤት ውስጥ የተቀቀለ ድንች፤ የተቀቀለ እንቁላል፤ ቆሎና ንፍሮ በመያዝ ወጣ ገባ የሚሉት ትንንሽ ልጆች በአረቄ ባዶውን የቀረ



ሆዳቸውን ታገስ እያደረጉ መለስ ቀለስ ይላሉ።

ሥራ ስላልነበራቸው በጊዜ አረቄ ቤት ገብተው ብዙም ሳይመሽ ሞቅ ያላቸው ወጣቶች ያንንም ያንንም እያነሳሱ ይጨዋወታሉ፡፡ ይከራከራሉ ጠብ ላይ ደርሰውም መለስ በማለት ጨዋታውን ይቀይራሉ። የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሱ ከሚጨዋወቱት መካከልም ወጣቶቹ ሞገስ ይገዙን ምትኩ ይመር ይገኙበት ነበር። ወጣቶቹ ብዙም የጠበቀ ግንኙነት ባይኖራቸውም በተደጋጋሚ በመተያየታቸው የተነሳ የአንገት ሰላምታ ይለዋወጣሉ። እንኳን ለፀብ የሚያደርስ ቂም ሊኖራቸው ይቅርና ለፍቅር የሚሆንም ትውውቅ አልነበራቸውም።

### የወጣቶቹ እሰጣ ገባ

ሰሞኑን ሥራ ማጣቱም፤ ወጪውም አመል ነሰቷቸዋል። የእለት እለት እየሰሩ የእለት እለቱን የሚኖሩት ወጣቶቸ ብዙም ሳይዘጋጁ ነበር ክረምቱ የደረሰባቸው። ያላቸውን አብቃቅተው ሥራ እስኪያገኙ ለመቆየት ግማሹን ቀን በመኝታ ነበር የሚያሳልፉት። ከዛም በቀን አንዴ በልተው አንድ ሁለት መለኪያ አረቄ እላዩ ላይ ደፍተው መልሰው ጥቅልል ማለት ልማዳቸው ነው።

የእለቱ ብርድ ከወትሮው ለየት ያለ ስለነበር ከተሟሟቀችው አረቄ ቤት መውጣት ያልፈለጉት ወጣቶች አንድ ሁለት እያሉ ደጋግመዋል። ጨዋታን ጨዋታ እያነሳ ስለ ብዙ ጉዳይ ሲያነሱ ቆይተው ሁለቱን የማያግባባቸው ጉዳይ መወራት ጀመሩ።

በንግግር አለመግባባት ውስጥ የገቡት ወጣቶች ጉዳዩን እንዳያከሩት ሌሎች ጣልቃ ቢገቡም ንግግሩ እየተሟሟቀ ከመጠጥ ጋር ተደምሮ አለመግባባታቸውን ከፍ አደረገው። ያን ጊዜ ቆመው ለመተናነቅ ሲዳዱ፤ ገላጋይ ሲይዛቸው ቆይቶ ድንገት አንደኛው እመር ብሎ አንዱ ላይ ተከመረበት።

ብርዱን ለመሸሽ ከገቡባት አረቄ ቤት ውስጥ ኃይለኛ ትርምስ ተነሳ። ከተጣላው ሰው ሌላ የተቀሩትን ሰዎች ጨምሮ ምትኩ ይመር የተባለው ሲሳደብ እና ሲዝት የተመለከተው ሞገስ ይገዙ የተባለው ወጣት «ተው እንዲህ አትበል» ሲለው ነበር ያልተሰበው ነገር የተከሰተው።

«ፀብህ ከእኔ ጋር ነው ሌሎቹን አትሳደብ» ብሎ የተናገረውን ሞገስ ይገዙን «አንተ ምናገባህ» በማለት ግብግብ ሲያያዙ ምትኩ በያዘው ቢላዋ በስለት ጀርባው ላይ በመውጋት በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ እንዲያልፍ ሆነ።

ያች በዘፈንና በጨዋታ ሞቃ የነበረችው አረቄ ቤት ደብልቅልቋ ወጣ። ያ ሳቅና ሁከታ በለቅሶና በዋይታ ተቀየረ። ያን ጊዜ በስካር የሰው ሕይወትን ያጠፋው ወጣት ትርምሱ ሰምተው በመጡ ፖሊሶች ቁጥጥር ስር ዋለ።

### ፖሊስ

የእለት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የነበሩት ፖሊሶች ከብርዱ ጋር በመተናነቅ የአካባቢውን ፀጥታ ሊያስጠብቁ ወዲያ ወዲህ እያሉ ነበር። አካባቢውን እየጠበቁ የነበሩት ፖሊሶች ድንገት ሙዚቃና ሁከት ቀርቶ በለቅሶና በዋይታ ሲተካ ጉዳዩን ለማየት በፍጥነት በቦታው ደረሱ።

ሐምሌ 10 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ጉርድ ሾላ ሰዓሊተ-ምህረት እየተባለ ከሚታወቀው አካባቢ መኮንን አረቄ ቤት ውስጥ ሲመለከቱ አንዱ ወጣት ጀርባው በደም ተለውሶ ተዘርግቷል። ሌላኛው ወጣት ደግሞ በእጁ ደም የተለወሰ ቢላዋ ይዞ ቆሞ ይመለከቱታል።

ወንጀል ሲሰራ ወዲያው ርምጃ መውሰድ ሥራቸው የሆነው ሕግ አስከባሪዎች ተጎጂውን ወደ ሆስፒታል በመላክ ጥቃት ያደረሰውን ወጣት ወደ ፖሊስ ጣቢያ አደረሱ።

ፖሊስ ወጣቶቹ የተጣሉበትን ጉዳይ በመመርመር፤ ከዓይን ምስክሮች ቃል በመቀበል፤ የሕክምና ማስረጃና የተጠርጣሪውን የእምነት ክህደት ቃል አንድ ላይ አድርጎ መረጃውን አደራጅቶ ጨረሰ። የተጠናከረውንም መረጃ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ አቀረበ።

### የአቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ከሟች ጋር በተፈጠረ ወቅታዊ አለመግባባት ምክንያት በቢላዋ በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርገሃል ባለው ተከሳሽ ላይ ክስ መሠረተ።

ይህን አሰቃቂ ድርጊት የፈፀመው ምትኩ ይመር የተባለው ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በዐቃቤ ሕግ ክስ አቅርቧል።

በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ የግድያ ወንጀሎችን እንደ አገዳደል ባህሪያቸው ከባድ፣ ቀላል፣ ተራ እና በቸልተኝነት የሚፈጸሙ በማለት የደነገገ ሲሆን ተራ የሆነ ግድያ ማለት ከባድ ግድያ ሥር የተቀመጡ እንደ ሰውን ለመግደል አስቀድሞ ማሰብና መዘጋጀት፣ ያገዳደል ሁኔታው ላይ የታየ የተለየ ጨካኝነት እና አደገኛነት፣ ለመግደል የተጠቀመው መሳሪያ እና ዘዴ ከባድ የማያስብለው ያልሆነ እንዲሁም ቀላል ግድያን ለማቋቋም እንደተዘረዘረው በደም ፍላት ወይም ከመጠን ያለፈ ሕጋዊ መከላከል እና መሰል ከፊል ይቅርታ የሚሰጥ ያልሆነ በሁለቱ ስር የማይወድቅ ሲሆን የወንጀል ሕጋችን ተራ የሆነ የሰው ግድያ በማለት ያስቀምጠዋል መሆኑን ዐቃቤ ሕግ አብራርቷል።

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ተከሳሽ ሰውን ለመግደል አስቦ ሐምሌ 10 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ጉርድ ሾላ ሰዓሊተ-ምህረት እየተባለ ከሚታወቀው አካባቢ መኮንን አረቄ ቤት ውስጥ ሟች ሞገስ ይገዙን በተፈጠረ ወቅታዊ አለመግባባት ተከሳሽ ሲሳደብ እና ሲዝት ሟች ተው እንዲህ አትበል ሲለው አንተ ምናገባህ በማለት ግብግብ ሲያያዙ ተከሳሽ በያዘው ቢላዋ በስለት ጀርባው ላይ በመውጋት በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ በፈፀመው ተራ ሰው መግደል ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶበታል።

### ውሳኔ

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት የቀረበው ተከሳሽ የተከሰሰበት ክስ በችሎት ተነቦለት የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቦ ክሱን በበቂ ሁኔታ ያስረዳ ሲሆን ፍርድ ቤቱ እንዲከላከል በሰጠው ቀጠሮ መሠረት 2 የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ቢያሰማም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችንና ማስረጃዎችን ማስተባበል ባለመቻሉ ተከሳሹ ይከላከል በተባለበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነህ ብሎታል።

ፍርድ ቤቱም ግንቦት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ባስቻለው ችሎት በተከሳሹ ላይ 3 የቅጣት ማቅለያዎች ተይዘውለት በእርከን 31 ስር በማሳረፍ ተከሳሽን ያርማል ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያስተምራል ያለውን በ13 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ እና ለ3 ዓመት ከሕዝባዊ መብቶቹ ታግዶ እንዲቆይ ሲል ወስኖበታል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ልብ ውልቅ - በመንገድ ላይ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

መሀል መንገድ ላይ ነኝ፡፡ ዛሬም በርካታ መንገደኞች ይተራመሳሉ፡፡ እንዲህ መሆኑ ለአካባቢው ብርቅ አይደለም። በየቀኑ እየተጋፉ የሚያልፉ፣ እያለፉ የሚለፈልፉ፣ እየለፈለፉ ሰላም የሚነሱ ባለጉዳዮች ብዙ ናቸው፡፡ ‹‹ወዳጆቼ! ›› እነዚህን ሰዎች ‹‹ባለጉዳዮች›› ማለቴ በምክንያት ነው፡፡ ሁሉም በሚባል መልኩ የራሳቸውን ሃሳብ ብቻ የሚዘውሩ ስለሆኑ።

አንዳንዴ ከትርምሱ ጋር የነሱ ጉሽማና ወከባ ይረብሻል፡፡ አብዛኞቹ የራሳቸውን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ አይሆኑት የለም፡፡ ከነዚህ መካከል ጥቂቶቹ ሲሻቸው ከሰው ጆሮ ተጠግተው፣ አልያም ራቅ ብለው የሚሉትን ይላሉ፡፡ ሁሉም በአንድ ቦታና ሰአት የተለያየ ሀይለ ድምጽ ባወጡ ጊዜ ውስጥን አንዳች የሆነ ስሜት ይጋፋል።

በስፍራው ተጠጋግተው፣ ተደጋግፈው የሚያስተጋቡት ዥንጉርጉር ድምፅ የሚፈጥረውን ረብሻ ማሰብ አይቸግርም፡፡ ሁሌም በየግላቸው ድምጻትና ዜማ አንዱ ከሌላው በልጦ ለመሰማት የሚያደርጉት ፉክክር አስገራሚ ነው፡፡ እኔን የሚደንቀኝ ግን ከደመቀው ትርምስ ነጠል ብለው ጉዳያቸውን የሚያራውጡ ሰዎች ድርጊት ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች ዓላማቸውን የሚያሳኩት በተለመደው አይነት የገበያ ግንኙነት አይደለም፡፡ ሁሌም ወደ መንገደኛው ተጠግተውና እግረኛውን አስቁመው በግልጽ የሰውን ጊዜ ይነጥቃሉ፡፡ ሃሳብን ሰርቀው በይሉኝታ ያሸማቅቃሉ፡፡

ሰዎቹ ትኩረት ያገኙ ሲመስላቸው በዋዛ አይላቀቁም፡ ፡ ወዲያው የያዙትን ዕቅድ ይዘረጋሉ። ራዕይና ተልኳቸውን እያስረዱም ግባቸውን ሊያስቃኙ ይጣደፋሉ፡፡ እኔ በየመንገዱ እንዲህ አይነቶቹ አድርቆች ስለሚደጋገሙብኝ ሁሌም ‹‹ልብ ውልቅ›› እላቸዋለሁ፡፡

አሁንም የእግረኞች መንገድ ላይ ነኝ። ካሰብኩት ለመድረስ ብጣደፍም ገና ከመንገዱ ጫፍ አልተጠጋሁም። ከጎን፣ ከኋላዬ የሚገፉፉኝ በርክተዋል፡፡ በድንገት አንድ ሰው ከፊት ለፊቴ ብቅ ሲል ዓይን ለዓይን ግጥም አልን። ከሚጨንቀው ትርምስ ለመውጣት እያሰብኩ ነበርና እንዳያስቆመኝ ፈራሁ፡፡ ስጋቴ ትክክል ነበር፡፡ ሰውዬው በተለየ ሰላምታ እየተሽቆጠቆጠ ሊያናግረኝ እንደሚሻ ነገረኝ፡፡

እውነት ለመናገር አለባበሱ የአምባሳደር ያህል ነው። በሙሉ ልብሱ ላይ ሸብ ያደረገው ባለቀለም ከረባቱ ድንቅ አድርጎ አስውቦታል፡፡ ጊዜ እንደሰጠሁት ሲረዳ በእጁ የያዘውን ፋይል መሳይ አጀንዳ እየገለጠ ንግግሩን ጀመረ።

ያለምንም ማቋረጥ እያነበነበ ቢሆንም ከቃሉ አንዳች ሃሳብ አይስትም፡፡ በሽምደዳ ያጠናው የሚመስለውን ጉዳይ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያንበለብለዋል፡፡ በየመሀሉ ቆም ይልና የሚናገረው በትክክል እየተደመጠለት መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ በልፍለፋው ልቤ ውልቅ ቢልም እየተገረምኩ በትእግስት ሰማሁት፡፡

‹‹ወዳጆቼ!›› እናንተንም እንደኔው ካስገረማችሁ ሰውዬው ያለኝን ላካፍላችሁ፡፡ የዚህ ሰው ዓላማ አንድ ታዋቂ ሪል ስቴትን ለነዋሪዎች ለመሸጥ በየመንገዱ ሰዎችን ማግባባትና ገበያን መሳብ ነው። እሱ እንዳለኝ ከሆነ ሪል ስቴቱ በከተማዋ ካሉት ሁሉ በዋጋ፣ በጥራትና በታማኝነት የላቀ የሚባል ነው፡፡ ይህን የመኖሪያ ቤት ፈጥኖና መርጦ የሚገዛ ቢኖር በእጅጉ ያተርፋል፤ በኑሮው ረክቶ በህይወቱ ይደሰታል፡፡

በጣም ያስገረመኝ ቢኖር ወደር የለሹን የመኖሪያ መንደር ለማስተዋወቅ ሰውየው በእግራቸው የሚራመዱ ሰዎችን እያደነ መምረጡ ነው፡፡ እንተዛዘብ ከተባለ እኮ ከእነዚህ ሰዎች አብዛኞቹ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ እንኳንስ ዘመናዊ ቤቶችን ተሻምተው ለመግዛት፣ ለአንገት ማስገቢያ ጎጇቸው የኪራይ እጅ ያጠራቸው፣ ችግር አብዝቶ የፈተናቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እኔና መሰሎቼም ብንሆን ሪል ስቴት ይሉትን ጉዳይ በታሪክ ካልሆነ በአካል አናውቀውም፡፡ እስከዛሬም በተግባር ልንሞክረው አላሰብንም፡፡ ለምን ከተባለ ማንም የሚኖረው በአቅምና በልኩ ስለሆነ፡፡ ይህ ሰው ግን ምን አሳይቶት፣ በእግሩ የሚኳትነውን መንገደኛ ምርጫው እንዳደረገ አይታወቅም፡፡

እንዴትና በምን አግባብ ይሆን ሌት ተቀን ኑሮ የሚያናውዘው በእግር ኳታኝ መንገደኛ ሪል ስቴቱ የሚያሳስብ የሚያስጨንቀው? ሰውየው ግን የምርጫ አቅጣጫውን በኑሮ ከበለጸጉት መንደር ማድረግን ያሰበ አይመስልም፡፡

በዘመንኛ መኪኖች የሚፈሱትን፣ በቅንጡ ኑሮ የሚቀማጠሉትን ተፈላጊዎች ተራምዶ ኑሮ አንገታቸውን ባስደፋቸው ሰዎች መሀል ልብ ሲያወልቅ፣ ይውላል፡፡ በእኔ እሳቤ ግን ይህ አይነቱ አታካች ‹‹ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ›› ይሉት አይነት ነው፡፡ አንድም ቀልድ፣ሌላም ኪሳራ ስለሆነ፡፡

መቼም በእግርዎ መራመድ ከጀመሩ የሚገጥምዎት ብዙ ነው፡፡ አንድ አፍታ አልፈውት በሚሄዱት መንገድ ልብ የሚያወልቅና አብዝቶ የሚያሰለች አይጠፉም። አንዳንዳዴ ከምታዘባቸው አጋጣሚዎች ውስጥ አስተውሎት የጎደላቸው እውነታዎች ያጋጥሙኛል፡፡ ይህኔ ሰው ምን ነክቶታል ከማለት ባለፈ ውስጤ አብዝቶ ይሸማቀቃል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሚባል ሁኔታ በየመንገዱ የግል ሃይማኖታቸውን የሚሰብኩ ሰዎች በዝተዋል፡፡ በእኔ እይታ እስካሁን ይህን በማድረጋቸው መብታቸው ሲጣስ ሃሳባቸው ሲታፈን አላጋጠመኝም፡፡ ችግሩ እንዲህ መሆኑ ላይ አይደለም፡፡ ከእነዚህ መሀል አንዳንዶቹ አብዝተው የሚይዟቸውን በራሪ ወረቀቶች ላገኙት ሁሉ ያድላሉ። ማደል ሲባል ደግሞ በሰዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ አይምሰላችሁ፡፡

ወረቀት አዳዮቹ የእጃቸውን አሳልፈው ከመስጠት ባለፈ መንገደኞችን አስቁመው መወትወት ልማዳቸው ነው። አልገባቸው ይሆናል እንጂ ከሚያናግሯቸው አብዛኞቹ የእነሱን ዕምነት የማይከተሉ ሊሆኑ ይችላል። ይህ አይነቱ ያልተገባ አጋጣሚ ባስ ባለ ጊዜ ዱላ የሚያማዝዝ ጠብን ሊያጭር ይችላል፡፡

እንዲያም ሆኖ አሁንም ድረስ ልብ ያልተባለው ስህተት ሳይታረም መቀጠሉን ልብ ይሏል፡፡ በመንገድ ላይ ከዚህም የባሰ ሃይማኖታዊ ስህተቶች ሲፈጸሙ ይስተዋላል።

አንዳንዶች የቅዱሳንን ስነ ስዕል አሳትመው በየጎዳናው ጥግ ይቆማሉ፡፡ እንዲህ ማድረጋቸው አላፊ አግዳሚውን በመወትወት በሚሰጡት ስዕል ያሰቡትን ገንዘብ ለመቀበል ነው፡፡ አስተውላችሁ ከሆነ እንዲህ አይነቶቹ ይሉኝታና ትዕግስትን አያውቁትም፡፡

ድንገት ባገኟችሁ ጊዜ ከኋላ ከፊት እየተከተሉ ያደርቋችኋል፡፡ ጉዳዩን እንዳልሰማ ለማለፍ ከሞከራችሁ ደግሞ በዋዛ አትለቀቁም፡፡ ትከሻችሁን እየነካኩ፣ ልብሳችሁን እየጎተቱ፣ ሰላም ይነሷችኋል። ለመሸጥ የሚጠቀሙት ቃላትና ማግባባት ደግሞ ለየት ይላል፡፡

አሁንም አስገራሚው ጉዳይ ይህ ብቻ አይደለም። እነሱ በውትወታ ‹‹ካልገዛችሁን›› የሚሉትን ምስል ለማን እንደሚያደርሱት አያስተውሉም፡፡ ጉዳዩ ገንዘብ እስካመጣላቸው ድረስ መንገደኛው ሁሉ ቢገዛቸው፣ ቢወስድላቸው ይወዳሉ፡፡ እኔ ግን ይህ አይነቱ ልማድ ከስህተት አልፎ የሌሎችን መብት እንደመጋፋት ይቆጠራል ባይ ነኝ ፡፡

አንዳንዴ እነዚህን መሰል እንከኖች ሲያጋጥሙኝ ከሌሎች ጋር አለመግባባቶች እንዳይፈጠሩ እሰጋለሁ። ሁሉም ሰው በተፈጥሮው ታጋሽ ነው ማለት አይደለም። በተለይ ሃይማኖታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማስተዋል ያለመኖሩ ስሜታዊነትን ሊያስከትል ይችላል ፡፡ ይህ አይነቱ እውነት እየተስተዋለ ካልተከወነ ጉዳቱ ከአንድ አልፎ ለብዙኃን ይተርፋል፡፡

የመንገድ ላይ ልብ አውልቆች ብዙ ናቸው፡፡ በየዕለት እንቅስቃሴችን ለምደናቸው ካልሆነ በቀር አሰልቺነታቸው፣ መብትና ፍላጎትን ጭምር መጋፋታቸው አይቀሬ ነው። አንዳንዴ እንደዋዛ ቆጥረን የምንለምዳቸው አጋጣሚዎች ውሎ አድሮ ጉዳታቸው ሊከፋ ይችላል፡፡

ጥቂቶች በሚፈጽሙት የስህተት መነሻም ብዙኃን የሚወቀሱበትና በርካቶች የሚጎዱበት አጋጣሚ ይኖራል። የመንገድ ላይ ልብ አውልቆች፣ መነሻና መድረሻቸው የግላቸውን ገቢ በማጋበስ የሌሎችን ኪስ ማራቆት ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ እነዚህ ግብር የማይከፍሉ፣ ይሉኝታና ክብር የሌላቸው ወገኖች ግን መስመር ሊበጅላቸውና አደብ ሊገዙ ይገባል፡፡ የግል አስተያየቴ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## በቻይና የቀዶ ህክምና እየተደረገላቸው የነበሩትን ህመምተኛ የደበደበው ዶክተር ቁጣን ቀሰቀሰ

በቻይና የቀዶ ህክምና እያደረገላቸው የነበሩትን ህመምተኛ በቡጢ የደበደበው ዶክተር ቁጣን ቀሰቀሰ። የቻይና ባለስልጣን በሆስፒታሉ የተከሰተውን ድብደባ አስመልክቶ ምርመራ መክፈታቸውን አስታውቀዋል። በዚህ ሳምንት በቻይና ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተለቆ በርካቶች ያዩት ቪዲዮም ከፍተኛ ቁጣን ቀስቅሷል።



ሆስፒታሉን በበላይነት የሚያስተዳድረው ኤየር ቻይና ድብደባውን ፈጽሟል ያለውን የቀዶ ህክምና ባለሙያን እንዲሁም ድርጊቱ የተፈጸመበትን የሆስፒታሉን ዋና ሥራ አስፈጻሚም አሰናብቷል። ቪዲዮው የዓይን የቀዶ ህክምና እየተደረገላቸው የነበሩት ህመምተኛ ሶስት ጊዜ በዶክተሩ በቡጢ መመታታቸውን ያሳያል።

የዓይን ሆስፒታሎችን በበላይነት የሚያስተዳድረው ኤየር ቻይና ክስተቱ በአውሮፓውያኑ 2019 በደቡብ ምዕራባዊቷ ቻይና በጉይጋንግ ሆስፒታል የተፈጸመ ነው ብሏል። ህመምተኛዋ የ82 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ሲሆኑ “በቀዶ ህክምናው ወቅት በተሰጣቸው ማደንዘዣ ምክንያት መቁነጥነጥ እየተሰማቸው” ነበር።

እጃቸውን እንዲሁም ዓይናቸውን በርካታ ጊዜ ማንቀሳቀሳቸውንም መግለጫው ጠቅሷል። ግለሰቧ ዶክተሩ ያስጠነቅቃቸው የነበረውን የማንዳሪን ቋንቋም ስላልገባቸው ግራ ተጋብተው እንደነበር የተገለጸ ሲሆን፤ “በድንገተኛ ህክምና ላይ የነበሩት ህመምተኛ በከፋ ሁኔታ ተይዘዋል” ተብሏል።

የአካባቢው ባለስልጣናት ህመምተኛዋ በድብደባው ጉዳት ደርሶባቸው እንደነበር እና ግንባራቸውም በልዞ እንደነበር አስረድተዋል።ከቀዶ ህክምናውም በኋላ የሆስፒታሉ አስተዳዳሪዎች ለህመምተኛዋ ይቅርታ ጠይቀው 500 ዩዋን (70 ዶላር) በካሳነት መስጠታቸውንም የህመምተኛዋ ልጅ ለሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ተናግሯል።

በተጨማሪም የእናቱ ግራ ዓይን እንደታወረ የገለጸ ሲሆን፤ ከዚህ ክስተት ጋር ስለመያያዙ ግልጽ አይደለም። ኤየር ቻይና ሆስፒታሉ ስለ ጉዳዩ ለዋናው መስሪያ ቤት ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበት ነበር። ሐሙስ ዕለትም የጉይጋንግ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ መታገዳቸውን እንዲሁም የሆስፒታሉ ዲን የሆነው የቀዶ ህክምና ባለሙያም “ሌሎች ያልተጠቀሱ ጥሰቶችን ጨምሮ በተደጋጋሚ በፈጸመው ከባድ ጥሰቶች” መባረሩ ተነግሯል።

ምንም እንኳን ክስተቱ የተፈጸመው በአውሮፓውያኑ 2019 ቢሆንም የህዝብ ትኩረት ያገኘው ታዋቂዋ ቻይናዊት ዶክተር አይ ፌን ድብደባውን የሚያሳይ የሲሲሲቲቪ ቪዲዮ ማጋራታቸውን ተከትሎ ነው። ዶክተሯ በውሃ ላይ የተከሰተውን የኮቪድ ወረርሽኝን በተመለከተ ህዝቡን ካስጠነቀቁ የዶክተሮች ቡድን መካከል አንዷ ሲሆኑ፤ ይህንንም ቪዲዮ ሁለት ሚሊዮን ተከታዮች ባላቸው ዌይቦ በተሰኘው የማህበራዊ ሚዲያ ገጻቸው አጋርተዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## በፕራግ ዩኒቨርሲቲ 14 ሰዎችን የገደለው ታጣቂ ተገደለ

በቼክ ሪፐብሊክ መዲና ፕራግ በሚገኝ ዩኒቨርሲቲ አንድ ታጣቂ ተኩስ ከፍቶ 14 ሰዎችን ሲገድል 25 ማቁሰሉን ባለስልጣናቱ ተናገሩ። ጥቃቱም በዘመናዊ የቼክ ታሪክ አስከፊው ነው ተብሏል።



የ24 ዓመቱ ታጣቂ በታሪካዊቷ ፕራግ በሚገኘው ቻርለስ ዩኒቨርሲቲ ያደረሰውንም ጥቃት ተከትሎም “መወገዱን” ፖሊስ አስታውቋል። ጥቃቱ እየተፈጸመ በነበረበት ወቅት የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የቻሉትን መንገድ ተጠቅመው ክፍሎቹን እንዲዘጉ ተነግሯቸዋል።

የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ፒተር ፊያላ ሐሙስ ዕለት የደረሰውን “አሳዛኝ ክስተት” ተከትሎም የነበራቸውን ዕቅዶች መሰረዛቸውን አስታውቀዋል።ጥቃቱ የተጀመረው በዩኒቨርሲቲው የስነ ጥበባት ህንጻ በአገሬው ሰዓት አቆጣጠር ከሰዓት ዘጠኝ ሰዓት ላይ ነው።በኋላም ላይ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የወጡ ቪዲዮዎች እንደሚያሳዩት አንዳንዶች ከህንጻው ፎቅ ሲዘሉ የታዩ ሲሆን የተኩስ ድምጽም ይሰማል።

በሌላ ቪዲዮ ላይ ደግሞ በርካታ ሰዎች በቱሪስቶች ታዋቂ ከሆነው አካባቢ በፍርሃት ሲሸሹ ይታያሉ። ታጣቂው የዩኒቨርሲቲው ተማሪ እንደነበር የሀገሪቱ ፖሊስ አዛዥ እና የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሐሙስ እለት በሰጡት አጭር መግለጫ አስረድተዋል።ከፕራግ 21 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከምትገኝ መንደር እንደመጣም ተነግሯል። የታጣቂው አባት ጥቃቱ ከመድረሱ በፊት ሐሙስ ቀደም ብሎ ሞተው ተገኝተዋል። የታጣቂው ዓላማ ለጊዜው አልታወቀም።

በጥቃቱ ምንም አይነት የፖሊስ አባላት እንዳልተጎዱም የቅድሚያ መረጃዎች እንደጠቆሙ ባለስልጣናቱ ተናግረዋል። ታጣቂው ባለፈው ሳምንት በፕራግ አቅራቢያ በሚገኝ ጫካ ውስጥ ሞተው የተገኙ ሁለት ሰዎችን ሳይገድላቸው እንዳልቀረም ፖሊስ ጥርጣሬ አለኝ ብሏል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር የሆኑት ሰርጌይ ሜድቬዴቭ ጥቃቱ ሲጀመር ከዩኒቨርሲቲው አዳራሽ ውስጥ በአንዱ እንደነበሩ ለቢቢሲ ተናግረዋል። “በወቅቱ እያስተማርኩ ነበር፡፡ እናም መጀመሪያ ላይ ምን እንደተፈጠረ በትክክል አልተገነዘብኩም። ድምጾች ይሰሙ ነበር። እኔ አትኩሮቴ በሙሉ ትምህርቱ ላይ ስለነበር ብዙም አልሰማሁም። ተማሪዎቼ በተሻለ ሁኔታ ሰምተውታል” ሲሉም አስረድተዋል።

“ከዚያም አንድ ትልቅ ነገር መከሰቱን ብንረዳም በኢንተርኔት ላይም ሆነ በመገናኛ ብዙኃን ምንም መረጃ አልነበረም። ከዚያም ልዩ ኃይሎች በሩን ጥሰው ገቡና ፈለግ፣ ፈለግ አድርገው ውስጥ እንድንቆይ ነገሩን” ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ከተስፋ መቁረጥ ስመውጣት

አስናቀ ፀጋዬ




ሰዎች በብዙ ምክንያቶች ተስፋ ሊቆርጡ ይችላሉ። ተስፋ መቁረጥ ግን ድሮም አሁንም ያለ ክስተት ነው፡፡ ልዩነቱ ተስፋ የሚያስቆረጡ ምክንያቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸው ነው፡፡ ሰው በኑሮ ውድነት ተስፋ ይቆርጣል። በጤና እጦት ተስፋ ይቆርጣል፡፡ በገቢ ዝቅተኛነት ተስፋ ይቆረጣል፡፡ አግኝቶ በማጣት ተስፋ ይቆርጣል፡፡ በነገሮች አለመሳካት ተስፋ ይቆርጣል። በትዳር ተስፋ ይቆርጣል፡፡ በቃ! ሰው ተስፋ ለመቁረጥ እንኳን ተስፋ እንደሚያስፈልገው እያወቀ ተስፋ ይቆርጣል።

በሰው ልጆች የሕይወት ዑደት ውስጥ ተስፋ የሚያስቆርጡ ሺህ ምክንያቶች እንዳሉ ሁሉ ተስፋን የሚያስቀጥሉና ተስፋ የሚሰጡ ሺህ ምክንያቶች እንዳሉ መረዳት ይገባል። በርግጥ አንዳንዴ ከሰዎች ጋር ላንስማማ እንችላለን፡፡ ሕይወት ተስፋ ሊያስቆርጠን፣ ትምህርታችንና ሥራችን እኛ በፈለግነው መንገድ ላይሄድልን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለከፋው፣ ላዘነና በእጅጉ ተስፋ ለቆረጠ ሰው ሁሉ መድኃኒት እንዳለ ልብ ማለት ይገባል፡፡

መቼም የጓደኛን ሥራ ታውቁታላችሁ። በእናንተ ውስጥ ያለውን ምርጡን ማንነት እንደመስታወት ሆኖ ማሳየት ነው፡፡ ለእናንተም ይህ ጽሑፍ ምርጡን ማንነታችሁን እንድታዩበት ይረዳችኋል። ከፍቶኛል፣ ደብሮኛል፣ ከሰዎች ጋር መስማማት አቅቶኛል፣ እየተጎዳሁ ነው ለምትሉ ሁሉ ጽሑፉ ያግዛችኋል፡፡ እነሆ አምስቱ ተስፋ ሰጪ ነገሮች፡፡

### 1ኛ.ነገሮችን ቁጭ ብሎ መተንተን

አንድ ሰው ከእስር ቤት መውጣት ከፈለገ መጀመሪያ ማድረግ ያለበት እስር ቤት እንዳለ ማወቅ ነው፡፡ ከእስር ቤት እንዴት ልውጣ የሚለው እስር ቤት እንዳለ ካመነ ነው፡፡ አያችሁ! ከተስፋ መቁረጥ መውጣት የምትፈልጉ ከሆነ ተስፋ ያስቆረጣችሁን ነገር ምን እንደሆነ መተንተንና ማሰብ ይጠበቅባችኋል፡፡ ስለችግሩ በደንብ ባወቃችሁ ቁጥር ወደ መፍትሔው የመቅረባችሁ ዕድል ይሰፋል። ነገሩን እንደፈልም አስቡት፡፡ ‹‹እኔን ተስፋ ያስቆረጠኝ የሥራ ጉዳይ ነው፣ የትዳር ጉዳይ ነው፣ የኑሮ ጉዳይ ነው፣ ትምህርቴ ነው፣ ቢዝነስ ነው፣ ምንድን ነው›› ብላችሁ እንደፈልም ሕይወታችሁን እዩት፡፡ አጥኑት፡፡ ጎዶሎው የቱ ጋር እንደሆነ ፈልጋችሁ አግኙት፡፡

ይህንየማድረግዋናውዓላማችግሩንተረድታችሁ መፍትሔ እንድታመጡና በሕይወታችሁ ማስተካከያ እንድታደርጉ ነው። ለምሳሌ የመስታወት ዓላማ አየት አድርጋችሁ የተንጨባረረ ፀጉራችሁን ወይም ነጭ የሆነ የፊታችሁን ክፍል አየት አድርጋችሁ እንድታስተካክሉ ነው፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደ መስታወት ራሳችሁን እዩት፣ አጥኑት፣ ምን እየሆንኩ ነው በሉ፡፡ ለምሳሌ ውሻችሁን ሐኪም ቤት ብትወስዱት ሐኪሙ ራሱ ውሻው ምኑ ጋር እንዳመመው ገምቶና አጥንቶ ለበሽታው መፍትሔ ይሰጣል፡፡

እኛ ሰዎች ብንታመም ግን ስለሕመማችን ራሳችን ነው የምንናገረው፡፡ ትንሽ ራሴን እያመመኝ ነው፣ ሆዴን፣ ጨጓራዬን፣ ኩላሊቴን... ወዘተ እንላለን፡፡ ስለዚህ ችግራችንን የሚፈታው ሌላ ሰው አይደለም። ራሳችን ነን፡፡ የቱ ጋር ነው ችግሩ ብለን ማጥናት አለብን፡፡ የዚህ መፍትሔ ዓላማ ወይም ችግራችንን የመተንተናችን ዋና ዓላማ ‹‹አሃ!›› እንድትሉ ማድረግ ነው፡፡ ‹‹አሃ!›› ለካ እዚህ ጋር ነው የኔ ችግር እንድንል ነው፡፡

### 2ኛ.መቀየር የምትችሏቸው ነገሮች ላይ አተኩሩ

ሰዎችን፣ ነገሮችን፣ ሁኔታዎችን እንዳስቀመጧቸው አያገኟቸውም፡፡ እንዳስቀመጡ የሚያገኙት ስቀው የተነሱትን ፎቶ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ራስዎን መለወጥ ላይ ብቻ ያተኩሩ፡፡ ሰዎችን ልትቀይሯቸው አትችሉም። የሚገርማችሁ ነገር ሚስት በባሏ እናት በጣም ተማረረች። ሁሌ ይጣላሉ ይደባደባሉ፡

፡ መረራት፡፡ ‹‹እኔ እኚህን ሴትዮ ምንድን ነው የማደርጋቸው›› ትላለች። በቃ መስማማት አቃታት፡፡ ከዛ ‹‹ሊሆን የሚችለውና ከባሌ ጋር በሰላም መኖር የምችለው እኚህ ሴትዮ ከሌሉ ነው፤ እናቱ ከሞቱ ነው›› ማለት ጀመረች፡፡ ‹‹እንዴት አድርጌ ገድያቸው ሰላሜን እንደማገኝ›› ትላለች ሁሌ፡፡ ቀጥላ ምክር ለማግኘት አንድ ጠቢብ ሰው ጋር ሄደች፡፡ ጉዳዩንም አማከረችው፡፡ ‹‹እየውልህ! እንዳትመክረኝ፤ ሰላም ፍጠሪ፤ ፀባይ ፍጠሪ እንዲህ ሁኚ እንዳትለኝ፡፡ እንዴት አድርጌ ሰው ሳያውቅብኝ እንደምገድላት ብቻ ንገረኝ፡፡ አንተ ጠቢብ ስለሆንክ እርሱ አያቅትህም›› አለችው፡፡

ጠቢቡ ሰው በደንብ ከሰማት በኋላ ‹‹ልክ ነሽ መፍትሔው የባልሽን እናት መግደል ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ እኔ አንድ አስገራሚ መፍትሔ እሰጥሻለሁ›› አለና የሆነች የውሃ ቀለም ያላት ትንሽዬ ብልቃጥ አመጣና ሰጣት። ይህን እናቲቱ ምግባቸው ውስጥ ወይም የሚጠጡት ነገር ላይ ትቀላቅይዋለሽ፤ ደስ የሚለው መርዙ በአንዴ አይገላቸውም፡፡ ቀስ እያለ፣ እያሳመመ፣ እየጎዳ ይገድላቸዋል፡፡ ያኔ አንቺም አይነቃብሽም›› አላት፡፡

ሚስት በጣም ደስ አላት፡፡ ‹‹በጣም አመሰግናለሁ›› አለችው ጠቢቡን ሰው፡፡ ልትሄድ ስትል ግን ጠቢቡ ሰው እንዲህ አላት፡፡ ‹‹ከዚህ በኋላ መጨቃጨቅ ማቆም አለብሽ። ምክንያቱም በሳምንታትና በወራት ውስጥ እኚህ ሴትዮ ሲሞቱ የምትጨቃጨቂያቸው ከሆነ ሰው ይጠረጥራል። ድሮም እሷ ናት ነገር እየገፋች ጎድታ የገደለቻቸው ይሉሻል፡፡ ስለዚህ አሁን እንደምንም ብለሽ አንገትሽን ድፊ፡፡ የምትወጃቸው ምሰይ፡፡ ቢቆጡ፣ ቢጮሁብሽ ተንከባከቢያቸው›› አላት፡፡

‹‹አሁንማ አረጋገጥኩ እኮ! ከአንድ ወር በኋላ ከሌሉ ለምን አንገቴን አልደፋም፡፡ እንደምወዳቸው እሆናለሁ ችግር የለውም፤ አመሰግናለሁ›› ብላ ሄደች፡፡ ቤቷ ሄዳ ማታ ላይ ሻይ ስታቀርብላቸው ያንን ፈሳሽ ቀላቅላ ሰጠቻቸው፡፡ ከሰጠቻቸው በኋላ ግን ቢሞቱስ ብላ መፍራት ጀመረች፡፡ ‹‹ግን ችግር የለውም ይሙቱ እኔ ፀባዬን አሳምራለሁ›› አለች። ከዛ ሲቆጧት ዝም ትላለች፡፡ ሳቅ እያለች ትመልሳለች። ጥሩ ምግብ አዘጋጅታ ታቀርብላቸዋለች፡፡ እግራቸውን ታጥባቸዋለች፡፡ ድሮ ነገር የሚፈልጓትና የሚሳደቡት ሴትዮ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገው ተውት፡፡ እሷን መመረቅ ጀመሩ፡፡ ልጄ ምን ዓይነት መልአክ የሆነች ሴት ነው ያገባው ማለት ጀመሩ። እሳቸውም ሳያውቁት ተቀየሩ፡፡ ሚስትና እናት ፍቅር በፍቅር ሆኑ፡፡

ከዛ ነገሮች ተቀየሩ፡፡ ለቤተ ዘመድ ሁሉ ሲያስተዋውቋት ‹‹እየውላችሁ እንዴት ያለች መልዓክ የሆነች ሚስት መሰለቻችሁ ልጄ ያገኘው›› ማለት ጀመሩ። ከዛ እሷም ሳትፈልግ ተቀየረች። ወደደቻቸው። መጠራጠር ጀመረች፡፡ ‹‹ወይኔ! ከሶስት ሳምንት በኋላ ቢሞቱስ›› ብላ መፍራት ጀመረች፡፡ ቢጨንቃት ጠቢቡ ሰው ጋር ሄደች። ጠቢቡ ሰውም ‹‹ምን ተፈጠረ፤ ሞቱ አይደል›› አላት። ኧረ አልሞቱም! ጉድ ሆኜልሃለሁ፡፡ የኔ ፀባይ ሲቀየር እርሳቸውም ወደዱኝ፡፡ አሁን እንዲሞቱ አልፈልግም፡፡ በጣም ጥሩ ሴት ናቸው፡፡ እኔም ባሌም ማዘን አንፈልግም፡፡ ስለዚህ ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ ? መርዙን የሚያሽር ነገር ስጠኝ አለችው፡፡

ጠቢቡ ሰው ፈገግ እያለ ድሮስ እኔ የሚገድል ነገር እኮ አልሰጠሁሽም፡፡ ውሃ ነበር በብልቃጥ የሰጠሁሽ። እንደዚህ እንደሚፈጠር አውቃለሁ አላት፡፡ አያችሁ አይደል! እኛ ስንቀየር ነገሮች፣ ሰዎችና ሁኔታዎች ይቀየራሉ፡፡ ሰዎችን ለመቀየር መሞከር የለብንም፡፡ ስለዚህ የምንቆጣጠረውንና ልንቀየር የምንችለው ነገር ላይ ማተኮር አለብን፡፡

### 3ኛ.መዝጋት ያሉብን በሮች አሉ

መዝጋት ያሉብን በሮች አሉ፡፡ ያውም ጥርቅም አድርገን፡፡ አብዛኛዎቻችን የምንኖረው ትላንት ላይ ነው። ስለትናንት ነው የምናስበው፡፡ የካዱንን፣ የጎዱንን በቃ! እርሱ እኮ እንዲህ እንዲህ አድርጎኝ፣ እንዲህ አድርጋኝ፣ እንዲህ ተፈጥሮ፣ ከስሬ፣ አብድሬው ካደኝ፣ ንፁህ ልቤን ሰጥቻት ካደችኝ ....ሃሳባችን ትላንት ላይ ነው፡፡ ዛሬን እየኖርን አይደለም፡፡ ስለነገም አናስብም፡፡ ትላንት የተጎዳነውንና የተበደልነውን ነው የምናስበው፡፡ ስለዚህ ጥርቅም አድርገን የምነዘጋቸው በሮች መኖር አለባቸው፡፡ እስከመጨረሻው የማንከፍታቸው ፋይሎች ያስፈልጋሉ።

ከትላንቱ መማር አለብን፡፡ ግን አንዳንዴ ደግሞ ትናንትን መዝጋትም አለብን፡፡ ትላንት ላይ መኖር የለብንም፡፡ ትላንት ቤቱን ሰራብን እኮ፡፡ አንድ ሰው እቃ ተሸክሞ ይሄዳል። ረጅም ጉዞ ነው የተጓዘው፡፡ እቃው ትንሽ ትከሻውን አድክሞታል፡፡ መንገድ ላይ ባለመኪና አገኘ፡፡ ባለመኪናው አዝኖለት መኪናውን አቁሞ ና! ግባ ብሎ እቃውን ኋላ መኪና እሱን ደግሞ ከፊት አስገብቶ ጉዞ ጀመረ፡፡ ግን የሚገርመው እቃውን የተሸከመው ሰውዬ ትከሻው ዘምበል ብሎ ነበር፡፡ አሁንም የተሸከመ ነው የሚመስለው፡፡

ለምን መሰላችሁ? እቃው ከትከሻው መውረዱን አላመነም፡፡ እቃው እኮ ግን ወርዷል፡፡ ከመኪናው ኋላ ነው የተቀመጠው፡፡ እርሱ ግን ትከሻውን አጎምብሷል። የጀርባ በሽታ ኖሮበትም አይደለም። አላመነም፡፡ እናንተም ትናንትናችሁን፣ ከባዱን ጊዜ፣ መጥፎውን ጊዜ ፈጣሪ አሳልፎላችኋል። የሚያሳዝኑ ነገር ግን ያለፉ ስንት ቀናት አሉ፡፡ ቀናቶቹን አልፋችኋል፡፡ ግን አልረሳችኋችሁም፡፡ የምትኖሩት ትላንት ውስጥ ነው። የትናንት ችግር አሁንም ተብትቦ ይዟችኋል፡፡ ስለዚህ በጥሱት፡፡

### 4ኛ. እንኳንም ተበላሸ!

አንዳንድ ነገሮች ካልደፈረሱ አይጠሩም። በሕይወታችን መበላሸት ያለባቸው ነገሮች አሉ። እንኳንም ተበላሸ! ብለን ማመን አለብን። አመለካከታችንና አተያያችን መቀየር አለብን፡፡ ንጉሡ ሁለት ስጦታዎች ተሰጡት። የሚያማምሩ ወፎች፡፡ አንዷ በሰማይ ላይ ስትበር ታፈዛለች፤ታምራለች። አንዷ ግን ቅርንጫፉ ላይ ቆማ ቀረች፡፡ ንጉሡ ደግሞ ይችኛዋን ስትበር ማየት ፈለገ፤ ጓጓ። ስለዚህ አማካሪዎቹን ጠራና ‹‹ጠቢብም ይሁን ማንም ሰው ጥሩና ይችን ወፍ እንድትበር ያድርግልኝ›› አላቸው። ብዙ ጠቢባን መጡ፡፡ ወፏ እንድትበር የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ፡፡ አልቻሉም። ንጉሡ ‹‹እየውላችሁ ወፏ ስትበር ከማየት በላይ የምፈልገው ነገር የለም›› እያለ አማካሪዎቹን ማስጨነቅ ጀመረ፡፡ ግን አልተሳካም፡፡

የሆነ ቀን ንጉሡ ሰገነቱ ላይ ሆኖ እየተዝናና እያለ ያቺ ወፍ ከፍ ብላ ስትበር ያያታል፡፡ በጣም ነው የምታምረው፡፡ ልቡ ተነካ፡፡ አማካሪዎቹን ጠራና ይችን ወፍ እንድትበር ያደረጋትን ጠቢብ ጥሩልኝ አለ፡፡ የመጣው ግን ጠቢብ ሳይሆን ገራገር ገበሬ ነበር፡፡ ንጉሡ ተገረመ። ‹‹የምትፈልገውን ነገር ሁሉ እሸልምሃለው፡፡ ‹‹ግን ምን አድርገህ ወፊቱን እንዳበረርካት፣ ምን ዓይነት ጥበብ ብትጠቀም ወፊቱ የበረረችው እስኪ ንገረኝ›› አለው፡፡

ገበሬው መለሰ ‹‹የዛፉን ቅርንጫፍ ቆረጥኩት፤ በረረች›› አለ፡፡ ንጉሡ በጣም ተገረመ፡፡ እኛም በሕይወታችን ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ከፍ ብለን እንድንበር፣ የምንፈልገውን እንድናሳካ፣ ነፃነት እንዲኖረን አንዳንድ መቆረጥ ያለባቸው ነገሮች አሉ። ከሕይወታችን መበላሸት፣ መደፍረስ ያለበት ነገር አለ፡፡ ለምን? እንደወፏ ከፍ ብለን እንድንበር። ነፃነት እንዲሰማን፡፡ አዲስ ነገር እንድሞክር ሊያደርጉን ይችላሉ፡፡

### 5ኛ. አለኝ የምትሉትን ነገር ዘርዝሩ

አይታችሁ ከሆነ ብዙዎቻችን ካለን ነገር ይልቅ የጎደለንን ማየት ይቀድመናል፡፡ ቆይ ይችን ነገር ብሞላት፣ እዛች ጋር ገቢ ባገኝ እኮ፣ ይችን እቃ ብገዛ፣ ይችን ባሟላ ደስ ይለኛል.... እንላለን፡፡ ግን ይሄ አለኝ፣ እንዲህ እኮ አለኝ አንልም፡፡ ሁልጊዜ ጉድለታችንን ነው የምናስበው፡፡ ልጁ በጣም አምርሮ እያለቀሰ ነው፡፡ ሰውዬው መጣና ‹‹አይዞህ! ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው?›› አለው፡፡ ‹‹አጎቴ ሞተብኝ፤ ምን ላድርግ›› አለ፡፡ አይዞህ! አይዞህ! ይለዋል፡፡ አይ አጎቴ እኮ ሲሞት ያወረሰኝ ገንዘብ አለ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር አለ፡፡ ታዲያ ለምን ታዝናለህ አጎትህ እኮ ጥሩ ነገር አስቀምጦልሃል አለው፡፡ ቢሆንም የዛሬ ዓመት ደግሞ ሌላኛው አጎቴ ሞቶ ነበር አለ፡፡ ወይ! አይዞህ ለዛኛውም አጎትህ አይዞህ! አለው፡፡ ያኛውም አጎቴ ያስቀመጠልኝ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብብ እኮ አለ አለው፡፡ በጣም ደስ ይላል አንተ አጎቶችህ ጥለውልህ የሄዱት ነገር አለው ሰውዬው፡፡

አሁንም ግን ልጁ እያለቀሰ ነው፡፡ ለምን ታዲያ ታለቅሳለህ ሲለው የዛሬ ሁለት ዓመት ደግሞ ሌላኛው አጎቴ ሞቶ ነበር አለው፡፡ እንዴ! አለ ሰውዬው በመገረም። አዎ! እሱም ሲሞት ግን ያስቀመጠልኝ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብትና ንብረት ነበር አለው። ታዲያ አንተ ለምን ታዝናለህ? ሶስቱም አጎቶችህ ሲሞቱ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አውረሰውህ ነው፡፡ ታዲያ አንተ ማዘን አለብህ? አለው፡፡ አሁንማ የሚያንገበግበኝ ሌላ የሚያወርሰኝ አጎት የሌለኝ መሆኑ ነው፡፡ ሶስቱ ሞተው አለቁ አለ፡፡

አስባችሁታል በሕይወታችን ብዙ የተሰጠንን አናይም፡፡ የጎደለን ምን አለ፣ ምን አነሰ፣ እጄ ላይ ምን ጎደለ፣ ምንድነው ቀዳዳው የምንለው። ምን ተደፈነ አንልም፡፡ ፈጣሪ ምን ሰጠኝ፣ ምን አደረገልኝ አንልም። ተስፋ አሳጣኝ፣ አነሰኝ፣ ጎደለኝ የምንለው ነገር ግን እጃችን ውስጥ ያለ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ጠንካራ መሠረት የጣለው የንግድ ሥራ- ከኢትዮጵያ እስከ ቻይና

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የንግድ ሥራቸውን አሀዱ ያሉት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ባጠናቀቁ ማግሥት ነው። ‹‹ወጣት የነበር ጣት›› እንዲሉ የንግድ ሥራውን በከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት፣ በብዙ ጥረትና ትጋት ነው የተቀላቀሉት፡፡ የንግድ ሥራውን በዕውቀት ለመምራትም በኢትዮጵያም በቻይናም ብዙ ወጥተዋል፤ ወርደዋል፡፡ የትናንቱ ሩጫ፣ ጥረትና ትጋታቸውም ዛሬ ላይ የኢንቨስትመንት ባለቤት አድርጎ ሾሟቸዋል፡፡

እኚህ የዛሬው የስኬት እንግዳቸችን አቶ እስመለዓለም ዘውዴ ይባላሉ፡፡ ገና በጠዋቱ ሕይወትን ቀላልና ምቹ ከሚያደርገው ቴክኖሎጂ ጋር የመተዋወቅ ዕድል ያገኙት እኚህ ሰው የኢዜድ ኤም ትሬዲንግና ኢንቨስትመንት መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የተማሩት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ወደ ሥራ ዓለም ሲገቡ ገና የ20 ዓመት ጎረምሳ ነበሩ። ‹‹ዕድሜ ቁጥር ነው›› እንዲሉ ያወቁትን ለሌላው ለማሳወቅ፣ ለማስተማርና እግረ መንገዳቸውን ደግሞ ነጋዴ ለመሆን አልቦዘኑም፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ተወልደው ያደጉት አቶ እስመለዓለም፣ ከዜሮ ክፍል ጀምረው ፊደል የቆጠሩት በቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ነው። የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውንም እንዲሁ በዚሁ ትምህርት ቤት ነው ያጠናቀቁት፡፡ የከፍተኛ ትምህርታቸውንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ፋኩልቲ /አራት ኪሎ ካምፓስ/ ተከታትለዋል፤ በዚህም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕውቀትን ታጥቀዋል፡፡ በወቅቱ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አዲስ ነገር በመሆኑ ቴክኖሎጂውን የማወቅና የመጠቀም ጉጉታቸው እጅግ ከፍተኛ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

በከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት የተከታተሉትን የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት በተግባር ለማዋል ጊዜ ያላጠፉት አቶ እስመለዓለም፤ አራት ኪሎ አካባቢ የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ቤት ሲከፍቱ እርሳቸው ያገኙትን ዕውቀት ለሌሎች ለማካፈል ከውስጥ የመነጨ ፍላጎት ነበራቸው። የንግድ ሥራቸው መነሻ የነበረው የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ቤትን ሲከፍቱ የቤተሰቦቻቸው እገዛ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው አጫውተውናል፡፡

በተለይ ኮምፒውተር በሚሰጠው አገልግሎት በእጅጉ ይገረሙ የነበሩትና በንግድ ሥራ የተሰማሩት ወላጅ አባታቸው አቶ ዘውዴ፤ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የኮምፒውተር ማስተማሪያ ትምህርት ቤት እንዲከፍቱ ትልቅ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ‹‹አባቴ እኔ ያገኘሁትን ዕውቀት ለሌሎች እንዳደርስ ብርቱ ጥረት አድርገዋል›› የሚሉት አቶ እስመለዓለም፤ እርሳቸውም በዘርፉ የቀሰሙትን ዕውቀት ለሌሎች ለማስተላለፍ ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት እንደነበራቸው በማስታወስ የንግድ ሥራቸውን አጠናክረው መቀጠል እንደቻሉ ተናግረዋል፡፡

ከመደበኛው የኮምፒውተር ትምህርታቸው በተጨማሪም ተያያዥ የሆኑትን የኮምፒውተር ጥገና፣ የኮምፒውተር ኔትዎርኪንግና ሌሎች ትምህርቶችንም ተከታትለዋል፡፡ የማስተማር ሥራንም እንዲሁ ጎን ለጎን አከታትለዋል፡፡ በወቅቱ መምህራንን ቀጥረው በቀንና በማታው ክፍለ ጊዜ ጭምር ነበር የሚያስተምሩት፡፡

በቤተሰባቸው ድጋፍና በግል ጥረታቸው ጭምር ወደ ንግድ ሥራ የገቡት አቶ እስመለዓለም፤ ወላጅ አባታቸው በሥጋ ሲለዩአቸው ደግሞ የእርሳቸውንም የንግድ ሥራ ደርበው የማስተዳደር ኃላፊነት ወደቀባቸው፤ ቢሆንም እጅ አልሰጡም፡፡ ሁኔታው ይበልጥ ጠንካራና ብርቱ ነጋዴ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የግል ሥራቸውን ከወላጅ አባታቸው የንግድ ሥራ ጋር ደርበው ለመሥራት የቤተሰብ እገዛ ያስፈለጋቸው በመሆኑ ወንድማቸውን አጋር አድርገው በጋራ መሥራት ጀመሩ፡፡

ወላጅ አባታቸው ለንግድ ሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ እንደ ኮምፒውተር፣ ቀለም፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን እና ሌሎች ቁሳቁስን ከጣልያን ሀገር ያስመጡ እንደነበር ያስታወሱት አቶ እስመለዓለም፤ ይህን ማድረግ ባይችሉም ቁሳቁስን ለማሟላትና የወላጅ አባታቸውን እንዲሁም የግላቸውን የንግድ ሥራ ለማስቀጠል መፍትሔ ይሆናል ወዳሉት ሀገረ ቻይና አቀኑ፡፡



አቶ እስመለዓለም ዘውዴ

**ለዚህም አስፈላጊና መሠረታዊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን ብቻ ከውጭ በማስመጣት ግብዓቶችን የሚያመርት ሲሆን፤ በቀጣይም ጥሬ ዕቃዎቹን በሀገር ውስጥ የመተካት ዕቅድ አለው**

‹‹ወደ ቻይና ስሄድ ሥራ ፍለጋ ነበር›› የሚሉት አቶ እስመለዓለም፤ ሀገር ውስጥ ያለውን የንግድ ሥራ ወንድማቸው እንዲመራው በማድረግ እርሳቸው ደግሞ የተሻለና አዲስ የሥራ አቅጣጫን ለመፍጠር ጭምር አቅድው ነው የተጓዙት፡፡ በ2002 ዓ.ም በዘመነ ሚሊኒየም ወደ ቻይና ያቀኑት አቶ እስመለዓለም ከቻይናውያኑ ቋንቋን ጨምረው ብዙ ተምረዋል፡፡ በዚህም ጠንካራ ትስስር በመፍጠር የንግድ ሥራቸውን ማስፋፋት ችለዋል።

ከስድስት ወራት ቆይታ በኋላ አፍሮ ቻይና የተባለ ቢሮ በቻይና ከፍተው የንግድ ሥራቸውን ማሳለጥ የጀመሩት አቶ እስመለዓለም፤ በወቅቱ ሀገር ውስጥ ላለው ድርጅታቸውና ለሌሎች ደንበኞችም ተያያዥ የሆኑና ጥራት ያላቸውን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቁሳቁስ በመላክ ውጤታማ መሆን ችለዋል፡፡ በወቅቱ ቻይና ውስጥ አሉ የተባሉ ፋብሪካዎች አካባቢ በመሄድ ምርቶቹ ሲመረቱ ተመልክተው የጥራት ደረጃቸውን አረጋግጠውና ሞክረው ወደ ሀገር ቤት ይልኩ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ ምርቶቹም በሀገር ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት ነበራቸው፡፡

በንግድና በቴክኖሎጂ ሰፊ ውቅያኖስ ከሆነችው ቻይና ገብተው የንግድ ሥራቸውን ማቀላጠፍ የጀመሩት አቶ እስመለዓለም፤ ወደ ቻይና ከሚመጡ ነጋዴዎች ጋርም እንዲሁ ትስስር በመፍጠር ነጋዴው የሚፈልገውን ዕቃ በማቅረብ ለነጋዴዎች ወኪል በመሆን ብዙዎችን አግዘዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ የንግድ ሥራቸውን እያሰፉ በመሄድ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወደ ግንባታ ዕቃዎች ተሸጋግረዋል፡፡

ለአብነትም አንድ ባለሀብት ለሚገነባው ሆቴል ግንባታ ግብዓት የሚሆኑ የተለያዩ የፊኒሺንግ ዕቃዎችን ፍለጋ ወደ ቻይና ካቀና በቀዳሚነት የሚፈለጉት አቶ እስመለዓለም መሆን ቻሉ፡፡ እሳቸውም ሰውዬው የሚፈልገውን እቃ አንድ በአንድ መግዛት የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሥራውን ያቀሉለታል፡፡ ለዚህ ሥራቸውም ለቻይናውያን እና ለኢትዮጵያውያን የሥራ ዕድል በመፍጠር ነጋዴው ቻይና ሲገባ ጀምሮ ሆቴል በመያዝ የሚፈልገውን ዕቃ በሙሉ ገዝተው ይልኩለታል፡፡ ነጋዴውም ያለድካምና እንግልት የሚፈልገውን ዕቃ መርጦ ይገዛል፡፡

አቶ እስመለዓለም በሀገረ ቻይና በነበራቸው የመጀመሪያ ቆይታ ቋንቋ ማወቃቸው ዛሬ ለደረሱበት ትልቅ የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራ መሠረት እንደጣለላቸው ይናገራሉ፡፡ አንዱ ሥራ ለሌላ ሥራ በር እየከፈተ በመሄዱ ኑሯቸው ቻይና ሊሆን ግድ ሆነና በቻይና ለ13 ዓመታት ቆይታ አድርገዋል፡፡

ከዚህ ቆይታ በኋላ ደግሞ በከፊል ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ የንግድ ሥራቸውን ማስቀጠል ጀመሩ፡፡ በአሁን ወቅትም ቻይና ውስጥ አብረው ለሚሰሩባቸው ድርጅቶች በኢትዮጵያ ወኪል በመሆን ኢዜድ ኤም ንግድና ኢንቨስትመንት የተባለውን ድርጅት ማቋቋም ችለዋል፡፡ ድርጅቱ የግንባታ ዕቃዎችን ጨምሮ የተለያዩ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን በማስመጣት አንድ እግሩን ቻይና ሌላኛው እግሩን ደግሞ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ አድርጎ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡

ከግንባታ ዕቃዎች በተጨማሪ የሕክምና ቁሳቁስን ወደ ሀገር ውስጥ በማስመጣት የሚታወቀው ኢዜድኤም ንግድና ኢንቨስትመንት በተለይም የላብራቶሪ ቁሳቁስንና የኤክስሬይ ማሽኖችን ያስመጣ እንደነበር ያስታወሱት አቶ እስመለዓለም፤ ዓለም አቀፍ ስጋት በነበረው የኮቪድ ወረርሽኝ ጊዜ ግብዓቶችን ከቻይና በማስመጣት ሰፊ ሥራ ሲሰሩ መቆየታቸውን አጫውተውናል፡፡

‹‹ቻይና በነበረኝ ቆይታ ከቻይናውያኑ ብዙ ተምሬያለሁ›› የሚሉት አቶ እስመለዓለም፤ ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው በንግድ ሥራ መሰማራታቸው ጠቅሟቸዋል። ከኢትዮጵያ እስከ ቻይና ያደረጉት የንግድ እንቅስቃሴም በሀገር ውስጥ ችግር ፈቺ በሆነው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለመሰማራት አስችሏቸዋል፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ከቻይና ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቧቸው የነበሩ የግንባታ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት ዝግጅታቸውን አጠናቅቀዋል፡፡ ለዚህም የዳበረ ግንኙነት ካላቸው ከቻይናውያኑ ዘንድ ማሽነሪዎችን ጨምሮ ዕውቀትና ልምድን ወደ ሀገር ውስጥ ማምጣት ችለዋል፡፡

የዳበረ ዕውቀትና ልምድ ይዘው በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩት አቶ እስመለዓለም፤ ለፋብሪካ ግንባታ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ 10 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ወስደዋል። ይሁንና ፋብሪካው ተገንብቶ ወደ ምርት ለመግባት የሚወስደው ጊዜ ረዘም ያለ በመሆኑ የኢንዱስትሪ ፓርክን አማራጭ አድርገዋል። በመሆኑም በቶሎ ወደ ምርት ለመግባት ያደረጉት ጥረት ተሳክቶ፤ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ባገኙት 3000 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ሼድ 14 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪ በማድረግ ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

ፋብሪካውን በተረከበ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ወደ ምርት የገባው ኢዜድኤም ንግድና ኢንቨስትመንት፤ በአሁን ወቅትም የጥራት ደረጃቸው ከውጭ ከሚመጡት ጋር ተወዳዳሪ የሆኑና ዘመኑን የዋጁ የግንባታ ዕቃዎችን በሙሉ አቅሙ በሀገር ውስጥ እያመረተ ይገኛል፡፡ ኢዜድኤም ንግድና ኢንቨስትመት ከሚያመርታቸው የግንባታ ዕቃዎች መካከልም ፒፒአር፣ ኤችዲፒኢ፣ ፒቪሲ ቧንቧዎች እና ቱቦዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ምርቶቹ አስፈላጊ ከሆኑ የመገጣጠሚያ ዕቃዎች ጋር የሚመረቱ በመሆናቸው በዘርፉ ከፍተኛ ዕድገትን የሚያስመዘግብ ነው ያሉት አቶ እስመለዓለም፤ ፋብሪካው፤ በዓመት እስከ ሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ፒፒአር ትቦዎች እና አንድ ሚሊዮን 900 ሺህ የፒፒአር መገጣጠሚያዎች፣ አንድ ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የፒቪሲ ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች እና 900 ሺህ የፒቪሲ መገጣጠሚያዎች እንዲሁም ሶስት ሚሊዮን 500 ሺህ ሜትር በላይ የፒቪሲ ኮንዲዩት ማስተላለፊያ ትቦዎችን የማምረት አቅም እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካው አንድ ሕንፃ ሲሰራ ለሕንፃው አስፈላጊ የሆኑ የኤሌክትሪካልና የውሃ መዘርጊያ ቁሳቁሶችን በሙሉ የሚያመርት ሲሆን፤ በተለያዩ ዘርፎች ያለውን የቧንቧ እና የቱቦ ዝርጋታ ሥርዓት አቅርቦትና ጥራት እጥረትን መፍታት የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም እነዚህን ምርቶች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ረገድም አበርክቶው ጉልህ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

ሀገር በብርቱ እየተፈተነች ያለችበትን የውጭ ምንዛሪ እጥረት የማቃለል ዕቅድ ያለው ኢዜድኤም ንግድና ኢንቨስትመንት በሙሉ አቅሙ ወደ ምርት ሲገባ በዓመት አስር ሚሊዮን ዶላር ወጪ የሚጠይቅ ምርት የማምረት አቅም እንዳለውና ይህም ማለት ሀገሪቷ ለግንባታ ማጠናቀቂያ ዕቃዎች ታወጣው ከነበረው የውጭ ምንዛሪ በዓመት አስር ሚሊዮን ዶላር ማዳን ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ በግንባታ ላይ እንደመሆኗ የግንባታ ማጠናቂቂያ ግብዓቶች በስፋት ይፈለጋሉ ያሉት አቶ እስመለዓለም፤ የሚገነቡ ሕንፃዎች በሀገር ውስጥ ምርት መጠናቀቅ እንዳለባቸውም ያምናሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ባለው የሕንፃ ግንባታ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑ ግብዓቶች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ በመሆናቸው ሕንፃውን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ያህል ነው፡፡ በእነዚህ የግንባታ ግብዓቶች የሀገሪቷ ኢኮኖሚ እየተናጋ ነው፡፡

ይሁንና ለዚህ ችግር እነሆ መፍትሔ ያለው ኢዜድኤም የንግድና ኢንቨስትመንት በአሁን ወቅት አንድን ሕንፃ መቶ በመቶ በሀገር ውስጥ ለማጠናቀቅ እየሠራ ይገኛል፡፡ ለዚህም አስፈላጊና መሠረታዊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን ብቻ ከውጭ በማስመጣት ግብዓቶችን የሚያመርት ሲሆን፤ በቀጣይም ጥሬ ዕቃዎቹን በሀገር ውስጥ የመተካት ዕቅድ አለው፡፡ ለዚህም ጥናት እያደረጉ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ እስመለዓለም፤ ማንም ሰው ለሚገነባው ሕንፃ ሙሉ የፊኒሺንግ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር ማስመጣት እንደሌለበትና ድርጅታቸው ኢዜድኤም ንግድና ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ጥራት እያመረተ መሆኑን በልበ ሙሉነት ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካው በምርት ሥራው ብቻ ከ300 ለሚልቁ ዜጎች የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም ሲኖረው በቀጣይ ምርቶቹን ወደ ገበያ በሚያወጣበት ወቅትም እንዲሁ ወኪል ሻጮችን ጨምሮ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለበርካቶች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ይሆናል፡፡ በቀጣይ በሶስት ፈረቃ ያመርታል ተብሎ የሚጠበቀው ይህ ፋብሪካ በአሁን ወቅት በአንድ ፈረቃ ለሚያመርተው ምርት 85፣ የቢሮ ሥራ ለሚሠሩ 100፣ ስቶር ላይ ለሚሰሩ 40 በድምሩ ለ225 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል፡፡

በርካታ ሥራዎችን የመሥራት ዕቅድ ያለው ኢዜድኤም ንግድና ኢንቨስትመንት ከሚያመርተው ምርት 50 በመቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ ተደራሽ የሚያደርግ ሲሆን 50 በመቶውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ በሀገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ ጉልህ አበርክቶ ይኖረዋል፡፡ በቀጣይም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወሰደው 10 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ፋብሪካ በመገንባት ሥራውን የማስፋፋትና በርካታ የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ አለው፡፡

ባለቤቱ እንደሚናገሩት ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ድርጅቱ ከኮንስትራክሽን ጋር በተያያዘ ለማህበረሰቡ ውሃ የማውጣት ሥራዎችን በመሥራት የሚታወቅ ነው። ሀገራዊ በሆኑ ማንኛውም ጥሪዎችም እንዲሁ ምላሽ በመስጠት ቀዳሚ ነው፡፡ የመንግሥትን ግብር በአግባቡ የሚከፍለው ኢዜድ ኤም ንግድና ኢንቨስትመንት ታማኝ ግብር ከፋይ በመሆን ተሸላሚ ከሆኑ ድርጅቶች መካከልም ተጠቃሽ ነው፡፡

ኢኮኖሚ

## መሠረተ ልማት

# የዓድዋ ድል ትሩፋት ማሸጋገሪያ ሙዚየም

በኃይሉ አበራ



የፕሮጀክቱ ግንባታ 95 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በአንድ ወር ውስጥ ሙሉ ለሙሉ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል፤

ከአዲስ አበባ ከተማ እምብርት ከማዘጋጃ ቤቱ በመነሳት ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያለውን ርቀት ለመግለፅ የኪሎ ሜትር መነሻ በመሆን ይታወቃል። በ 1888 ዓ.ም በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ለተደመደመው የዓድዋ ጦርነት የወቅቱ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ባደረጉት የክተት ጥሪ መሠረት ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን ወደ ዓድዋ ጉዞ ሲያደርጉ መነሻቸውም ይሄው ታላቅ ሥፍራ ነው፡፡ ሥፍራው እስከ አሁን ስያሜው ፒያሳ (አራዳ) በመባል ይታወቃል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሥሪያ ቤት (ማዘጋጃ ቤት) ፊት ለፊት እና ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ አደባባይ ጥቂት ዝቅ ብሎ በሚገኘው በዚህ ታሪካዊ ቦታ አንድ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ሲገነባ ቆይቶ አሁን በማጠናቀቂያ ምእራፍ ላይ ይገኛል፡፡

በተንጣለለው ቦታ ላይ ግንባታው ሲካሄድ የቆየው ይህ ታላቅ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክት የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ሙዚየም ፕሮጀክት በመባል ይጠራል፡፡ የመላው ጥቁር ሕዝብ ኩራት፣ ህያው ምስክር እንዲሁም ለመጪው ትውልድም ታሪካዊ ቅርስ እንዲሆን ታስቦ የተገነባው ይህ ዓድዋ ሙዚየምና የተለያዩ አገልግሎት መስጫ መሠረተ ልማቶች የተካተቱበት ግዙፍ ፕሮጀክት ግንባታ 95 በመቶ ላይ ደርሷል፤

የከተማዋ አስተዳደሩ ከከተማዋ ትላልቅ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ጋር በመሆን የዓድዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም የግንባታ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በቅርቡ ለመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች እና ጋዜጠኞች አስጎብኝቷል። በዚሁ ወቅት እንደተጠቆመውም፤ የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም ፕሮጀክት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሃሳብ አመንጪነት ተጀምሮ ግንባታው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለቤትነት በቻይናው ጂያንግሱ ኩባንያ ተቋራጭነት ላለፉት ዓመታት ሲካሄድ የቆየ ግዙፍ ፕሮጀክት ነው።

በአዲስ አበባ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት እየተገነቡ ከሚገኙት እና የተለየ ዋጋ ካላቸው ፕሮጀክቶች አንዱ ነው፡፡ ከአንድ ወር በኋላ ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገም ነው። ኢትዮጵያውያን ደማቅ የነፃነት እና የአልገዛም ባይነት ገድል የፈጸሙበት የዓድዋ ድል ታሪክ የሚዘከርበት ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት፣ ዘርፈ-ብዙ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ በርካታ ግንባታዎችና ቴክኖሎጂዎች የተካተቱበት መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

የከተማዋ ከንቲባ ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ወርቁ በጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት፣ የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም ፕሮጀክት በተያዘለት በጀት እና ጊዜ እንዲጠናቀቅ የበላይ አመራሩ ከአማካሪውና ኮንትራክተሩ ጋር በመገናኘት በተደጋጋሚ ምልከታ እና ክትትል አድርጎለታል። የቴክኖሎጂ እና የፋይናንስ አቅርቦት በማድረግም የግብዓት ችግሮች እንዳይኖሩ ጥረት ተደርጓል። በዚህም በተያዘለት የጊዜ ገደብ መሠረት ግንባታው እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡ በቀጣይ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ይጠናቀቃል።

ፕሮጀክቱ የዓድዋ ሙዚየም እንደመሆኑ ለሙዚየሙ የሚሆኑ ቅርሳቅርስ የሚያሰባስቡ ኮሚቴዎች ተዋቅረውም ቅርስ የማሰባሰቡ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ሃላፊው፣ ሙዚየሙ ኢትዮጵያውያንን በሚያሰባስብ፣ አልበገርነታቸውን በሚያሳይ እና ለትውልድ ግንባታ በሚሆን ደረጃ ኢንዲደራጅ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪዎች እና በዓድዋ ድል ዙሪያ በፃፉ አካላት ታሪኩን የማደራጀት ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል። አካባቢው የቱሪዝም መስህብ እንደሚሆን ጠቅሰው፣ በከተማ አስተዳደሩ ከሚገነቡት ግዙፉ ፕሮጀክት ቀዳሚው መሆኑን አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ኃላፊ ኢንጂነር ደቦ ቱንካ በጉብኝቱ ወቅት እንዳብራሩት፤ የዓድዋው ድል ኢትዮጵያውያን በጦርነቱ ራሳቸውን በመሰዋት ለዓለም ሕዝብ ራሳቸውን ይበልጥ የገለጹበት የጥቁር ሕዝቦች ኩራት መሆናቸውን ያረጋገጠበት፣ የአልበገርነትና የጀግንነት እሴት የተገኘበት መሆኑን ጠቅሰው፣ የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት ይህን ትሩፋት ለትውልድ በማስቀጠል የአንድነት ምሰሶ ሆኖ እንደሚያገለግል አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ፕሮጀክቱ ፕላዛ አንድ እና ፕላዛ ሁለት የሚባሉትን ያካተተ ሲሆን፤ ፕላዛ አንድ የሚባለው በተለምዶ መነፀር ቤቶች በሚባለው አካባቢ እየተገነባ የሚገኝ ነው። ከለገሃር ባቡር ጣቢያ ጀምሮ ቸርችል ጎዳናን ይዞ ፒያሳ ድረስ ያለው ስፍራ የኢትዮጵያ የታሪክ መዘክሮች ኮሪደር መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህ ስፍራ ፕላዛ ሁለት በሚል ተጨማሪ መዘክር መካተቱን ጠቁመዋል። ኮሪደሩን ተከትሎም ዓድዋ ሙዚየም ሲደርስ ትልቁን እሴት የሚያሳይ ቦታ ይኖረናል ብለዋል።

ኢንጂነሩ እስካሁን ዓድዋ በስም እና በሃሳብ ብቻ ሲዘከር መቆየቱን አስታወሰው፤ የዓድዋ ሙዚየም ግንባታ እውን ከመሆኑ በተጨማሪ፣ በስፍራው ለመታሰቢያነት የሚውል የ20 ሜትር ከፍታ ያለው ሐውልት እንደሚገነባም ይገልፃሉ።

ኢንጂነር ደቦ ቱንካ እንዳታስታወቁት፤ የዓድዋ ሙዚየም አምስት በሮች አሉት። አራቱ በሮች ለዓድዋው ጦርነት በተደረገው የክተት ጥሪ መሠረት ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ እና ከምዕራብ (ከሁሉም አቅጣጫዎች) የተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን ወደ ዓድዋ ጉዞ ለማድረግ የተመሙበትን ሁኔታ ማሳያ ናቸው።

አምስተኛው በር ደግሞ ከከንቲባ ፅህፈት ቤት ጋር የሚያገናኘው በር ሲሆን፣ አዲስ አበባ ለመግባት ያሉትን አምስት በሮች ተምሳሌት ያደረገ ድልድይ የተካተተበት ነው። በስተምዕራብ በኩል የሚታየው የሙዚየሙ መግቢያ በር፣ በዓድዋ ተራሮች ላይ የተደረገው አድካሚ ጉዞ ተምሳሌት እንዲሆን ተደርጎ የተገነባ መሆኑን ገልጸዋል።

በዓድዋ ድል ላይ ሚና የነበራቸው ሴቶች፣ እንዲሁም ከሰው እስከ ፈረሰኞች የነበራቸውም ሚና በሙዚየሙ ተወክለዋል። ታሪኩ በዋናው ሙዚየም የሚጀመር ሲሆን፣ በተለያዩ የጥበብ ሥራዎች በዓድዋ ድል ወቅት ዋነኛ ሚና ያላቸው ጀነራሎች፣ ንጉሠ ነግሥቱ ዳግማዊ አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱን ታሪክ የሚዘክሩ የተለያዩ የሥነጥበብ ሥራዎች የሚገኙበት ክፍል አለው።

ኢንጂነር ደቦ ቱንካ እንዳብራሩት፤ በሙዚየሙ የበርሊን ኮንፍረንስ ወይም አፍሪካን የመቀራመት ስብሰባ እና የውጫሌ ስምምነትን የሚያስታውስ ተምሳሌት እንዲሁም ስምምነቱ መፋለሱን ማሳያው የክተት አዋጅ፤ ከክተት አዋጁ በኋላ ጦርነቱ እና በድል መጠናቀቁ፤ የክተት አዋጁም ከዓድዋ ድል ባሻገር ለፓን አፍሪካኒዝም ምስረታ ውጤት ያመጣ መሆኑን የሚያመለክቱ ማሳያዎች፣ ሌሎች የዓድዋ ጀግኖችን የሚወክሉ ቅርፃ ቅርፆችና ምሰሶዎችም ተካተውበታል።

ሙዚየሙ አምፌ ትያትር ይኖረዋል፡፡ ትያትር ኢትዮጵያ ሲጀመር የነበረውን ታሪክ የሚዘከር የሚደራጅበት እንዲሁም አረንጓዴ ስፍራዎች ተካተውበታል፡፡

ኢንጂነር ደቦ እንዳስታወቁት፤ ከዓድዋ ድል በኋላም ሀገራችንን ለማፅናት የሠራናቸው ሥራዎች፣ የአሁኑ ትውልድ ያበረከታቸው አስተዋጽኦዎች፤ የዓባይ ግድብ መገንባት ድሉን በማጽናት፤ ልማትን ማፅናት የተቻለበት ነው።

ሙዚየሙ በኢትዮጵያ የላቀ ደረጃ ያለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ የያዘ ሲሆን፣ ይህም ዓድዋን



ለመዘከር እና የኩራታችን ምንጭ መሆኑን ማሳየትን፣ ምሁራን የሚመራመሩበትን፣ ሁሉም ሰው ሃሳብ የሚለዋወጥበትን ሁኔታ ታሳቢ ተደርጎ የተገነባ ነው። የመሰብሰቢያ ቦታው በአንድ ጊዜ ዘጠኝ ሺህ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል ሲስተም ተካቶበት ተሠርቷል።

የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም ፕሮጀክት አማካሪ እንዲሁም የዲዛይን ቁጥጥር እና የሱፐርቪዥን ሥራዎች የህንጻ ዘርፍ ተጠሪ ኢንጂነር አስራት ሰለሞን በበኩላቸው እንደገለጹት፣ ፕሮጀክቱ ሦስት ነጥብ ሶስት ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ነው። ግንባታውም አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በጀት ተይዞለት የተከናወነ ነው።

ፕሮጀክቱ አስራ አንድ ዋና ዋና ህንፃዎች ተካተውበታል። የመጀመሪያውና ዋነኛው ሶስት ብሎኮችን የያዘውና ዓድዋን መሠረት ያደረገው የሙዚየሙ ክፍል ነው። ይህ የሙዚየሙ ክፍል 1888 ዓ.ም ላይ ለነፃነታቸው ቀናኢ የነበሩት ኢትዮጵያውያን የከፈሉትን መስዋዕትነት ለአፍሪካውያን እና ለመላው ጥቁር ሕዝብ አርአያ መሆናቸው የሚዘከርበት፣ ለአሁኑ ትውልድ ደግሞ ታሪክ የሚሸጋገርበት ነው፡፡

ጦርነቱ የተደረገው ዓድዋ ላይ ቢሆንም.፣ ከዚያ በፊት ኢትዮጵያውያን አምባላጌ እና መቀሌ ላይም ተዋግተዋል የሚሉት ኢንጂነሩ፤ በተለይም መቀሌ ላይ የሴቶች ኢትዮጵያውያን ብልህነት እና መለኘነት የሚገለፅባቸው ሁነቶች እንደነበሩ አስታወሰዋል። በዚህ ምክንያትም በሙዚየሙ እቴጌ ጣይቱ ጣልያኖቹን ለመያዝና በጦርነት ድል እንዲገኝ ያደረጉትን አስተዋፅኦ መዘከሪያ የውሃ ኩሬ እና የእቴጌ ጣይቱ ሐውልት እንዲሁም ከጎኑ የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሐውልት እየተሠራ ይገኛል።

በአቅራቢያውም የፈረሰኞች ሚና የሚዘከርባቸው የአርት ሥራዎች፤ ከዓድዋ ጋር ተያይዘው የተሠሩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች እንዲሁም ለዓድዋ ጦርነት ምክንያት የሆነው የውጫሌ ውል በአማርኛ እና በጣሊያንኛ የሚዘከርባቸው ህንጻዎች በፕሮጀክቱ መካተታቸውን አብራርተዋል።

እንደ ኢንጂነር አስራት ገለፃ ፤ በሙዚየሙ የሚገኘው ሌላኛው ህንጻ ሁለት ሺህ 200 ሰዎችን መያዝ የሚችለው ዘመናዊ የከተማ አዳራሽ ነው። ይህ ህንጻ የጅምናዚያም የኤሮቢክስ ሥራዎች የሚሠራበትም።

አራት ሺህ ሰዎችን የማስተናገድ አቅም ያለው እና ባለሁለት ወለል የአዲስ አበባ ምክር ቤት መሰብሰቢያ ሁለገብ አዳራሽም ተገንብቷል። ቮሊቦል፣ ባስኬት ቦል፣ ቴብል ቴኒስ የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ስፖርታዊ ጨዋታዎች ማካሄጃዎችም ተሟልተውበታል። በሁለት ተጨማሪ ህንፃዎች ውስጥም ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኒማ ቀድሞ የተጀመረበትን ለማስታወስ የሲኒማ ቤቶች ግንባታ የፕሮጀክቱ አካል እንዲሆኑ ተካተዋል።

የዓድዋ ዜሮ ዜሮ ሙዚየም ፕሮጀክት ግንባታ በአሁኑ ወቅት 95 በመቶ የደረሰ ሲሆን፣ አሁን የማጠናቂቂያ ሥራዎች እየተከናወኑለት ይገኛል። ሙዚየሙ በተገነባበት አካባቢ ባሉ ሥፍራዎች የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ ናቸው። የዘንድሮው የዓድዋ በዓልም በእዚህ ታላቅ ሙዚየም እንደሚከበር ተጠቁሟል፡፡

በጉብኝቱ ወቅት እንዳስተዋልነው፤ ፕሮጀክቱ የዓድዋው ድል ታሪካዊ ሁነቶችን የሚያመላክቱ በርካታ ግንባታዎች፣ የጥበብ ስራዎች የተካተቱበት ብቻ አይደለም፤ ሲኒማ ቤት፣ ትያትር ቤት፣ ግዙፍ የስብሳባ አዳራሽን ጨምሮ የተለያዩ አዳራሾች፣ የአዲስ አበባ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱባቸው ስፍራዎች የተካተቱበት ነው፡፡ ይህ ሁሉና ፕሮጀክቱ ከተካሄደበት ስፍራ ግርጌ ባሉ ቦታዎች እየተካሄዱ የሚገኙ ልዩ ልዩ ግንባታዎች በአካባቢው ላይ የሚያመጡት ለውጥ ሲታሰብ ፕሮጀክቱ አዲስ አበባ ከተማን አዲስ ልዩ ገጽታን የሚያላብስ ይሆናል፤ ገና ከአሁኑም ይሄው መታየት ጀምሯል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለግብርናው ዘርፍ ስኬት ተገቢው እውቅና ሊሰጠው ይገባል !

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ለጀመረችው ልማት ስኬት በግብርናው ዘርፍ ያላትን ትልቅ አቅም አሟጣ ለመጠቀም ከፍ ባለ መነቃቃት መንቀሳቀስ ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። በዚህም በዘርፉ ውጤታማ መሆን ችላለች። በዘርፉ እያስመዘገበች ያለችው ይህ ውጤታማነት ዓለም አቀፍ እውቅና እያገኘ ከመጣም ውሎ አድሯል።

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ለስንዴ ልማት የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ተከትሎ ሀገሪቱ በዘርፉ እያስመዘገበች ያለችው ስኬት የብዙ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን አጀንዳ ሆኗል፤ እንደ አንድ ዓለም አቀፍ ተሞክሮም ተወስዶ እውቅና ሲቸረውም ተደጋግሞ ተደምጧል።

ከዚህም ባለፈ እንደ አፍሪካ ልማት ባንክ የመሳሰሉ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት፤ ይህን ሀገራዊ ስኬት በዓለም አቀፍ መድረክ ደጋግመው ሲያነሱ ፤ ስለዚህ ውጤታማ ተሞክሮና ሀገሪቱ በምግብ እህል ራሷን ለመቻል የጀመረችው የራሷ መንገድ ተስፋ ሰጪ ስለመሆኑ በልበ ሙሉነት ሲመሰክሩ ተሰምተዋል።

ለዚህም የአፍሪካ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት አኪንውሚ አዴሲና / ዶ/ር/ ከዓመት በፊት የሀገሪቱን የስንዴ ልማት አድንቀው ሲናገሩ መደመጣቸውን በቅርቡ በተካሄደ የዓለም የምግብ ሽልማት መድረክ ላይም ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቧን ብቻ ሳይሆን የስኬታማነት ማሳያዎችን በመጥቀስ አድናቆታቸውን ሲገልጡ ተደምጠዋል ፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ ከትናንት በስቲያ የሚኒስቴሩን የ2016 በጀት ዓመት የአምስት ወራት ሥራ አፈጻጸም አስመልክተው የሰጡት መግለጫ፤ እውነታው ከዚህም ከፍ ያለ ስለመሆኑ አመላክቷል፡፡ ሀገሪቱ አጠቃላይ በሆነው የግብርናው ዘርፍ እያስመዘገበች ያለችው ስኬት፤ አህጉራዊው የአፍሪካ ግብርና እድገት ፕሮግራም ያስቀመጠውን ግብም ያሳካ ነው፡፡

እንደ ሚኒስትሩ መግለጫ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት አማካይ የግብርና ምርት ውጤቶች የምርት እድገት ምጣኔ ስድስት በመቶ ደርሷል፤ ይህም ፕሮግራሙ በአፍሪካ ደረጃ የግብርና ምርት እድገት ያስቀመጠውን የስድስት በመቶ የእድገት ምጣኔ የሚያሟላ ነው፡፡

ሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ አዋጭ ፖሊሲዎችንና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን አስቀምጣ በትኩረት መስራቷ፤ ስኬቶችን ከማጣጣሟ ባለፈ በአህጉራዊ ተቋማት ደረጃ የተቀመጠ ግብን ማሳካት መቻሏ የአፍሪካ ኅብረትን ግቦች እያሳካች ስለመሆኗም ተጨባጭ ማሳያ ነው፡፡

በተለይ እንደ ሀገር በስንዴ ልማት የምትከተለው ብሔራዊ የስንዴ ልማት ስትራቴጂ ያስገኘው ስኬት ከሀገራዊ ፍጆታ ባለፈ፤በዓለም አቀፍ ደረጃ በስንዴ ገበያ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሊያደርጋት የሚችለውን ጠንካራ መልዕክት ማስተላለፍ አስችሏል፡፡

ሀገሪቱ ካላት ለስንዴ ልማት የሚውል ሰፊ መሬት ፤ ምቹ የአየር ንብረት ፤ ለመስኖ ልማት ሊውል የሚችል የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ አንጻር፤ እነዚህን አቅሞች በዘመናዊ ቴክኖሎጂና እውቀት አቀናጅቶ በትኩረት መስራት ከተቻለ በዘርፉ እንደ ሀገር አዲስ ታሪክ መጻፍ አስቻጋሪ ሊሆን የሚችል አይደለም።

ለዚህም በመንግሥት በኩል የተጀመረውና በብዙ መልኩ ተስፋ ሰጪ የሆነው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እንደ አንድ ማሳያ ይጠቀሳል፡፡ ልማቱ በተጀመረበት ዓመት ሦስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ማምረት ተችሏል፤ ይህ አሀዝ ባለፈው ዓመት 47 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ አሀዙን በተያዘው ዓመት ወደ 117 ሚሊዮን ለማሳደግ እየተሠራ ነው፡፡

የሀገሪቱ የግብርና ምርት እድገት በተለይ በስንዴ ልማቱ እየታየ ያለው ትልቅ እምርታ ሀገሪቱ በምግብ እህል ራስን ለመቻል የጀመረችውን ጥረት የሚደግፍ ፤ ከዛም ባለፈ ሀገሪቱ ስንዴ ወደ ውጪ በመላክ ተጨማሪ የውጪ ምንዛሪ የምታገኝበትን እድል የሚያሰፋም ነው።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ሀገሪቱ ቀደም ባለው ጊዜ ስንዴ ከውጭ ለማስገባት በየዓመቱ ከ700 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ታደርግ ነበር፡፡ የስንዴ ልማቱ ይህን ታሪክ የቀለበሰ አልፎም ተርፎ ስንዴ ለጎረቤት ሀገር በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ያስቻለም ሆኗል፡፡

በስንዴ ልማቱ የተገኘው ስኬት ዓለም በስንዴ አምራችነታቸው የሚታወቁት ሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ውስጥ በገቡበት ባለፈው ዓመት በርካታ ሀገሮች ስንዴ ለመግዛት የተቸገሩበት ሁኔታ በኢትዮጵያ እንዳይከሰት ማድረግ አስችሏል፡፡ በዚያ መልኩ ስንዴ በሀገሪቱ ተመርቶ ባይሆን ሀገሪቱ ማዳበሪያ ለመግዛት የገጠማት ፈተና በስንዴ ግዥ ሊገጥማት ይችል እንደነበርም መገመት አይከብድም፡፡

ይህ እንደ ሀገር በግብርናው ዘርፍ የተያዙ እቅዶች ስኬትን ያመላከተ፣ከዚህም አልፎ የአፍሪካ ግብርና ልማት ግብን ማሳካት የቻለ፣ ለዓለምም ጭምር ታላቅ መልዕክት ያስተላለፈ የግብርና ልማት ስኬት እውቅና ሊሰጠው፣ በሚገባው ደረጃ አድናቆት ሊቸረው ይገባል፡፡


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኑሮ ውድነቱ ፈተናና መውጫ መንገዱ

ቲሻ ልዑል

ባለንበት ወቅት የኑሮ ውድነት በሩን ያላንኳኳበት ሰው አለ ለማለት ይከብዳል፡፡ ‹‹የኑሮ ውድነቱን መቋቋም አልቻልንም፤ በየቀኑ በምርትና በአገልግሎት ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እየተደረገ በመሆኑ መኖር ከብዶናል›› የሚል ምሬት መስማት ከጀመርን ዓመታት ተቆጥረዋል። ምን መስማት ብቻ በኑሯችን ላይ የሚያሳድርብን ጫና ይለያይ እንጂ አብዛኛዎቻችን የዚሁ ችግር ሰለባም ሆነናል።

የነዳጅ ዋጋ ማሻቀብ፣ ጦርነት፣ የበሽታ ወረርሽኝ በምርቶች ላይ የሚታይ ዓለም አቀፍ የዋጋ ንረት ለኑሮ ውድነቱ እንደአሳማኝ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡ እርግጥ ነው፤ እነዚህ ችግሮች ሲከሰቱ ገበያ መደነቃቀፉ አይቀርም፡፡ ምርት ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር፤ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሊዘዋወር አይችልም፡፡ ነዳጅ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ከሚጫወተው ሚና አንጻር ድንገት የዋጋ ጭማሪ ሲደረግበት ከእርሱ ጋር ተያይዞ በአገልግሎቶችና በምርቶች ላይ ጭማሪ መምጣቱ የማይቀር ነው፡፡

በምግብ፣ በቁሳቁስ፣ በአገልግሎት እና በሌሎችም ላይ እለት ተእለት እየጨመረ የመጣው የዋጋ ንረት በሀገራችን በከፍተኛ ፍጥነት እያሸቀበ ነው፡፡ አንዳንዶች ችግራቸውን አምቀው የቤቴን በቤቴ ብለው ተቀምጠዋል፤ የባሰባቸውም ጎዳና ወጥተው ምጽዋት እስከመጠየቅ ደርሰዋል፡፡ ይህንን ሀቅ ለማረጋገጥ አካባቢያችንን እና ጎረቤቶቻችንን መቃኘት በቂ ነው፡፡

አንዳንድ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ተፅእኖዎች ለኑሮ ውድነቱ መፈጠር እንደምክንያት መጠቀሳቸው እውነትነት ቢኖረውም ከፊል እንጂ ሙሉ ድርሻ ይኖራቸዋል የሚል እምነት ግን የለኝም። ምክንያቱም አንዳንዶቹ የዋጋ ጭማሪዎች ነጋዴዎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የሚፈጥሯቸው ናቸው፡፡

እርግጥ የምንከተለው ነጻ ገበያ ነው፡፡ ነጻ ገበያ በሰለጠነው ዓለም እና በእኛ ማህበረሰብ ዘንድ እየተተረጎመ የሚገኘው ግን በተለያየ መንገድ ነው፡፡ የነጻ ገበያ እሳቤ በነጋዴው ማህበረሰብ ዘንድ ከምርት አቅርቦት፣ ጥራትና ከዋጋ አንጻር የተፎካካሪነት መንፈስን በመፍጠር አገልጋዩንም ተገልጋዩን ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ፤ ጥቂት ነጋዴዎች ምርትን አጋብሰው በመጋዘን እያከማቹ፤ በሚፈልጉት ሰአት እየቆነጠሩና የፈለጋቸውን ዋጋ እየጨመሩ የሚሸጡበት የገበያ ሥርዓት አይደለም።

ዛሬ በሀገራችን ለተፈጠረው የኑሮ ውድነትም ሆነ ችግሩን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደረገው ይሄው በነጋዴዎቻችን ዘንድ የሚስተዋለው የአስተሳሰብ መዛነፍ ነው፡፡ የሀገርና የህዝብን ችግሮች የመክበሪያ መንገድ አድርጎ ማየትና ይህንኑም ያለ ይሉንታ ተግባራዊ ማድረግ።

በርግጥ በየወቅቱ እንደምንሰማው መንግሥት በተለያዩ መንገዶች የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር በተለያዩ መንገዶች ይደጉማል። በመቶ ሚሊዮን ዶላሮችን ወጪ በማድረግም ከውጪ አስፈላጊ ሸቀጦችን ገዝቶ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላሉ የማህበረሰብ ክፍሎች በዝቅተኛ ዋጋ ያቀርባል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ስብሰባ ከምክር ቤት አባላት ለተነሱላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያ፤ መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት በሸማቾች ሪቮልቪንግ ፈንድ በርከት ያለ ገንዘብ በሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር ውስጥ እንዲንሸራሸር ማድረጉን መግለፃቸው ይታወሳል።

ከዚህ በተጨማሪ ቅዳሜ እና እሁድ በየቦታው የምናገኘው የእሁድ ገበያ የኑሮ ውድነትንና በገበያ ላይ የሚታየውን ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ለማረጋጋት ታስቦ በመንግሥት ተግባራዊ የተደረገ ነው። በነዚህ ገበያዎች ማህበረሰቡ በሌላ ቀን በውድ ዋጋ የሚገዛቸውን እቃዎች በተሻለ ዋጋ መገበያየት እንዲችል ማድረግ ችሏል፡፡

**ነዳጅ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ከሚጫወተው ሚና አንጻር ድንገት የዋጋ ጭማሪ ሲደረግበት ከእርሱ ጋር ተያይዞ በአገልግሎቶችና በምርቶች ላይ ጭማሪ መምጣቱ የማይቀር ነው**

ገበሬው ያመረተውን ምርት በቀጥታ ያለደላላ ጣልቃ ገብነት ራሱ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ማድረስ የሚችልበትን መንገድ ለማመቻቸት የገበያ ማዕከላት እየተገነቡ መሆኑም የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ከተሰሩ ስራዎች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህ ትልቅ እና ሊበረታታ የሚገባ ተግባር ነው።

ስራው ገበሬው ያመረተውን ምርት በቀጥታ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ማድረስ እንዲችል ማድረግ መቻል እና ማህበረሰቡም ምርቱን ካመረተው ገበሬ በቀጥታ መግዛት መቻሉ በመሃል በደላሎች ምክንያት የሚኖረውን የገበያ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመር ለመግታት ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡

ከዚህም ባለፈ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ምርታማነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው። ለዚህም አሁን ላይ የተጀመረውንና ውጤታማ የሆነውን የበጋ መስኖ ስንዴ በስፋት በመላ ሀገሪቱ መተግበር ያስፈልጋል። በሌሎች የምግብ እህሎች የተገኙ ውጤታማ ተሞክሮዎችንም ማስፋት ያስፈልጋል።

ገበሬው ያለ ደላላ ጣልቃ ገብነት በቀጥታ ለተጠቃሚ ምርቱን ማድረስ እንዲችል ለማድረግ የተጀመረው የገበያ ማዕከላት ግንባታም አጠናክሮ ከመቀጠል ባለፈም፤ በማእከላቱ የሚከናወኑ ግብይቶች ሥርዓት እንዲዙ ማድረግም በተመሳሳይ መልኩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ከዚህ ባሻገር የንግዱ ማህበረሰብ የህብረተሰቡ አንድ ክፍል እንደመሆኑ መጠን ከጥንት እስካሁን አብሮን የኖረውን የመተሳሰብ ባህላችንን ማስቀጠል ይኖርበታል፡፡ በእንደዚህ አይነት ጊዜ ሁሉም ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ በመተሳሰብ ነገሩ ከዚህም በላይ ከባድ እንዳይሆንብን መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡

ይህን ስል የማህረሰቡን ችግር የሚረዱ ነጋዴዎች ቢኖሩም በዚያው ልክ እኔ ብቻ ልጠቀም ባይ ነጋዴዎችም በስፋት ስለመኖራቸው ለመጠቆም ፈልጌ ነው፡፡ ያለ ትርፍ ህዝባችን ያለበት ችግር የማይታያቸው ስግብግብ ነጋዴዎች ከድርጊታቸው ሊታቀቡ ይገባል፡፡ መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት የሚወሰዳቸውን የመፍትሄ እርምጃዎች በቀላሉ ውጤት እንዳያመጡ የነዚህ አይነት ነጋዴዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነውና መታረም ይጠበቅባቸዋል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ያልተከፈለ ውለታ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

### የወታደሩ ልጅ ...

የአዲስ አበባ ልጅ ነው ። ስድስት ኪሎ «ቸሬ» ከተባለ ሰፈር ተወልዶ አድጓል ። ስለ ልጅነቱ ሲያስታውስ ፊቱ በደማቅ ፈገግታ ይበራል። ልጅነቱ ለእሱ መልካም የሚባል ነበር ። በዕድሜው እንደ እኩዮቹ ተጫውቶ ቦርቆ አሳልፏል ። ያን ጊዜ ሲያስታውስ በአእምሮው የማይጎረብጥ ትዝታ ውል እያለው ነው ።

የወታደር ልጅ ነው ። ገና ከልጅነቱ ወታደር አባቱን በአትኩሮት ሲከታተል አድጓል። ወታደር ሀሞተ ኮስታራ ነው። ቆራጥና ሀገር ወዳድ። ወታደር ድንበር ጠባቂ ርቆ ተጓዥ ነው ። ከእኔ ይልቅ ለእኛ፣ ከቤተሰብ ይበልጥ ለሀገር ፣ ወገን ቅድሚያውን ይሰጣል ።

ትንሹ ጥላሁን ይህ አይነቱ ሀቅ ለእሱ ብርቅ አይደለም። አባቱ ሁሌም ድንበር ሊያስከብሩ ከመላው ቤተሰብ ርቀው ይሄዳሉ። አለባበሳቸው ያምራል፣ አቋማቸው ይማርካል። በርካቶች ስለ እሳቸው የሚሰጡት ክብር ለየት ይላል። ይህ ሁሉ እውነት ለጥላሁን ትርጉሙ ብዙ ነው ። ሁሌም ወታደር አባቱ ከሌሎች እንደሚለዩ፣ ይሰማዋል። ክብራቸው፣ አቋምና ባህሪያቸው ይማርከዋል።

ጥላሁን ዕድሜው ከፍ ማለት ሲይዝ ውስጡ ብዙ አሰበ ። ለእሱ ከአባቱ ሙያ የበለጠ ሥራ የለም። ውትድርናን ከልብ ይወደዋል። ቆራጥነት ጀግንነት፣ ሀገር መውደድ ይሉትን ትርጉም ከወታደር አባቱ ተምሯል። ትምህርቱ እንደጓደኞቹ ነው ። ከእኩዮቹ ጋር ቀለም ቆጥሮ ይመለሳል። ልጅነትን ተሻግሮ ወጣትነቱ ሲጀምር ግን የውስጡ መሻት ከትምህርት ራቀ። ውትድርናን አጥብቆ ተመኘ ።

### የወታደር ልጅ ወታደር ...

በዕድሜው ልጅ ቢሆንም ካሰበው እቅድ አልዘገየም። የዘመኑን ግዴታ አሟልቶ በክቡር ዘበኛ ክፍል የጦር አባል መሆን ቻለ ። ጥላሁን በሚወደው የአባቱ ሙያ ላይ መገኘቱ አስደሰተው። በሙሉ ልብ ለሀገሩ ድንበር ዘብ ሊቆም ቃል ገባ። ልክ እንደ አባቱ ቆፍጣና ወታደር ሊሆን ራሱን አዘጋጀ።

ከማሰልጠኛ እንደወጣ የመጀመሪያ ምድቡ አዲስ አበባ ሆነ። ተወልዶ ባደገበት አካባቢ በወታደር ልብስ መታየት ለእሱ ክብር ነበር። አሁን ወዶና ፈቅዶ የገባበት ውትድርና ግርማ ሞገሱ ሆኗል።

ጥቂት ጊዜያትን አዲስ አበባ የቆየው የክቡር ዘበኛው ወታደር ወደ አሰብ እንዲሄድ ግዳጅ ተሰጠው። አሰብ ከአዲስ አበባ በብዙ ይርቃል፡ የአየሩ ባህሪ ሞቃታማና ለእንግዳ የሚከብድ ነው፡ ግዳጅ ነውና ጥላሁን ስፍራው መሄድ አለበት፡ ለውትድርናው አዲስ የሆነው ወጣት አሰብ ደርሶ ስራውን ጀመረ።

አሰብና ጥላሁን ዓመታትን በአብሮነት ዘለቁ። ሙቀት፣ ግለቱ የወታደር ሌላው ግዳጅ ነበር። በዚህ ስፍራ ችግርን ተቋቁሞ በአሸናፊነት መውጣት ግድ ይላል። ጥላሁን የሙያውንና የተፈጥሮን ፈተናዎች በጥንካሬው አሸንፎ ጊዜያትን ቆጠረ።

ወታደር ማረፊያው ከአንድ አይደለም። «ተነስ» ባሉት ጊዜ ጓዙን ሸክፎ ሊሮጥ ይፈጥናል። ወታደር ቋሚ ቤት የለውም። በየደረሰበት እግሩን ይተክላል። ጥላሁን ወታደር ሆኗልና በዚህ ግዳጅ ውስጥ አለፈ። አሰብን በለቀቀ ጊዜ ማረፊያው ከአንድ አልሆነም ። በየሀገሩ በየስፍራው ተጓዘ ።

ከውጊያ አውድማው፣ ከጦርነቱ እሳት ተገኘ። ወታደሩ ጥላሁን መገኛው የኤርትራ ተራሮች ሆኑ። ጀበርናውን ይዞ፣ ቆቡን ደፍቶ፣ መሳሪያውን አንግቶ ከቀበሮ ጉድጓድ መሸገ። የከረን ምድር እጁን ዘርግቶ ተቀበለው።

ኤርትራ በቆየ ጊዜ ከአስር ቦታዎች በላይ



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

ተዘዋውሯል። የሄደበት ግዳጅ ከጦርነት ስጋት አልራቀም። በየቀኑ የጥይት ድምጽ በጆሮው ያፏጫል። ታንክና ፣መድፉ ፣ በላዩ ያጓራል። ጥላሁን ይህ እውነት የማንነቱ መለያ ነው። የአባቱ ሙያ፣ የልጅነቱ ምኞት ነውና ችግር መከራውን አምኖ ተቀብሏል።

### ቁስለኛው ወታደር...

ጦርነት ክፉ ነው። ህይወት ያጠፋል፣ አካል ያጎድላል። በጦርነት የትግል ጓድን ከቅርብ ማጣት ብርቅ አይደለም። ጥላሁን ግዳጅ ላይ በቆየባቸው ዓመታት እነዚህን እውነታዎች በግንባር ተጋፍጧል፡ በጦር ሜዳ ውሎ ወድቆ መነሳት፣ ገድሎ መሞት፣ ያለ ነው።

ጥላሁን በጦር ሜዳ ውጊያ አካሉን በፈንጂ ተመቷል። ከዚህ ቁስሉ ሲያገግም ግን «በቃኝ» ብሎ ቤቱ አልቀረም። በተለየ ሞራልና ስሜት ዳግም ከግዳጅ ዋለ። እንዲያም ሆኖ ችግር አላጣውም። በሌላ አውደ ውጊያ በጥይት ተመቶ ቁስለኛ ሆነ ።

ህይወት በዓመታት የውትድርና ጉዞ ቀጠለ። ጥላሁን ከጦርሜዳ ውሎ ግዳጁን መወጣቱን አላቆመም። የኤርትራ በረሀ፣ የከረን ምድር ከዕድሜው ቀንሰው ዋጋ አስከፈሉት። የወታደር ልጅ ነውና በሆነው ሁሉ አልተማረረም። ግዴታውን በብቃት እየተወጣ ለሌላው አዲስ ግዳጅ ራሱን አዘጋጀ ።

ውሎ አድሮ ግን በሀገሪቱ አዲስ ነገር ተከሰተ ። ኢህአዴግ መላው ሀገሪቱን ሲቆጣጠር የደርግ ሥርዓት ወደቀ። ይህ አጋጣሚ በውትድርና ዓመታትን ለዘለቁ የሠራዊቱ አባላት የበዛ ፈተናን አቀበለ። በድንገት ነገሮች ተለዋወጡ፣ የነበረው እንዳልነበረ ተቀይሮ በአዲስ ታሪክ ተተካ።

### ያልተከፈለ ዋጋ...

ጥላሁን በቆየባቸው የውትድርና ዓመታት ከንጹህ ደመወዙ ያለፈ ሀብት ንብረት አላፈራም። እስከዛሬ ከሚከፈለው ጥቂት የወታደር ገቢው ለእናቱ እየሰጠ ሲጦራቸው ቆይቷል። ድንገቴው አጋጣሚ ለእሱና መሰሎቹ ያልተጠበቀ ነበር። ብዙዎቹ ከነበሩበት ተፈናቀሉ። በርካቶች ያለአንዳች ጥቅም ከጎዳና ወደቁ። ለሀገር ውለታ የከፈሉ አንጋፋዎች ዋጋቸው ተረስቶ እንደዋዛ ተቃለሉ ።

ለጥላሁን ድንገቴው የመንግሥት ለውጥ ያደረሰበት ጅራፍ ቀላል አልነበረም። ዓመታትን ያለፈበት የውትድርና ህይወት እንደ ልፋቱ አልከፈለውም። እሱም እንደ ትግል አጋሮቹ በፈተና መንገዶች ተመላለሰ። ከቀናት በአንዱ ግን ለጆሮው መልካም ነገር ደረሰ። የእሱን ልምድ በሚመጥን ደረጃ ከአንድ ታዋቂ ድርጅት በጥበቃ ሥራ ተቀጠረ። ይህ ሥራ ዓመታትን በውትድርና ላሳለፈው ጥላሁን አልከበደውም። የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እየተወጣ ዓመታትን ዘለቀ።

አምስት ዓመታትን በጥበቃ ሙያ የገፋው የቀድሞ ወታደር ህይወትን ሊያሸንፍ ቀን ተሌት ታተረ። ከውትድርናው ያተረፈው የሀገር ፍቅርና የሙያን ክብር ብቻ ነው። ስለደማ ፣ ስለቆሰለበት ታሪክ የተቀበለው የጀግንነት ሜዳይ አልነበረም ።

ጥላሁን በምስጋና ተቀብሎ በይሁንታ የሚኖርበት የጥበቃ ሥራ እንደነበረው አልቀጠለም። ከቀናት በአንዱ አምስት ዓመታት ካገለገለበት ኩባንያ መቀነሱ ተነገረው። ይህኔ የቀድሞው ቁስለኛ ወታደር ይይዘው፣ ይጨብጠው አጣ። ባሰለፋቸው የውትድርና ዓመታት አቅሙን በሚደግፍ ዕውቀትና ትምህርት አልታገዘም። ሙሉ ህይወቱን የሰጠው ለዋለበት ግዳጅና ለተሰጠው ኃላፊነት ብቻ ነው።

አሁን በድንገት የሆነበት ሥራ ማጣት ለማንነቱ ፈተና ሊሆን ግድ ብሏል። ጥላሁን ምርጫ አልነበረውም። ከሥራ ሊሰናበት ራሱን አዘጋጀ። ሥራ መልቀቁን ተከትሎ ግን ሰላም አላገኘም። ጤናው ተቃወሰ። እንደ ቀድሞው የህክምና ምርመራን መቀጠል አልቻለም። ድርጅቱን ሲለቅ ይህ ዕድል አብሮት ተቋረጠ። ዕለት በዕለት ህመሙ ተደራርቦ በሽታውን አባሰው።

### ትዳርና ህይወት...

ጥላሁን ከውትድርና መልስ ትዳር ይዞ ፣ ጎጆ ለማቅናት ሞክሯል። ከባለቤቱ ጋር የነበረው አብሮነት ግን በሰላም አልዘለቀም። ፍቅር የጠፋበት ጥምረት ኑሯቸውን አቀዝቅዞ ህይወታቸውን ረበሸው። ትዳሩ መልካም ሳይሆን ቢቀር ውሎ አድሮ በፍቺ ተቋጨ።

ባልና ሚስቱ በመሀላቸው የተፈጠረው አለመግባባት ለብዙ እንዳደረሳቸው ዛሬም ድረስ ያስታውሳል። ግጭታቸው በከፋ ጊዜ የእሱ ውሳኔ ከፍቺ በላይ ነበር። በሰላም ተለያዩ እንጂ አብሮነታቸው ቢቀጥል ኖሮ ውጤቱ መልካም እንደማይሆን ያውቃል። ከተስማሙበት ፍቺ በኋላ አባወራው በብቸኝነት ሊኖር ግድ አለው።

ጥላሁን የጤናውን ጉዳይ በቀላሉ መቆጣጠር አልቻለም። እንደዋዛ አልጋ ያስያዘው ህመም ደም ብዛት ስኳርና ኮሌስትሮን አስከትሎ ሰላም ነሳው። ከበሽታ የሚታገለው ህመምተኛ አሁን ከጎኑ ማንም የለም። ከህመሙ እኩል ችግር አብዝቶ እየፈተነው ነው።

የሚኖርበት ቤት የቀበሌ ቢሆንም ለዓመታት ሳይከፍለው የቆየ የኪራይ ውዝፍ አለበት። ይህን ቢያውቅም ለመፍትሄው ፈጥኖ አልሮጠም። ባልተመቸ ህይወት ዕዳውን እያሰበ መኖሩን ቀጠለ። ትንሽ ሻል እንዳለው ራሱን አበርትቶ መቆሙ አልቀረም። ዳግም የዘበኝነት ሥራ ጀምሮ ለህይወቱ መታገል ያዘ።

### የፈረሰው ጎጆ ...

አንድ ቀን ጥላሁን ሥራ አድሮ ወደቤቱ ጉዞ ጀመረ። ውስጡ ድካምና እንቅልፍ እየተሰማው ነው። ሰፈሩ አካባቢ ሲደርስ ግን ዓይኖቹን ማመን ተሳነው። ደሳሳዋ የድሀ ጎጆው በባለ ብርቱዎቹ ክንድ ተሰብራለች። አፉ እንደደረቀ ጠጋ ብሎ ሊጠይቅ ሞከረ። ምላሽ ከማግኘቱ በፊት የቤት ዕቃውና ጥቂት ልብሶቹ ከደጅ ተዝረክርከው ተመለከተ። የቀበሌ ቤቱን በውዝፍ ዕዳው ሰበብ እንዲለቅ ሲባል የተደረገ ውሳኔ ነበር ።

በወር ሰባት ብር ብቻ ይከፍልበት የነበረው ቤት ከእይታ ለመግባት ቀላል ነበር ። ዙሪያውን ያለው ሰፊ ቦታ ተጨማሪ ቤት ለመስራት አመቺ ነው። ውዝፉን አሰበው ለሌላ ሰው ለመስጠት ያሰቡት የቀበሌው ኃላፊዎች እሱን መንቅረው ለማስወጣት ፈጽሞ አላዘኑም።

ከዚህ በኋላ ጥላሁን በኪራይ ቤት ኑሮ መንከራተት ያዘ። ጤና ማጣቱ ከእጅ መንጣቱ ተዳምሮ በእጅጉ ተፈተነ ። ብቸኝነት የዞረበት ማንነቱ ባይተዋርነትን አክሎ በብዙ አንገላታው። ውሎ አድሮ አቅሙ ተዳከመ። ብስጭትና ጤና ማጣት ተጋግዘው አቅሉን አሳጡት። ጥላሁን ተስፋ ቆረጠ። «አለንህ» የሚል ወዳጅ ዘመድ ነጠፈበት።

ጥላሁን ጤናውን አጥቶ በደከመበት ጊዜ ውትድርናውን አስቦ ስለ ሀገር ዕድሜውን የገበረበትን አስታውሶ የጦር ኃይሎች ሆስፒታልን ደጅ ጠንቷል። በወቅቱ ግን ስለእሱ ውለታ ማንም ግድ ያለው አልነበረም። እሱን ጨምሮ ሌሎች አጋሮቹ የዕድሉ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከበር ተመልሰዋል።

የትናንትናው ክንደ ብርቱ ጥላሁን አሁን በባዶ ቤት በር ተዘግቶበት «የሰው ያለህ» ማለት ይዟል። ያለፈበት የህይወት ውጣውረድ ፈተና ሆኖ ቢጥለውም ለሀገር የከፈለው ታላቅ ዋጋ አልተመዘገበለትም። ጥላሁን ይህን ሲያስብ ውስጡ ያዝናል፣ ዓይኖቹ በዕንባ ይሞላሉ። ጠዋት ማታ በንዴት ሲበግን ቆሽቱ እያረረ መሆኑ ይሰማዋል። የዚህ ውጤት ለስኳር ህመሙ መባባስ ምክንያት ሆኗል። አንዳንዴ ሁሉን በትዕግስት ማለፍ ቢችል ህመም እንደማይበረታበት ያስባል።

በዚህ ስሜቱ ለመዝለቅ ግን ሁኔታዎች ቀላል አይደሉም። አንዱ ሲሞላ ሌላው እየጎደለ ብሶቱን ያንረዋል። ከቀናት በአንዱ ግን ይህን ታሪክ ከሚቀይር አጋጣሚ ድንገት ተገናኘ። ችግሩን በውል የሚያውቅ አንድ ወንድሙ «የወደቁትን አንሱ »ከተባለ ግብረሰናይ ድርጅት ማረፊያ እንደተገኘለት ነገረው።

### ህይወትን በእፎይታ ...

ይህ ዜና ብዙ ላየው ጥላሁን ታላቅ የምስራች ነበር። ዓመታትን ለሀገር ዋጋ ለከፈለው፣ በችግር ለተፈተነው፣ በህመም ለተሰቃየው ሰው እፎይታ ሆኖታል። ከወደቀበት ደሳሳ የኪራይ ቤት በአምቡላንስ በተወሰደ ጊዜ ውስጡ ያደረውን ስሜት ዛሬ በተለየ ትውስታ ያወጋዋል።

ጥላሁን የዛኔ አሁን ላለበት ህይወት ላበቃው ወንድሙ የተለየ ክብር ይሰጣል። ዛሬም ቢሆን ከነባለቤቱ እየመጣ ዓይኑን የሚያየው እሱ ብቻ ነው። ሌሎች በቅርብ የሚያውቁት ግን ከነመፈጠሩም አስበውት አያውቁም። ትናንት ከእሱ እጅ የበሉ፣ አብረውት ክፉ ደግ ያሳለፉ ዛሬ ጎኑ ያለመኖራቸው ሀዘን ከቁጭት ያሳድርበታል።

በውትድርና ዓለም ሳለ ሁለት ልጆችን ወልዷል። አንዱ አሰብ እያለ ተለይቶታል። ሁለተኛው ደግሞ ኑሮው በሀገረ አሜሪካ ስለመሆኑ ሰምቷል። ይህ ሁሉ ግን ለዛሬ ማንነቱ ያኖረለት አሻራ የለም። ሁኔታዎች ተለውጠው ታሪኩን ቀይረውታል ።

አሁን ላይ ጥላሁን እግሮቹ ፈጽሞ አይታዘዙትም። እንደ ልቡ መቆም ያለመቻሉም የዊልቸር ተጠቃሚ አድርጎታል። ለችግሩ መፍትሄ እንዲሆን ግን ህክምናውን በወጉ ቀጥሏል። ያለፈበትን ውጣውረድ ሲያስበው ሀዘን የሚመላለስበት ይህ ሰው ዛሬ ላይ ስላቆመው ፈጣሪ ምስጋናውን ያቀርባል።

ጥላሁን «የወደቁትን አንሱ» የተባለው ድርጅት ከወደቀበት አንስቶ ታሪኩን ቀይሮለታል። ዛሬ ትናንት ያለፈበት የብቸኝነት ፣የችግርና መከራ ህይወት ከእሱ የለም። ቢታመም ይታከማል፣ ቢራብ ጠግቦ ያድራል። ለሀገሩ በከፈለው ዋጋ ልክ ውለታው ባይመለስም። ህይወት በፈቀደችለት ዕድል ዛሬን እንዲህ እየኖረ ስለነገው ህይወት በተስፋ ይሻገራል። ጥላሁን ኩማ መንፈሰ ጠንካራው የቀድሞ ጀግና።

# ስፖርት





# የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ ነገ ይጀመራል

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ የ2016 ዓ.ም ፕሪሚየር ሊግ ውድድር ነገ በአዲስ አበባ ትንሿ ሁለገብ ስቴድየም መካሄድ እንደሚጀምር የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን አስታውቋል። በሊጉ 10 ክለቦች የሚሳተፉ ሲሆን አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መደረጉም ተገልጿል። በውድድሩ የመጀመሪያ ቀንም አምስት ጨዋታዎች ይከናወናሉ፡፡

ውድድሩ ዘንድሮ ለ8ኛ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን ከ1ኛ-4ኛ ሳምንት ያሉት የሊጉ ጨዋታዎች በአዲስ አበባ እንደሚካሄዱ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል፡፡ በዚህም መሰረት ሊጉ ነገ ጠዋት ሶስት ጨዋታዎች ሲካሄዱ 2፡30 የመጀመሪያው ጨዋታ በመቻልና አሜድላ መካከል ይደረጋል፡፡ 3፡40 ላይ ከሶስት ዓመታት በኋላ ወደ ሊጉ የተመለሰው መቐለ 70 እንደርታ ከፌዴራል ማረሚያ ይጨወታሉ፡፡ 4፡30 ፋሲል ከነማ ከሚዛን አማን ከተማ ይጫወታሉ፡፡ ከሰዓት ሁለት መረሀ ግብሮች የሚስተናገዱ ሲሆን ፤ ባህርዳር ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ 8፡00 እና ከምባታ ዱራሜ ከኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ጨዋታቸውን የሚያካሂዱ ክለቦች ይሆናሉ፡፡

ውድድሩ በየመሃሉ እረፍት እየወሰደ ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ቀሪ መረሀ ግብሮች ተከናውነው የአራቱ ሳምንት ውድድር እንደሚጠናቀቅ ተጠቁሟል። በፕሪሚየር ሊጉ 10 ክለቦች የሚያደርጉት ፍልሚያ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ለዚህም ክለቦችን በመደገፍ እና የተሻሻሉ ህጎችን ከማዘጋት አኳያ ፌዴሬሽኑ ተገቢውን ዝግጅት ማድረጉን አስታውቋል፡፡ ቅድመ ዘግጅቶች በሚደረጉበት ወቅትም ከሀገራዊ ሁኔታው ጋር ተያይዞ ተግዳሮቶች ማጋጠሙ ተጠቅሷል፡፡ አዲስ አበባ በሚደረገው ውድድርም 20 የሚደርሱ ጨዋታዎች ይደረጋሉ፡፡



**በሊጉ አስር ክለቦች ጠንካራ ፉክክር ለማድረግ ተዘጋጅተዋል፣**

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞላ ተፈራ፣ የውድድሩን መጀመር አስመልክቶ ስለተደረገው ዝግጅት ማብራሪያ ሲሰጡ፣ የሊጉ ውድድር ከተጀመረ ስምንት ዓመታትን ማስቆጠሩንና በርካታ እንቅፋቶችን በማለፍ እዚህ ደረጃ መድረሱን ተናግረዋል። በዝግጅት ወቅት ብዙ ችግሮች ማጋጠማቸውን ጠቅሰው፤ ከነዚህም ውስጥ የክለቦች የፋይናንስ ጉዳይ አንዱ እንደነበረ ገልፀዋል። ይሄን ችግር ለመፍታት ፌዴሬሽኑ ከየክለቦቹ አመራሮች ጋር በመነጋገር የፋይናንስ ችግራቸው እንዲፈታ በመደረጉ አስሩም ተሳታፊ ክለቦች ውድድራቸውን እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡ በዘንድሮው ውድድር ላለፉት ሶስት ዓመታት በነበረው ጦርነት ምክንያት ከውድድር ርቆ የነበረው መቐለ 70 እንደርታ እጅ ኳስ ክለብ እንደሚሳተፍም አስረድተዋል።

የክለቦች መፍረስ ለፌዴሬሽኑ ዋነኛው ተግዳሮት እንደሆነና ለሊጉ መዘግየትም ምክንያት መሆኑን ያነሱት አቶ ሞላ፣ ይህም ክለብ ውስጥ በሚገኙት ባለሙያዎችና አሰልጣኖች መካከል በሚፈጠር ችግር ምክንያት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ ለአብነትም የኮልፌ ቃራኒዮ ክፍለ ከተማ እጅ ኳስ የአመራርና የፋይናንስ ችግር ሳይኖርበት በአሰራር ጉድለት አለመግባባት ተፈጥሮ ክለቡ ከውድድር ውጪ ሊሆንበት የሚችል እድል ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሰዋል። የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ባደረጉት ጥረት ክለቡ ወደ ውድድሩ ሊመለስ እንደቻለ ታውቋል፡፡

የዘንድሮ ዓመት የክለቦች ፋይናንስ የተሻለ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ሞላ፣ ክለቦች የውድድሩን ወጪ እራሳቸው እንዲሸፍኑ መደረጉንና እስከ አሁን ፌዴሬሽኑ የክለቦችን የውድድር ወጪ ሲሸፍን የነበረው የራሱ ገቢ ስለነበረውና ከመንግሥት የሚደረገው ድጋፍ በቂ ስለነበር ነው ብለዋል። ከዚህ ቀደም ክለቦች ለውድድር ከ30-40 ፐርሰንት ብቻ የሚያወጡ ሲሆን ዘንድሮ 70 ፐርሰንት የውድድር ወጪን የሚሸፍኑ ይሆናል፡፡ ፌዴሬሽኑ ከመንግሥት የሚያገኘው በጀት ትንሽ በመሆኑ ከክለቦች ጋር በመነጋገር የውድድሩን አብዘኛውን ወጪ እንዲሸፍኑ ሊደረግ ችሏል፡፡

ከስፖንሰርና ከመንግሥት በጀት በሚገኘው ገንዘብ የዘንድሮውን ውድድር ለማካሄድ ሙሉ ዝግጅት መደረጉ የተጠቆመ ሲሆን፣ ለውድድሩ አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ከየክልሉ ተመልምለው ውድድሩን የሚመሩ ኮሚሽነሮችም ተሰይመዋል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴውም አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጓል፡፡

የመጀመሪያው ዙር አካል የሆነው የአራት ሳምንታት ውድድር እስከ ህዳር 20 ድረስ በወጣው መረሀ ግብር መሰረት ተካሂዶ ከተጠናቀቀ በኋላ የአንደኛ ዙር ማጠቃለያ ጨዋታዎች ከጥር 26 ጀምሮ በድሬዳዋ ከተማ ይካሄዳሉ፡፡ በዚህም ከአምስተኛ እስከ 9ኛ ሳምንት ያሉት 25 ጨዋታዎች የሚካሄዱ ይሆናል፡፡

በውድድሩ ከስፖርተዊ ጨዋነት ጋር በተያያዘ ችግሮችን ለመቅረፍ በቅድመ ዝግጀት ወቅት መሰረታዊና አዳዲስ የእጅ ኳስ ህጎችን ለክለብ ተወካዮችና አሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም የስፖርታዊ ጨዋነትን ችግር በሚቀርፍ ሁኔታ በውድድር ወቅት ተጫዋቾች ህጎችን እንዲተዋወቁ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡ በዚህም በውድድሩ የተሻለ ስፖርታዊ ጨዋነት፣ ፉክክርና በውድድሩ የሚያንጸባርቁ ወጣቶች ይታዩበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ ፌዴሬሽኑ ጠቁሟል፡፡